የሚከተለው ሠንጠረዥ 41 የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚውን በተለይ ለብሔራዊ ጠቅላላ የሥራ ምርት ድር ሻ ከእርሻ ፣ ከንግድና ከአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚዎች አኳያ በብርና ከመቶ ስሌት በንጽጽር ያሳያል ። በሠንጠረዡ በአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚው ስርና ስም የባንክ ፣ የኢንሹራንስ ፣ የመንግሥት ንብረት ፣ የመስተዳደር ፣ የአገር መከላከያ ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅቶችና ሥራዎች በአንድነት ተጠቃልሎአል ።

ሠንጠረዥ 40

በ1953 በተሠራበት መደበኛ ዋጋ የተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ለጠቅላላ ያገር ውስጥ ምርት አስተዋጽኦ በብርና ከመቶ

ክፍለ ኢኮኖሚ	ለጠቅላላ ያገር ውስጥ ምርት አስተዋጽኦ በሚሊዮን ብርና ከመቶ									
	1955		1957		1959		1962		1966	
	በብር	ከመቶ	በብር	ከመቶ	በብር	ከመቶ	በብር	ከመቶ	በብር	ከመቶ
እርሻ	1572.7	62.9	1670.3	59.5	1739.2	57.0	1838.3	53.9	1940.0	49.3
ኢንዱስትሪ	327.3	13.0	371.7	13.2	455.6	14.9	495.0	14.6	633.7	16.1
ንግድናመገናኛ	248.9	9.9	329.5	11.9	362.1	11.9	484.2	14.2	612.7	15.6
አገልግሎት	367.5	14.5	436.4	15.5	493.0	16.2	584.7	17.3	749.5	19.0
ጠቅላላ ድምር	2516.4	99.9	2807.9	100	3049.9	100	3397.2	100	3936.0	100

ምንጭ ፤ CSO, Statistical Abstract (1971, 1972, (1976)

በዚህ ሠንጠረዥ በተጨባጭ እንደተቀመጠው ፣ በአብዮቱ ዋዜማ በመጨረሻው አሥር ዓመታት ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጠቅላላ ያገር ውስጥ ዓመታዊ ምርት የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚው አስተዋጽኦ በአንደኛው ደረጃ ከ62.5 እስከ 49.3 በመቶ ፣ አገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚው በሁለተኛው ደረጃ ከ14.5 እስከ 19 በመቶ ፣ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚው በሦስተኛው ደረጃ ከ13.0 እስከ 16.1 በመቶ ሲሆን የንግድና የመገናኛ ክፍለ ኢኮኖሚው በአራተኛው ደረጃ ከ9.9 እስከ 15.6 በመቶ ነበር ።

የዘመኑ የአዲው ለማሪዎችና የኢኮኖሚ ፖሊሲ አውጭዎች ለመስተዳደርና ለመከላከያ ድርጅቶች መዉና ከ1949 እስከ 1965 ድረስ ለአራሪ አምስት ዓመታት የተሞከረውን የአምስት ዓመት ብሔራዊ የልማት ፕላን ቁምር ለኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ልማት የሚያስፈል ገው በቂ ገንዘብ ከአገር ውስጥ ምርት ፣ ንግድና አገልግሎት ሥራዎች በግብርና በቀረጥ መንገድ ማግኘት ፈጽሞ አቃታቸው ። ይህ የኢኮኖሚ ሁኔታ በሥራ ልምድ ከታመቀ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት መሪዉ ችና ፖሊሲ አውጭዎች አመቺ የሆኑ የጉምሩክ ፣ የግብርና የታሪፍ ፣ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ፖሊሲዎች በመቀየስ በማል ከፒታል አን ቨስትመንት በአገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ለማሄድ ልጉ የውጭ አገር ዜጐችና ድርጅቶች የመሬት ካፒታል በነጻ ወይም በት ንሽ ሂሳብ በመስጠት ለአገራቱ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ሥራ የሚያ ስፈልገውን ገንዘብና እውቀት ከውጭ አገር ለማስገባት ብርቱ ጥረት ማድ ረጋቸው ይታወሳል ።

በዚህ ነገር አንደ አገራቱ መሪዎች ምኞትና ፍላጐት ፣ እንግሊ ዝና አሜሪካ ቁምር የማዕራባ ካፒታሊስት መንግሥታትና ታላላቅ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ፣ የንግድ ፣ የማዕድን ድርጅቶች አነስ ተኛ ወጪ እየከፈሉ ለወቅታዊ የስትራቴጂ አገልግሎት አገራቱን ከመ ጠቀም ባሻገር ከፍተኛ የገንዘብና የእውቀቱ ወጪ እውተው በአትዮ ጵያ ሰፊ የልማት ሥራ ለማሄድ በቂ ገቢያ ሆነ ሌላ ምክንያት አላገኙም ።

በዚህ አኳያ በ1933 በፋሽዝም አገር የተተኩ የአንግሊዝ ኢምፔሪያ ሊስቶች አገሪቱን አስከ 1937 መጀመሪያ ድረስ እንደ ጥገኛ ግዛት ይዘው በገዙ ጊዜ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሰጡት ጥቅል የገንዘብ ድጐማ 3,250,000 ፓውንድ ስተርሊንግ ወይም በወቅቱ በነበረ የውጭ አገር ገን ዘብ ምንዛሬ መሠረት የኢትዮጵያ 32,000,000 ማሪቴሬዛ ብር የሚያህል ብቻ ነበር።[25] እንግሊዞች በ1945 ከአርትራ ሲወጡ ፣ በክፍለ ሀገሩ ከኢት ዮጵያ መንግሥት የቃኘውን የመር ሠፈር በውል የያዙ አሜሪካኖች የከፈ ሉትም የውጪና ኪራይ ሂሣብ ደግሞ በወቅቱ በሌላ ዓለም አነባቢ ለተ መሳከይ የመር ሠፈር ኪራይ ከሚከፍሉት ሂሳብ በጣም አነስተኛ አንደ ነበር ታውቀል ።

በድህረ ጦርነት ለመልሶ ግምቢታ ሥራ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕርዳታ ከሰጡት ታላላቅ ዓለም አቀፍ የገል ድርጅቶች የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የመልሶ ግምቢታና ልማት ባንክ (IBBD) እንደነበር አዩሪ ሳም ። እስከ 1948 መጀመሪያ ድረስ የኢትዮጵያ የውጭ አገር ዕዳ ለተጠቀሰው ባንክና ለአሜሪካ መንግሥት የሚከፈለውን ዉጭር

በ28,100,000 ብር [26] የሚገመት እንደነበር ሲታሰብ የኢትዮጵያ መን ግሥት የውጭ አገር ዕርዳታ ፍላጐትና ጥረት በምዕራቡ ካፒታሊስት መንግሥታትና ታላላቅ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ብዙ ተቀባይነት እንዳልነበረው ያመለክታል ።

በሌላ በኩል የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከእርካሽ የተፈጥሮ ሀብትና የሰው ጉልበት ጋር ለውጭ አገር ዜጐችና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የከፈቱ የኢትዮጵያ መንግሥት የኢንቬስትመንት ፡ የገንዘብና የንግድ ደንቦች በ1946—1951 በአጼ ኃይለ ሥላሴ በምዕራብ አውሮፓ ፡ በሰሜንና በማ ዕከላዊ አሜሪካ ፡ በእስያ ፡ በአፍሪካና በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች የተካ ሄዱ የሥራ ጉብኝቶች ነበሩ ። የአጼው የምዕራብ ዓለም ጉብኝቶች በ19 40ዎቹና በ1950ዎቹ ከወጡ የኢትዮጵያ መንግሥት የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲዎች ጋር በአንድነት በአገሪቱ ውስጥ ቀላል የምግብ የጨርቃጨ ርቅ ፡ የመጠጥ ወዘተ ኢንዱስትሪዎችን ለመከፈት የሚፈልጉ የውጭ አገር ዜጐችንና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶችን እንደአደፋፈሩአቸው የሚከተ ለው የታሪክ ሁኔታና ሂደት በግልጽ ያሳያል ።

ከውጭ አገር የኢንዱስትሪ ካፒታል አኳያ ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት የሥራ ግብር ፡ የጉምሩክ ቀረጥ ፡ የባንክና የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ፡ የታሪፍና የመሬት ስጦታ ደንቦችን በሚመለከት ፡ በሥራ ግብር አዋጅ ቁጥር 107 እና 173 በቅደም ተከተል በ1941 እና በ1953 ፡ በኢንዱስትሪ ፡ በትራንስፖርትና በማዕድን የሥራ መሶኮች በኢትዮጵያ ብር ከ200,000 የማያንስ ገንዘብ በሥራ ላይ ያዋሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች የምርት ድርጅቶቻ ቸው የማምረት ተግባር ከጀመሩበት ወቅት "አንስቶ ከአምስት ዓመት ለማ ይበልጥ ጊዜ ከትርፍ ግብር ነጻ" ይሆናሉ ተብሎ መታወጁ ይታወሳል ። [27]

ይህ የኢትዮጵያ ጅምር የውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስትመንት ፖሊሲ በመስከረም 5 ቀን 1956 "የውጭ አገርና የሀገር ውስጥ ገንዘብ(ካፒ ታል) በኢትዮጵያ ውስጥ በልማት ሥራ ላይ እንዲውል ለማበረታታት " በወጣ የአጼው ድንጋጌ በዝርዝር ሰፍቶና ተብራርቶ በብሔራዊ ሸንጐው ከጸደቀ በኋላ በሀዳር 1959 የአሠራር ለውጥ ተደርጐበት በአዋጅ ቁጥር 242 የአገሪቱ አንድ ዋና የኢኮኖሚ ፖሊሲ መመሪያ ሆነ ።

በተባለው ድንጋጌ — አዋጅ መመሪያ በተለይ የተሸፈኑ ከፍለ ኢኮ ኖሚዎች " የእርሻ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ የማዕድን ፡ የትራንስፖርትና የቱሪ ዝም ሥራዎች " ሲሆኑ ፡ በእነዚህ የኤኮኖሚ ዘርፎች በኢትዮጵያ ብር ከ200000 ያላነሰ ገንዘብ በምርት ሥራ ላይ ያዋሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሚከተሉ የኢኮኖሚና የሕግ እርዳታዎችን ያገኛሉ ተባለ ።

1. የማምረት ሥራ ከጀመሩበት አንስቶ ለአምስት አመታት የሥራ ግብር አይከፍሉም ።

2. የማምረቻ ድርጅቶቻቸውን የበለጠ ሲያስፋፉ ደግሞ ለሦስት ተጨማሪ ዓመታት የሥራ ግብር አይከፍሉም ።

3. " በተለይ ለእርሻና ለኢንዱስትሪ ሥራ የሚያገለግሉ የእርሻና የኢንዱስትሪ መኪናዎች ፡ ለመኪናዎቹ አስፈላጊ የሆኑ መሣ ሪዎች ፡ መለዋወጫዎች ወይም የእነዚሁ ከፍል ሁሉ ከውጭ አገር ሲገቡ የጉምሩክ ቀረጥ በገቢ ዕቃ ላይ የሚከፈል የትራ ንዛክሽን ታክስ ፡ የማዘጋጃ ቤት ታክስና ወይም በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚወሰን ሌላ ዓይነት ታክስና ግብር አይከፈልባቸውም ።

4. " በኢትዮጵያ ውስጥ በፋብሪካ የተሠሩ ዕቃዎች በውጭ አገር ገበያ ሊወዳደሩ እንዲችሉ ከውጭ ዕቃ ቀረጥ ነጻ ማድረግ አስ ፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እነዚሁ ዕቃዎች ከኢትዮጵያ ሲወጡ ለተወ ሰነ ጊዜ ከውጭ ዕቃ ቀረጥና ከትራንዛክሽን ታክስ ነጻ ይሆናሉ። በባንክ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬ አገልግሎት በሚመለከት ደግሞ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሚከተሉት ጉዳዮች የሚ ውል የውጭ ገንዘብ ምንዛሪ ይሰጣል " ። ማለትም ፡

5. " ገንዘባቸውን (ካፒታላቸውን) በኢትዮጵያ ውስጥ በልማት ሥራ ላይ ያዋሉ የውጭ አገር ባለሀብቶች ከዚሁ ሥራቸው ያገ ኙትን ትርፍ ካፒታሉ ወደ መጣበት አገር ለማስተላለፍ የሚያ ስችላቸው ።

6. " ማናቸውም የውጭ አገር ባለገንዘብ በኢትዮጵያ ውስጥ በ ሥራ ላይ ያዋለውን ገንዘብ (ካፒታል) በከፊል ወይም በሙሉ በሽጠ ወይም ሂሳቡን ባጣራ ጊዜ ከዚሁ የሚያገኘውን የተጣራ ገንዘቡን ለመውሰድ የሚያስችለው ።

7. የገንዘብ ሚኒስቴር " ወይም እርሱ የወከለው ባለሥልጣን በብ ድሩ አስቀድሞ የተሰማማበት ከሆነ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ለሚፈጸም የልማት ሥራ ድርጅቶች ከውጭ አገር ለተዋዋሉት ብድር ወለድና ዋናውንም ብድር ለመክፈል የሚሆን ።

8. " በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሥራቸውን የሚያካሂዱ የልማት ድር ጅቶች ለሥራቸው የቀጠሩአቸው የውጭ አገር ሠራተኞች ከደ መወዛቸው ቆጥበው ያጠራቀሙትን ገንዘብ ተፈጻሚነት ባለው የውጭ አገር ምንዛሬ ደንብ መሠረት ወደ አገራቸው መላክ የሚያስችላቸው ።

9. " በልማት ሥራ ላይ ለዋሉ ዕቃዎች መለዋወጫ ዕቃዎችና እን ዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ዕቃዎች መግዣ የሚ ሆናቸው ። "

ለማምረቻ ድርጅቶች የሚያስፈልጋቸውን የማይንቀሳቀስ የመሬት ካፒታል በሚመለከት እንዲሁም ፡

10. " በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሥራ የሚያቋቁሙ የውጭ አገር ድርጅቶች ለኢንዱስትሪው ሥራ ማቋቋሚያ የሚያስፈልገውን መሬት ለማግኘት ይችላሉ ። [28]

ይህ በጣም አመቺ የሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ሁልአቀፍ የውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስትመንት ፖሊሲ ከ1940ዎቹ ሁለተኛው አጋማሽ ጀምሮ ብዙ የውጭ አገር የግል ዜጐችና ድርጅቶች በአገሪቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የካፒታልና የቴክኒክ ኢንቬስትመንት የሚያደርጉባቸውን ፡ ከ1949 አንስቶ እስከ 1965 ለሦስት ተከታታይ ዙሮች የተካሄደውን የአምስት ዓመት የልማት ፕላን ጭምር ብዙ የሥራ ሁኔታዎች መንገዶችና ምክንያቶች እንደ ፈጠረ ግልጽ ነው ።

በዚህ ረገድ ለምሳሌ የውጭ አገር የግል ካፒታል ድርሻ በሁለተኛው የአምስት ዓመት የልማት ፕላን (1955—1959) በደምር 122.5 ሚሊዮን ብር ፡ በሦስተኛው (1960—1965) ደግሞ 192.9 ሚሊዮን ብር [29] ነበር ። በሁለተኛው የአምስት ዓመት የልማት ፕላን መጨረሻ በአገሪቱ ውስጥ በልዩ ልዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች አጠቃላይ የውጭ አገር የግል ካፒታል ኢንቬስትመንት መስክና መጠን በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ በግልጽ ይታያል ።

ሠንጠረዥ 41

በ1958 በተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የውጭ አገር የግል ካፒታል ስርጭትና መጠን በብርና ከመቶ

ክፍለ ኢኮኖሚ	በየክፍለ ኢኮኖሚው የካፒታል ስርጭት በብር	በየክፍለ ኢኮኖሚው የካፒታል ስርጭት ከመቶ ስሌት
ኢንዱስትሪ	166,000,000.00	58.2
ንግድና አገልግሎት	90,000,000.00	31.6
እርሻ	12,500,000.00	4.5
ትራንስፖርትና መገናኛ	9,500,000.00	3.3
ሕንጻና ኮንስትራክሽን	7,000,000.00	2.4
ጠቅላላ ድምር	185,000,000.00	100

ምንጭ ፡ Duri Mohammed, "Private Investment" (1969)

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ ውስጥ እንደተመለከተው ፡ በ1958 ከውጭ አገር የግል ካፒታል ኢንቬስትመንት 58.2 ከመቶ የያዘው የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ነበር። በኢንዱስትሪ ክፍል ኢኮኖሚውም ውስጥ፡ ከካፒታል ኢንቬስትመንት ፡ ከሠራተኛ ብዛትና ከምርት መጠን አኳያ ሲታይ በድምር አምላ ከመቶ በላይ የያዙ ቀላል ወይም አነስተኛ የምግብና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች መሆናቸውን ከሚከተለው ሠንጠረዥ ማየት ይቻላል ።

ሠንጠረዥ 42

ከጠቅላላ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የምግብና የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች የካፒታል፡ የሠራተኛና የምርት ድርሻ

ካፒታል ፡ ሠራተኛና ምርት	የምግብ ፋብሪካዎች ድርሻ ከመቶ			የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ድርሻ ከመቶ		
	በ1959	በ1961	በ1962	በ1959	በ1961	በ1962
ካፒታል ኢንቬስትመንት	28.3	39.7	15.0	27.2	17.7	25.9
የሠራተኞችብዛት	17.6	15.3	16.8	43.5	45.8	44.2
ጠቅላላ የሥራ ምርት	31.7	24.4	24.5	28.9	33.7	31.8

ምንጭ ፡ Eshetu Chole, "Import Substitution" 1973

በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት ፡ በ1959 ፡ በ1961 እና በ1962 ከኢትዮጵያ ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ካፒታል በአማካይ 51.2 በመቶ ፡ ከሠራተኛ በአማካይ 61.1 በመቶ እና ከጠቅላላ የሥራ ምርት 58.0 በመቶ የምግብና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ድምር ድርሻ እንደሆነ ማየት ይቻላል ።

ከሁሉ በፊት በአመዛኙ በአነስተኛ የምግብና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ያተኮረ የኢትዮጵያ መንግሥት የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መነሻና ተግባር ከአገሪቱ የፊውዶ ቡርዣው ሥርዓት የምርት ግንኙነት ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዘ ነበር ። በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ በንግድ ክፍለ ኢኮኖሚ ትችት በሠንጠረዥ 36 ከ1940 ጀምሮ ከውጭ ንግድና ገንዘብ ምንዛሪ አኳያ የአገሪቱ የገቢ ንግድ ዕቃዎች ዋጋ ሚዛን በወጪ ንግድ ዕቃዎች ዋጋ ላይ እንደሆነ አይተናል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት መሪዎችና የኢኮኖሚ ፖሊሲ አውጭዎች በአመዛኙ ከዚህ በላይ በተገለጸው የውጭ አገር የካፒታል ኢንቬስትመንት ዕርዳታ የምግብና የጨርቃ ጨርቅ ዕቃዎችን ጭምር በዓለም አቀፍ ንግድ ሚዛን የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ዕዳ በማስከተል የታወቁ የኢንዱስትሪ ዕቃዎችን ምትክ በአጭር ጊዜ ገደብ በአገር ውስጥ በማምረት በአንድ በኩል ለሕብረተሰቡ አስፈላጊውን የኢንዱስትሪ ምርት ለማቅረብ በሌላ በኩል ደግሞ ለተባሉ የፍጆታ ዕቃዎች የሚወጣውን የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬ ዕዳ ለማስቀረት ያስቸለናል ብለው ያመኑበት የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ስትራቴጂና ታክቲክ ቀየሱ ።

በንግድና በኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ላይ በ1955 በኢትዮጵያ መንግሥት በተካሄደው ገምገማ መሠረት ፡ በ1949—1954 የአገሪቱ ወደ ውጭ አገር የተላኩት የንግድ ዕቃዎች ዋጋ ከ155—184 ሚሊዮን ብር ሲ ሆን ፡ ከውጭ አገር የገቡ የንግድ ዕቃዎች ዋጋ ግን ከ167—228 ሚሊዮን ብር ነበር ። በግምገማው እንደተባለው ፡ ይህ ግልጽ የሆነው ፤

“ በወጪና በገቢ ንግድ መካከል ያለው አለመስተካከል የጀመረው በ1951 ሲሆን በሚከተሉትም ዓመታት በዚሁ አኳኋን ቀጥሎአል ። ይኽ ም የሆነበት ምክንያት ገቢ ዕቃዎች በፍጥነት እየጨመሩ በመሄዳቸውና ለኢትዮጵያ ንግድ የማይደግፉ ስለሆነ ነው ። ለኢንዱስትሪ የሚያገለግ ሉና ተሠርተው ያላለቁ ከውጭ አገር የሚገቡ ዕቃዎች ለንግድ ሚዛን ጉድ ለት ምክንያት ሲሆኑ እንዲሁም ተበልተው ወይም ተሠርቶባቸው የሚ ያልቁ ሸቀጦችና አንዳንድ ነዋሪ የሆኑ ዕቃዎች ገቢውን ንግድ አበርክተ ውታል ። ኢትዮጵያ በብዛት ወደ ዓለም ገበያ የምትልካቸው ከእርሻ የሚ ገኙ ሰብሎች ዋጋ እየቀነሰ በመሄዱና የማያበረታታ ሆኖ በመገኘቱ እን ዲሁም በኢንዱስትሪ ተሠርተው የሚወጡ ዕቃዎችም ዋጋ የማደግ ዝን ባሌ ያለው በመሆኑ ወደ ውጭ የሚላኩት ዕቃዎች ብዛት ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡት ዕቃዎች ብዛት ጋር ሊወዳደር አልቻለም ። ” [30]

ከአምስት ዓመታት በኋላ በ1961 በተካሄደው ሌላ የመንግሥት ግም ገማ መሠረት ለዚህ ለንግድና ለኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የምር ትና ንግድ ሚዛን ችግር መፍትሔው ከውጭ አገር ለሚገቡ የንግድ ዕቃ ዎች ምትክ የሚሆኑ የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ ማም ረት ነው ። በ1961 መንግሥታዊ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ግም ገማ በግልጽ እንደተባለው ፤

“ ከኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙት ሥራዎች የፋብሪካ ኢንዱስትሪ ተግባረዕድና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ማዕድን የልዩ ልዩ ሕንጻ ሥራና የኤሌክትሪክ ኃይል የመሳሰሉት ሁሉ ተጠቃልለው ከ1954 እስከ 1959 ባለው ጊዜ ውስጥ በዓመት አሥራ ሁለት በመቶ 12% ያህል የዕድገት መጠን አሳይተዋል ። ይህም በ1954 ለጠቅላላው የአገር ውስጥ የሥራ ውጤት ወደ እነዚህ ክፍሎች ያበረከቱትን ዘጠኝ በመቶ (9)% ድርሻ በ1959 አሥራ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ (12.5%)አሳድጉታል ።

“ ይሁንና የተጠቀሱት የልማት ክፍሎች ያሳዩት ዕድገት የተለያየ መልክና ሁኔታ አለው ። የፋብሪካዎች ውጤት በዓመት አሥራ ስድስት በመቶ (16%) ያህል በማደግ ከፍተኛነት አሳይቷል ። ይህ የሆነበትም አስቀድሞ የዕድገቱ መሠረት ዝቅ ያለ ስለነበረ ነው ። ይሁንና ዕድገቱ ከፍ ተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ። ሠራተኛን በመቅጠር ሆነ በሥራ ውጤት

ረገድ ከፍተኛውን ቦታ የያዙት የምግብና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ናቸው ። ቀጥሎም የመጠጦች ኢንዱስትሪ ከዚያም የትምባሆ ፡ የቆዳና የጫማ ኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ ውጤት አሳይተዋል ።

“ እነዚህ የመሳሰሉት ተበልተው ወይም ተሠርቶባቸው የሚያልቁ ዕቃዎችን የሚሠሩ ቀላል ከሆኑት ፋብሪካዎች ክፍል የሚቆጠሩ ናቸው ። እነርሱም ሠራተኛን በመቅጠርና በሥራ ውጤት ከሚያስገኙት ከፍተኛ ጥቅም ሌላ ከውጭ ለሚመጡት ዕቃዎች ምትክ በመሆን የአገሪቱ የውጭ አገር ንግድና የገቢ ሚዛን እንዲስተካከል ይረዳሉ ። ” [31]

ይህ የኢትዮጵያ መንግሥት የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ግምገማ ብዙ መሠረታዊ ነገሮችን ከግምት አላስገባም ። በአመዛኙ በውጭ አገር የግል ካፒታል ኢንቬስትመንት የተጀመረው የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖ ሚ ልማት ለአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚሆን የመንግሥቱን የግምጃ ቤት ገቢ መጠን ከማሳደግ ረገድ ያደረገውና የሚያደርገው ድርሻ ምን እንደሚመስል ለማየት ነገሩን ከግምገማ ሚዛን አላስገባም ።

በዚህ አኳያ በተከታታይ በ1961 በ1965 እና በ1974 በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ በተለያዩ የግምሪቻ ድርጅቶችና የሥራ መስ ኮች የተካሄዱ [32] ጥናቶች የሚከተሉ አጠቃላይ ገጽታዎችን አሳይቷል ።

አንደኛ ፡ የካፒታል ኢንቬስተመንት መስክ መጠንና ባለቤትነት በሚመለከት ፡ በ1964 ፡ ከ64 የምግብ ፋብሪካዎች 86.2 ሚሊዮን ብር ድ ምር ካፒታል 53.3 ሚሊዮን ወይም 61 በመቶ ፡ ከ29 የመጠጥ ፋብሪካዎች 26 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 5 ሚሊዮን ወይም 19 በመቶ ፡ ከ42 የጨ ርቃጨርቅ ፋብሪካዎች 81.6 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 44.4 ሚሊዮ ን ወይም 54 በመቶ ፡ ከ16 የቆዳና የጫማ ፋብሪካዎች 6.9 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 5 ሚሊዮን ወይም 72 በመቶ ፡ ከ24 የእንጨት ፋብሪካዎች 7 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 4.3 ሚሊዮን ወይም 61 በመቶ ፡ ከ6 የወ ረቀት ፋብሪካዎች 11.8 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 4.1 ወይም 34 በመ ቶ ፡ ከ16 የማተሚያ ድርጅቶች 6 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 480 000 ወይም 13 በመቶ ፡

ከ25 የኬሚካል ፋብሪካዎች 68.3 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 7.1 ሚሊዮን ወይም 10 በመቶ ፡ 28 ብረታብረት ካልሆኑ የማዕድን ሥራ ድር ጅቶች 25.2 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 6.7 ሚሊዮን ወይም 26 በመቶ፡ ከ18 የብረታብረት ሥራ ድርጅቶች 8.2 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒታል 5.6 ሚሊዮን ወይም 68 በመቶ ፡ ከ3 የብረታብረት ሥራ ፋብሪካዎች 8.6 ሚሊ ዮን ብር ድምር ካፒታል 4.4 ሚሊዮን ወይም 51 በመቶ ፡ በጥቅል አነጋ ገር ከ273 አነስተኛ የግምረቻ ድርጅቶች 335.8 ሚሊዮን ብር ድምር ካፒ

ታል 140.7 ሚሊዮን ብር ካፒታል ወይም 41 በመቶ የውጭ አገር የግል ዜጐችና ድርጅቶች ይዞታ ነበር ። [33]

ለእነዚህ የፍጆታ ዕቃ ኢንዱስትሪዎች የአገር ውስጥ ገበያ ለማስገኘት የኢትዮጵያ መንግሥት በታሪፍ ሕግ በሕብረተሰቡ የገበያ ጥቅም ላይ ያደርግ የነበረውን የፖሊሲ ተግባር የመነን መጽሔት በመጋቢት 1965 እትሙ ከዚህ እንደሚከተለው ያብራራል ። በመነን ቃል ፣ የአጼው መንግሥት ፤

" ለነዚህ ኢንዱስትሪዎች ከሚሰጠው ድጋፎች መካከል አንደኛው የኢትዮጵያ ገበያ ተመሳሳይ ከሆኑት የውጭ አገር ውጤቶች መጠበቅ ነው ። ለምሳሌ ከሀንድ የሚመጣ ካኪ አዲስ አበባ ደርሶ የሚሸጠው በሜትር አንድ ብር ቢሆንና የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሠርቶ የሚያወጣው ተመሳሳይ ካኪ በሜትር አንድ ብር ተኩል ቢሆን የገዥው ምርጫ የሀንዱን ካኪ ይሆናል ። የኢትዮጵያ ካኪ ገዥ የለውም ማለት ነው ። ስለዚህ የሀንድን ካኪ ካገራችን ካኪ በላይ ዋጋውን ከፍ የሚያደርግ ቀረጥ መጣል የመንግሥቱ ሥልጣን ነው ። መንግሥት ላገር ውስጥ ፋብሪካዎች ውጤት በቀረጥ ጥበቃ ያደርጋል የሚባለው አነጋገር ይህ ነው ።

" በመሠረቱ መንግሥት ይህ ጥበቃ የሚያደርገው ለዘለዓለሙ አይደለም ። ነገር ግን ፋብሪካዎቹ በአመራራቸው ሰልጥነውና ሠራተኞቻቸው በሙያቸው ተራቀው ሥራቸው በቅልጥፍና ለማካሄድ እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ነው ። ሆኖም ቀድሞም ከተከፈቱ በቅርብም ከተቋቋሙ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ከዚህ " የእድገት ደረጃ " የደረሱ የሉም ። ሁለቱም መንግሥት " ለታዳጊ ኢንዱስትሪዎች " የሚሰጠውን ጥበቃ የሙጥኝ እንዳሉት ይገኛሉ ።

" ይህ የሚሆነው በሁለት ዋና ምክንያቶች መሆኑን በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚገኙ የክፍሉ ባለሥልጣኖች ይናገራሉ ። አንደኛ የውጭ መንግሥታትም ቢሆኑ ለውጭ ንግድ የሚሠሩትን ኢንዱስትሪዎች በብዙ መንገድ በገንዘብ ስለሚደግፉ የነዚህ አገሮች እቃዎች ኢትዮጵያ ተልከው በርካሽ ሊሸጡ ይችላሉ ። . .

" ሁለተኛ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች " ከታዳጊ ኢንዱስትሪዎች " ጥበቃ ሊወጡ ያልቻሉት የአሠራር ቅልጥፍናቸው ገና ከሌሎች አገሮች ጋር ባለመስተካከሉ ነው ።

" አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት መንግሥት ያለማቋረጥ " ለታዳጊ ኢንዱስትሪዎች " በሚል ዓላማ ላገር ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ጥበቃ ኢንዱስትሪዎቹ ያላንዳች ሥጋት እንዲያዘግሙ አድርጐአቸዋል ። መንግሥቱ የውጭ አገር ውጤቶች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ ስለሚጥል ባገር

ውስጥ የተረጋገጠ ገበያ አላቸው ። የእግሌ ዕቃ ገበያተኞቼን ይቀማኛል የሚል ፍርሃት የላቸውም ። ስለዚህም እቃዎቻቸውን በቀልጣፋ ዘይና በቅናሽ ዋጋ ሠርተው አምጥተው ለመሸጥ አይጓጉም ። አይቻኩሉም ። የዓይነትና የጥራቱንም ደረጃ ቶሎ ቶሎ አይለውጡም ። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ባገር ውስጥ የሚጠይቁትን ዋጋ ዝቅ አድርገው ከዓለም ገበያ ዋጋ ጋር ለማስተካከል አይሹም ። ባለኢንዱስትሪዎቹ ይህን በመሰለ ሰመመን ውስጥ እንደሚገኙ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴሩ ቃል አቀባይም አልካዱም " ።

ሠንጠረዥ 43

በ1962 አንዳንድ በኢትዮጵያ የሚሠሩ የኢንዱስትሪ ዕቃዎችን የሚወዳደሩ ተመሳሳይ ዕቃዎች ከውጭ አገር እንዳይገቡ ለማድረግ የወጣ የታሪፍ ዋጋ ከመቶ

በከፍተኛ ታሪፍክ ውጭ የማይገቡ ዕቃዎች	በወረቀት የተጻፈ ዝቅተኛ የታሪፍ መጠን	ተግባራዊ የሆነ ከፍተኛ የታሪፍ መጠን
ጨርቃ ጨርቅ	140	522
ድርና ማግ	53	502
የቤት ቆርቆሮ	49	435
ከጥጥ የተሠራ ልብስ	93	388
ጫማ	110	230
ከሸክላ የተሠራ የቤትክዳን	68	188
የወንድ ሙሉ ልብስ	83	165
ሳሙና	42	120
ጀንያ	70	90

ምንጭ ፣ Adebay Adedeji, African Economies (1981)

ሁለተኛ ፣ በተጠቀሱት 273 የማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ ከጠቅላላ ኢንዱስትሪ ሠራተኛ ኃይል 1.4 በመቶ የሚሆኑ የውጭ አገር ሠራተኞች ቁልፍ የአስተዳደርና የቴክኒክ ሥራ ቦታዎችን ይዘው ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ደሞዝ 16 በመቶ እያገኙ ከአገሪቱ ብሔራዊ ባንክ ጋር በነበራቸው ሕጋዊ ስምምነት ከደሞዛቸው 35 በመቶ በውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬ ወደ እየአገሮቻቸው ይልኩ እንደነበር በሚከተሉ ሠንጠረዦች ውስጥ ይታያል ።

በሠንጠረዥ ውስጥ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት 53,992 ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች 1.4 በመቶ ወይም 765 የውጭ አገር ሠራተኞች ነበሩ ። በ1964 በ42 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩ 200 የውጭ አገር ሠራተኞች ነበሩ ። እነዚህ ጥቂት በጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሠሩ የውጭ አገር ሠራተኞች ከ1954 እስከ 1962 በየዓመቱ ከጠቅላላ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ደሞዝ ያገኙት የነበረው ድርሻ በብርና ከመቶ ሰሌት እንዲሁም ሠራተኞቹ ከደሞዛቸው በያመቱ በአገሪቱ ባንክ በኩል በውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬ ወደ አገሮቻቸው ይልኩት የነበረው የገንዘብ መጠን በሠንጠረዥ 45 ላይ ይታያል ።

ሠንጠረዥ 44

በ1964 በ273 የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ውስጥ የውጭ አገር ሠራተኞች ብዛትና ደሞዝ

የኢንዱስትሪ ዓይነት	ብዛት	ካፒታል	የሠራተኞች ደሞዝ በሚሊዮን ብር		
			ኢትዮጵያ ውያን	የውጭ አገር	ድምር
ምግብ	64	86.2	8721	189	8901
መጠጥ	29	26.0	2971	45	3016
ትምባሆ	2	4.3	581	9	590
ወረቀት ወረቀት	42	81.6	23574	200	23744
ቆዳና ጫማ	16	6.9	2164	35	2199
እንጨት	24	7.0	4198	40	4238
ወረቀት	6	11.8	680	12	692
ግትሚያ	16	6.0	1569	31	1600
ኬሚካል	25	68.3	2609	64	2673
ሊሚንትና ሸክላ	28	25.2	4024	73	4097
ብረታ ብረት	18	8.2	1478	53	1531
ብረታ ብረትና ኤሌክትሪክ	3	8.6	658	23	681
ድምር 1	273	340.1	53227	765	53992
ከመቶ 1	100	100	98.6	1.4	100
የአገር ይዞታ ከመቶ		59	ይዞታ አገራቱና ወዘይሩን አገራቱ እንደሆነ ከኢትዮጵያ ጋር የኢንቨስትመንት ከዚህ መረጃ ግልጽ ነው።		
የውጭ ይዞታ ከመቶ		41			

ምንጭ ፡ Adebay Adedji, African Economies (1981).

ሠንጠረዥ 45

ከመቶኛው የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ደሞዝ በወጪ ንግድ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ የውጭ አገር ሠራተኞች ደርሻ

ዓመት	የሠራተኞች ድምር በብር	በወጪ ንግድ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች የሚሠሩ የውጭ አገር ሠራተኞች ደርሻ						የውጭ አገር ሠራተኞች ከደመወዛቸው በውጭ ምንዛሪ ወደአገራቸው የሚልኩት ገንዘብ ለክ በብር	
		በብር		ከመቶ					
1954	17 870 000	536	100	2.9				187 635	
1955	20 159 000	604	770	2.9				211 670	
1956	22 263 000	667	890	2.9				233 762	
1957	32 965 000	988	950	2.9				346 133	
1958	41 567 000	1 247	010	3.0				436 454	
1959	48 888 000	1 466	640	3.0				513 324	
1960	53 398 000	1 601	940	2.9				560 679	
1961	57 907 000	1 737	210	2.9				608 024	
1962	61 825 000	1 854	750	3.0				649 163	

ምንጭ ፡ Eshetu Chole, Import Substitution (1973).
በአዲስ ዝንጅት በመረጃው ጥናት እንደ አመድምድን ዘመን የተደረገው የጊዜ ሰልት ከኢንዳንዱ ዓመት ሰልት አስተካክሎ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ተሰውሷል ። በዚህ ጥናት በሌላ አንባብ ባለው ሥሩ እንደሆነ ተጽፏል ።

ሠንጠረዥ 46

በ1966 በኢትዮጵያ በመንግሥትና በግል ፋብሪካዎች ውስጥ የውጭ አገር ሠራተኞች ብዛትና ደሞዝ

የደሞዝ መጠን በብር		በመንግሥትና በግል ፋብሪካዎች ውስጥ የሠራተኞች ብዛት		
በወር	በዓመት	በመንግሥት	በግል	ድምር
ከ 1500— 2249	2,286,000— 3,427,476	81	46	127
ከ 2250— 2299	2,160,000— 2,207,040	55	29	84
ከ 3000— 3749	2,052,000— 2,564,316	40	17	57
ከ 3750— 4499	1‘035,000— 1,241,724	17	6	23
ከ 4500— 5249	1,836,000— 2,141,592	28	6	34
ከ 5250— 5999	504,000— 575,904	6	2	8
ከ 6000— 6749	216,000— 242,964	1	2	3
ከ 6750— 6999	81,000 — 83,988	1	—	1
ከ 7000— 8499	756,000— 917,892	6	2	9
ከ 8500— 9999	714,000— 839,916	5	2	7
ከ10000—12500	240,000— 300,000	2	—	2
ድምር	11,862,000—14,543,802	242	113	355

ምንጭ ፡ Adedege Adedeji, African Eccnoomies (1981).

በዚህ ሠንጠረዥ በቀረበው መረጃ መሠረት ፡ በ1966 355 የውጭ አገር ሠራተኞች በመንግሥትና በግል ድርጅቶች ውስጥ በዓመት ያገኙት የነበረው የደሞዝ ድምር መጠን ከ11,862,000 እስከ 14,443,812 ብር ሲሆን በዓመቱ የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ጠቅላላ ደሞዝ መጠን 87,994,000 ብር ነበር ።

ሦስተኛ ፡ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ኪሳራ ከውጭ አገር በሚገቡ የኢንዱስትሪ ዕቃዎች ምትክ በውጭ ካፒታል ኢንቬስትመንት አማካይነት በአገር ውስጥ የአነስተኛ ኢንዱስትሪ ድርጅቶችንና ምርቶችን ለማስፋፋት ይረዳል ተብሎ ፡ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የሚገቡ የእርሻና የኢንዱስትሪ ማምረቻ መሣሪያዎችን ፡ የኢንዱስትሪ ድርጅቶችን የሥራ ግብርና በብ ሔራዊ ባንክ ለግል ካፒታል ሰዎችና ድርጅቶች የውጭ አገር ገንዘብ ምን ዛሬ አገልግሎት በሚመለከት በኢትዮጵያ መንግሥት የተወሰደው የግል ካፒታል ኢንቬስትመንት ፖሊሲ በአገሪቱ የውጭ ንግድ ሚዛን ላይ የበ ለጠ ኪሳራ በማስከተል የመንግሥቱን የገንዘብ ገቢ ምንጭና መጠን በከ ፍተኛ ደረጃ እንደቀነሰ በጥናት ተረጋግጦአል ። [34]

አራተኛ ፡ በሌላ በኩል የውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስመንት በአገሪቱ ውስጥ በተወሰኑ አካባቢዎች በተለይም በአዲስ አበባ ፡ በሸዋ ፡ በሐረርጌና በኤርትራ ክፍለ ሀገራት በ1940ዎቹ ፡ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ለወዛደር መደብና ለከተማ ዕድገት ታሪካዊ አስተዋጽኦ አድርጉአል ።

ሠንጠረዥ 47

በ1958 በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ድርጅቶች የክፍለ ሀገር ስርጭት

ተራ	የኢንዱስትሪ ሥፍራ	የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ብዛት
1	አዲስ አበባ	118
2..	ኤርትራ	91
3	ሐረርጌ	18
4	ሸዋ	10
5	ትግራይ	3
6	ወሎ	3
7	ጉጂም	2
8	ሲዳሞ	2
9	ጎንደር	1
10	አርሲ	—
11	ባሌ	—
12	ጋምጉፋ	—
13	ከፋ	—
14	ኢሉባቦር	—
15	ወለጋ	—
	ድምር	248 ፋብሪካዎች

ምንጭ ፡ A. Bequele and E. Chole, Ethiopian Economy)1964).


በዚህ ነባር የሲቪል ይሁን የሚሌቴሪ ወይም የኢንዱስትሪ ሠራተኛ በኢትዮጵያ ጉልበቱን ዕውቀቱንና ጊዜውን በሰዓት በቀንና በወር ሂሳብ እየሸጠ በቅጥር የሚሠራ ደሞዝተኛ ሰው ከ1933 ወዲህ የተፈጠረ አዲስ የኩታማ ሰው እንደሆነ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ከዚህ በላይ በልዩ ልዩ መንገዶች ምክንያቶችና ወቅቶች ተገልጸአል ።

በማዕከላዊው መንግሥት ሥር የመከላከያ ሚኒስቴር የሕዝብ ጸጥታ ጥበቃና የፖሊስ መሥሪያ ቤቶች አባሎች ሆኑ ፡ በመደበኛ መስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ሲቪል ሠራተኞች ይሁኑ ወይም እንደ ባንክ ፡ ኤሌክትሪዘ መብራትና ኃይል ፡ አየር መንገድ ፡ አውራ ጐዳና፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ቦርድ፡ ትምባሆ ሞኖፖል ፡ ምድር ባቡርና ቡና ቦርድ በመሳሰሉ ልዩ ወይም ወኪል የመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ሆኑ ሁሉም በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራና አገልግሎት መስኮች የተሰማሩ የመንግሥት ተቀጣሪ የደሞዝ ሠራተኞች ናቸው ።

የወዛደሩ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

የኢትዮጵያ አምራቹ የኢንዱስትሪ ወዛደር በታሪካዊ አመጣጡና ገጠመኝ ከአገሪቱ የመንግሥት ሠራተኛ ልዩ የሚሆንበት ዋናው ታሪካዊ ምክንያት በአመዛኙ በ1940ዎቹና በ1950ዎቹ ውስጥ የውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስትመንት ፍጡር መሆኑ ነው ። በዚህ ነገር ለምሳሌ በ1944 የሆላንዱ የግል ስኳር ኩባንያ የወንጂ የሸንኮራ አገዳ ማሳና የስኳር ፋብሪካ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በኢትዮጵያ የኢንዱስትራ ሠራተኞች ብዛት ስንት እንደነበር በትክክል የሚያሳይ ዘገባ እስካሁን የለም ። በእንድ ጥናት መሠረት ፡ በድሬዳዋ ጨርቃጨርቅና በድሬዳዋ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ውስጥ የነበሩትን 3000 ሠራተኞችን በእንድነት ሳይጨምር ፡ በ1950 አካባቢ በኢትዮጵያ የነበሩ ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ብዛት በ10000 የሚቆጠር ብቻ ነበር ። [35]

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 42 ውስጥ እንደተመለከተው ፡ በአብዮቱ ዋዜማ በኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪ ሠራተኞች ዕድገት ዋና ምክንያቶች የሆኑ ሁለት የማምረቻ ዘርፎች የአገሪቱ በአመዛኙ በውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስትመንት የተፈጠሩ የምግብና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ነበሩ ። ለምሳሌ ፡ በ1959 ፡ በ1961 እና በ1962 የሁለቱ ማምረቻ ድርጅቶች ድምር የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ድርሻ 61 በመቶ እንደነበር በተጠቀሰው ሠንጠረዥ የተመለከተው ነው ።



34 የወንጂ — ሸዋ የሸንኮራ አገዳ እርሻ በ1956

ምንጭ ፡ በያራሲው እጅ የሚገኝ የወንጂ — ሸዋ ስኳር ኩባንያ ካርታ

በ1960 አካባቢ የወንጂ—ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች ብዛት 14,000 ሲሆን የጠቅላላው የፋብሪካው ሕብረ ተሰብ አባላት ብዛት (ማለትም ሠራተኛው ከነቤተሰቡ) ደግሞ 30,000 እንደነበር ታውቋል ። [36] በዚሁ ወቅት በአ ገሪቱ በተለያዩ የጨርቃጨርቅ ማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የነበሩ ወዛደሮች ቁጥር እንዲሁም [37] በ14,000 የሚ ቆጠር ነበር ። ለጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃ ለማቅረብ ተብሎ ከ1955 ጀምሮ በአዋሽ ሸለቆ ሰፊ የተን ዳሆ ጥጥ እርሻ ሥራ መጀመሩ ይታወሳል ። በ1964 በዚህ የጥጥ እርሻ በድምሩ 87,453 ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ይሠሩ ነበሩ ። በዓመቱ ለእነዚህ ሠራተኞች የተከፈለው ገንዘብ ደግሞ 5,550,774 ብር ነበር [38] ።

ሠንጠረዥ 48

በአብዮቱ ዋዜማ የኢንዱስትሪና የመንግሥት ሠራተኞች ብዛትና ደሞዝ

ዓመት	የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ብዛትና የደሞዝ መጠን		የመንግሥት መደበኛ የመስተዳደር መሥሪያ ቤትና ያገር መከላከያ ሠራተኞች					
			የመደበኛ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ		የወ.ል መሥሪያ ቤት ሠራተኞች		ያገር መከላከያ መ/ቤት አባሎች	
	የሠራተኞች ብዛት	የደሞዝ መጠን	የሠራተኞች ብዛት	የደሞዝ መጠን	የሠራተ ኞች ብዛት	የደሞዝ መጠን	የወታደር ብዛት	የወጪ መጠን ማለትም ያገር መከላከያ በጀት
1957	47,745	32,965,000	15,803	3,223,315	9,461	2,395,580	በ4 ከፍለ ጦር	95,851,000
1958	54,800	41,567,000	16,280	3,257,264	11,309	3,120,179	ድርጅቶች ስር	11,8594,000
1959	58,694	50,976.000	16,427	3,390,500	11,595	3,200,400	በ40000 እና	98,451.000
1960	—	—	16,589	3,526,600	12,263	3,525,900	በ 50000 ከልል	86,786,000
1961	47,332	57,907,000	17,287	3,927,800	13,826	4,176,300	የሚገመቱ የሠራዊት	86,788,000
1962	48,903	61,824,000	18,494	4,331,500	14,733	4,612,500	አባሎች ነበሩ	85,341,000
1963	51,312	66,521,000	19,340	4,658,800	14,110	4,635,500		87,380,000

ምንጭ ፡ COS, Statistical Absıract, (1966, 1969, 1971, 1972)

በዚህ ሠንጠረዥ በአብዮቱ ቀዜማ በአገሪቱ በምርት መስክና ተግ በርቶ የተሰማሩ 51,312 የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ጥቅል ደሞዝ 66,521 000 ብር በመስተዳደሩ መደበኛና ወ.ል መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በአስተ ዳደርና በአገልግሎት ሥራዎች ላይ የተሰማሩ በድምር 33,450 ብር የመ ንግሥት ሠራተኞች ጥቅል ደሞዝ 9,294,300 ብር ሲሆን በአራት ከፍለ ጦር ድርጅቶች ስር ከ40,000 እስከ 50,000 የተገመቱ የሠራዊት አባሎች የሚገኙበት የአገር መከላከያ መሥሪያ ቤት ጠቅላላ በጀት 87,000,000 ብር እንደነበር ይታያል ።

የወንጂ ወዛደር የሥራና የኑሮ ሁኔታ

አምስተኛ ፡ ከዚህ በላይ በተገለጸው ታሪካዊ ሁኔታና ወቅት የኢት ዮጵያ የወዛዱ መደብ መፈጠርና ዕድገት በሕይወትና በገበረት የጠየ ቀው ቀን እጅግ በጣም ከፍተኛ ነበር ። ከ1944 እስከ 1958 ድረስ የወንጂ ሸዋ የስኳር ማምረቻ ድርጅት የታሪክ ቢጋር በኢትዮጵያ በወዛደር መደብ ልዩነትና ዕድገት ወቅት በሕይወትና በገበረት የተከፈለውን ታላቅ ዘሌ ራዊ መስዋዕትነት በብዙ ፈርጆች እንደሚከተለው ያሳያል ። የታሪኩን መረጃ በማስታወሻ የለበሰበትን ከ1953 እስከ 1958 በትምህርትና በሥራ ምክንያቶች በናዝሬት ወንጂ አካባቢ በነበርኩበት ጊዜ ነው ። በመሆኑም ከዚህ በታች የቀረበው ትንታት የሚገልጸው የድርጅቱን ከ1958 በፊት የነበረውን ሁኔታ ነው ።

በወቅቱ በናዝሬት ከተማ ከወባ ማጥፊያ ድርጅት በተገኘው በአንድ ሰነድ መሠረት ፡ በ1958 በወንጂና በአካባቢው ከፋብሪካው ጋር አብረው በተፈጠሩ በአምስቱ የኮሎኔቶቹ ፡ የገረረሰ ፡ የገንደቆሬ ፡ የመጫንና የዓለም ጤና ትንሽ ከተሞች የነዋሪው ሕዝብ ብዛት በድምር 37,000 ነበር። ከዚህ ሕዝብ 10,000 በወንጂ—ሸዋ የሸንኮራ አገዳ ማሳዎችና የስኳር ፋብሪካ ዎች ውስጥ መደበኛ ሠራተኞች ነበሩ ። በወንጂ ስኳር ማምረቻ አጠገብ የሚገኘው ፡ ‘‘ የደስታ ’’ ከረሜላ ተብሎ ድርጅት የኮሚያው ሦስተኛ ፋብሪካ ነው ።

በድርጅቱ የተሸፈነው ጠቅላላ የመሬት ስፋት 6840 ሄክታር መይም 171 ጋሻ ሲሆን ፡ ከሥራና ምርት አኳያ የኮሚያው የመሬት ይዞታ የማሳና የፋብሪካ ክፍሎች በተባሉ ሁለት ከልሎች ይከፈላል ። የማሳው ከልል ራሱ ‘‘ እንደኛ ካምፕ ’’ ፡ ‘‘ ሁለተኛው ካምፕ ’’ ‘‘ አሥራኛ ካምፕ ’’ ‘‘ . . . ተብለው በቁጥር በሚጠሩ አሥራ ስድስት መንደሮች ተከ ፍሎአል ። የማሳ መንደሮችና የፋብሪካ መንደሮች በመሉ በዘመናዊ ፕላ ንና ቅየሳ በተሠሩ የውስጥ መንገዶች እርስ በርሳቸው ተገናኝተዋል ። የቆ ብረካ ከልል መንደሮች ደግሞ ‘‘ የሸበ ግቢ ’’ ፡ ‘‘ የሲሚንቶ ሠፈር ’’ ፡ ‘‘ የብር

ጭቆ ሠፈር ” ፡ “ አንድ ዓይናማ ሠፈር ” ወዘተ . . . ተብለው የወንጂ ሕብረተሰብን ማህበራዊ ጥንቅር በሚገልጹ ስያሜዎች ይጠራሉ ።

ይህ የወንጂ ሜዳ በሸዋና በአርሲ ድምበር ከቆታ ግድብ በታች ከና ዝሬት ከተማ በስተደቡብ በአሥራ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በአዋሽ ወንዝ ዳር የሚገኝ የቀድሞ ጅሌ ማህበረሰብ አገር ነው።በሰኔ 1943የኢት ዮጵያ መንግሥት የጅሌን የወንጂ መሬት ኤች.ቪ.ኤ(H.V.A.) ለተባለው ለአንድ ሆላንዳዊ ዓለም አቀፍ ስኳር አምራች ኩባንያ ለአንድ ጋሻ በዓ መት የአንድ ብር ኪራይ ሂሳብ ለዘጠና ዓመት ኮንትራት ሰጠ ። ከ1943 እስከ 1953 ድረስ ኩባንያው በእንሰሳት እርባታ የሚኖረውን የጅሌን ሕ ዝብ አለ ካሳ ወይም የመሬት ምትክ ከአባት ከቅድመያቱ መሬት ሙሉ በሙሉ አቦረረው ። የጅሌ ሕዝብ ከወንጂ መበተን የወንጂ ስኳር ልማት በኢትዮጵያ ላይ በሕይወትና በንብረት ከአደረሳቸው ጉዳቶች አንዱና የመጀመሪያው ሆነ ።

የኤች. ቪ. ኤ ኩባንያ የጅሌን ሰፊ መሬት ከአዋሽ ወንዝ ውሃ ጋር እንደዚህ በነጻ ከአገኘው በኋላ ከኢንዶኔስያና ከደቡብ አፍሪካ የፈረሱ አሮጌ የማምረቻ መሣሪያዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ አስገብቶ በ23000, 000 ብር ካፒታል ሥራውን ጀመረ ። ከሰባት ዓመታት በኋላ በ1951 የኩ ባንያው ካፒታል ወደ 50,400,000 ብር አደገ ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሸዋና የመተሃራ ስኳር ፋብሪካዎች ሲጨመሩ የኩባንያው የካፒታል መጠን ወደ 100 ሚሊዮን ብር ደረሰ ።

በ1943 የኤች. ቪ. ኤ ኩባንያ ሥራውን በጀመረ ጊዜ ያገጠመው ታላቁ ችግር የወባ ትንኝ መናኸሪያ የነበረውን የወንጂ ረግረግ መሬት በጉ ልበታቸው የሚያለሙ የሥራ ልምድ ያላቸውን ጠንካራ ሠራተኞች ማግ ኘት ነበር ። ለችግሩ መፍትሔው እንዲሆን በኢትዮጵያ ለብዙ ጊዜ የኖረ አንድ ሲኞር ስቴላ የተባለ ኢጣሊያዊ ግለሰብ በእንስት ተክል ምርትና ባህል የከባድ ሥራ ልምድ ያላቸው ሰዎች በደቡብ ኢትዮጵያ በከምባታና ሀዲያ አገር እንደሚገኙ ለኩባንያው እንደጠቆማው ታውቋል ።

ከ1937 እስከ 1946 ድረስ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በጉልተኞችና በሕዝቡ መካከል ታላቅ የመሬት ችግር እንደነበር ይታወሳል ። [39] በመሆ ኑም በ1943—1944 ፡ በወንጂ የቅጥር ሥራ መገኘቱን የሰሙ ሰዎች በከ ምባታና ሀዲያ አውራጃ ከመሬት ችግር የሚያመልጡ መስሎአቸው በማ ያቋርጥ ሂደት ወደ ወንጂ መፍለስ ጀመሩ ።

በ1950ዎቹ መጀመሪያ በናዝሬት የተባበሩት መንግሥታት የወባ ማጥፊያ ድርጅት ከአካባቢው የወባ ትንኝ እስኪያጠፋው ድረስ በወንጂ በተለይ ከግንቦት እስከ ጥቅምት ድረስ ፡ ዱሮ የጅሌ ሰዎች ከረግረጉ ሜዳ ሸሽተው በተራራ ላይ የሚኖሩበት ወራት ፡ የወባ በሽታ ወረርሽኝ እንደ ነበር ታውቋል ። በመሆኑም የኩባንያው የስኳር ልማት ሥራ ከተጀመረ

በት ጀምሮ በመጀመሪያ ሰባት ዓመታት ውስጥ በከምባታና ሀዲያ ከመ ሬት ችግር ከተሰደዱ ሠራተኞች ከምጣዱ ወደ እሳቱ እንደሚሉት ፡ ብዙ ዎቹ በወባ በሽታ እንደአለቁ ታውቋል ።

ከአካባቢው የወባ ትንኝ እስኪጠፋ ድረስ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ግም ባታ በመጀመሪያ ዓመታት ምን ያህል የኢትዮጵያ ሠራተኞች እንደሞቱ በእጠቃላይ መንገድ ለመገመት እስከ 1958 ድረስ በወንጂና በሸዋ ስኳር ፋብሪካዎች ቀለበት ዙሪያ በሚገኙ እምስት የመቃብር ቦታዎች የሚታዩ የመቃብር ላይ ምልክቶችንና በናዝሬት ከተማ በኃይለ ማርያም ማሞ መታሰቢያ ሆስፒታል ከ1940ዎቹ ጀምሮ የሚገኙ የወንጂ ሕመማንና ሙታን መዛግብትን ማጥናት ይጠቅማል ። በተጨማሪም በ1940ዎቹ መጨረሻ በወንጂ የኩሩፋቱ አቦ ቤተ ክርስቲያንና መካነ መቃብር እስኪ መሠረት ድረስ በወንጂ የሠራተኞች ሠፈርና በናዝሬት ከተማ በኃይለ ማርያም መታሰቢያ ሆስፒታል ለብዙ ዓመታት የሞቱት ሠራተ ኞች የተቀበሩት በናዝሬት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገዳም በሆነው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሙካነ መቃብር ነው ።

በዚህ ነገር በ1958 አቶ ለማ ጠቢቃ በወንጂ — ሸዋ ሸንኮራ አገዳ ማሳ በስድስተኛው ሠፈር ውስጥ በ1940ዎቹ በወንጂ ከወባ በሽታ እል ቂት ከተረፉት ዕድለኛ ሠራተኞች አንዱ ነበር ። ለምሳሌ በወባ በሽታ ሠራተኞች በሚያልቁባቸው ዓመታት በአንድ ቀን አቶ ለማ ይኖር በት በነበረው በአንደኛው ሠፈር ሰባት ሰዎች በወባ በሽታ ሲሞቱ እሱና ጓደኞቹ የአምስቱን እሬሳ ከሰዓት በፊት ቀበረው ስለደከማቸው ለምሳ እረ ፍት ወደ ሠፈራቸው ሄዱ ። ከሰዓት በኋላ የቀሩትን ሁለት እሬሳዎች ቀበሩ ።

በ1950 አካባቢ የወባ ትንኝ ከቀበሌው እስኪጠፋ ድረስ እንደዚህ በአንድ ቀን የብዙ ሠራተኞች ሞትና ቀብር በወንጂ የተለመደ ጉዳይ እንደ ነበር ጥቂት ከዘመኑ የሞት መቅሰፍት የተረፉ የዓይን ምስክሮች በ1950 ዎቹ ይህን ጥናት በማካሄድበት ጊዜ ደግመው ደጋግመው በመራራ ትዝታ አጫውተውኛል ። ባጭሩ ከጅሌ መበተን በኋለ በወንጂ የወባ እልቂት የውጭ አገር ካፒታል በሕይወትና በንብረት በኢትዮጵያ ላይ ከአ ደረሰው ጉዳቶች ሁለተኛው መራራ ነገር ሆነ ።

በወንጂ ሠራተኞች ታሪክ ከወባ እልቂት ቀጥሎ የሚመጣው ሌላ መራራ ነገር ፡ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ሠራተኞቹ ቢታላቅ ትግል በድ ርጅቱ ውስጥና በአገር አቀፍ ደረጃ በሙያ ማህበር እስኪደራጁ ድረስ የ ኤች. ቪ. ኤ. ኩባንያ የማሳ ፡ የመስኖና የሸንኮራ አገዳ ቆረጣ ሠራተኞችን በተለይ ለሂሳብ ጥበቃና ቁጥጥር በማያመች የኮንትራት አሠራር የመበዝ በዙ ሁኔታ ነው ። የብዝበዛውን ሪቂቅ ስልትና አሠራር በትክክል ለመረ ዳት የኩባንያውን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሆላንድ ከአምስተርዳም ከተማ

ጀምሮ በወንጂ እስከ የማሳው ሠፈር የተዘረጋውን የመዋቅር ሰንሰለትና ዕዝ ግጤን ያስፈልጋል ።

1. የኩባንያው የሥራ ሕጐችና መመሪያዎች በአምስተርዳም ከተማ በሆላንድ ተዘጋጅተው ወደ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ይመጣሉ ።
2. የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ከአምስተርዳም የሚመጡ የፖሊሲና የሥራ መመሪያዎችን ለወንጂ ቅርንጫፍ የማሳና የፋብሪካ ጥምር ሠ ምሪያ ያስተላልፋል ።
3. በወንጂ በማሳና በፋብሪካ ጥምር የእስተዳደር መምሪያ ሥር የኩባንያው የማሳና የፋብሪካ ዘርፎች የየራሳቸው ውስብስብና ረጅም የመ ዋቅር ሰንሰለትና ዕዝ አላቸው ።
4. ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ፣ የማሳ ዘርፍ ራሱ በአሥራ ስድስት የእርሻ ክፍሎችና የመኖሪያ መንደሮች ተከፍሎዋል ።
5. እያንዳንዱ የአሥራ ስድስቱ የማሳው የእርሻ ክፍሎች አንድ አቬርሴር ማለትም የበላይ ተቆጣጣሪ ነጭ አላፊ (OVERSEER) "ከሽቦ ግቢ" መኖሪያው በሥራ ሰዓት በሞተር ቢስክሌት እየዞረ ከሥሩ ለሚገኙና ሙሉ በሙሉ የአገሪቱ ዜጐች ለሆኑ ሠራተኞችና የበታች ተቆጣጣሪዎች ወታደራዊ የሥራ ትእዛዝ ይሰጣል።
6. ከነጩ የበላይ ተቆጣጣሪ በታች "የፊልድ አሲስታንት" (THE FIELD ASSISTANT) ተብሎ የሚጠራ ኢትዮጵያዊ ረዳት በማሳው መኖሪያ መንደር በልዩ የፊልድ አሲስታንት ቪላ እየኖረና እየሠራ ከሥሩ ሠራተኞችን የሚቆጣጠሩ ብዙ "ዋና ካቦዎችን" እና "ረዳት ካቦዎችን" ይቆጣጠራቸዋል ። ዋና ካቦዎችና ረዳት ካቦዎች በማሳ መኖሪያ መንደር በደረጃ ከፊልድ አሲስታንት ቪላ የሚያንስ የግል መኖሪያ ቤት አላቸው ።
7. ዋና ካቦዎች ከፊልድ አሲስታንቱ የሚቀርብላቸውን የሥራ መመሪያና ትእዛዝ ለረዳት ካቦዎች ያስተላልፋሉ ።

በወንጂ ስኳር ኩባንያ ታሪክ በጣም የሚያስገርመው ነገር ከአምስተርዳም ጀምሮ በወንጂ ማሳ ክፍል እስከ ዋና ካቦ የተዘረጋው የመዋቅር ሰንሰለትና ዕዝ ለኩባንያው የስኳር ምርትና ትርፍ የመነሻ መሠረት ከሆነው ከማሳ ሠራተኛ ጋር ቀጥተኛ የሆነ የሥራ ግንኙነት አልነበረም ። እስከ 1958 በወንጂ በማሳ ውስጥ የእርሻ የመንገድ ፣ የመስኖና የአገዳ ቆረጣ ሠራተኞች በሙሉ ከረዳት ካቦ በላይ በኩባንያው ውስጥ በምንም ክፍል ከሥራ አኳያ በቀጥተኛ መንገድ የማይታወቁ ዘወትር ጊዜያዊ የቀን ሠራተኞች ነበሩ ።

8. ረዳት ካቦዎች በማሳው የእርሻ ክፍልና የመኖሪያ መንደር ከአቬርሴሩ ነጭ ፣ ከፊልድ አሲስታንቱና ከዋና ካቦ እንደ ወቅቱ አሠራርና ተጨባጭ ሁኔታ በግልጽና በስውር በሚሰጣቸው የሥራ ትእዛዝ መሠረት በማሳው መኖሪያ መንደር በኩባንያው መጋዘኖች ውስጥ በሕብረት እየኖሩ በየቀኑ የኮንትራት ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞችን ለተወሰኑ ቁርጥ የእርሻ ፣ የመንገድ ፣ የመስኖና የአገዳ ቆረጣ ሥራዎች እንደፈለጉ ቀጥረው ያሰራሉ። ያባርራሉ ። ለሠራተኞቹ የመኖሪያ ሥፍራ ይሰጣሉ ። ወይም ይከለክላሉ ። ከሥራ ጊዜ ውጪ ሠራተኞቹ ካቦዎቹን እንደ የቤት ሠራተኞችና አሽከሮች በልዩ ልዩ መንገዶች ያገለግላሉ።

ከ1953 እስከ 1958 ድረስ በተለይ በወንጂ ማሳ በሥራ መስኩችና በመኖሪያ መንደሮች ብዙ ጊዜ እንዳየሁት ፣ ረዳት ካቦዎች ከቅርብ አለቆቻቸው ከፊልድ አሲስታንቶችና ከዋና ካቦዎች በሚሰጣቸው የሥራ ትእዛዝ መሠረት በኮንትራት ስምምነት ሠራተኞችን ለተወሰኑ ቁርጥ የእርሻ፣ የመንገድ ፣ የመስኖና የአገዳ ቆረጣ ሥራዎች በየጊዜው ሲቀጥሩ ከሚያገኙት ገንዘብ የተወሰነውን ክፍል በድብቅ እንደሚሰሙአቸው በቅድሚያ ግዴታ ያስገቡአቸዋል ።

ሠራተኞቹ ለተወሰኑ ቁርጥ ሥራዎች የሚሰጣቸውን ገንዘብ በመኖሪያው መንደር ውስጥ ከማሳው ትንሽ ጽሕፈት ቤት በፊርማቸው ከተቀበሉ በኋላ በቅድሚያ በተስማሙበት መሠረት የተወሰነው ድርሻ በየፊናቸው ወስደው ለረዳት ካቦው በስውር እቤቱ ይሰጡታል ። ይህን ገንዘብ ረዳት ካቦው ፣ ዋና ካቦውና ፊልድ አሲስታንቱ በመካከላቸው በሚኖረው ስምምነትና አሠራር በአንድነት ተከፋፍለው ይወስዳሉ ።

በ1958 በወንጂ ማሳ ክፍል በእርሻና በአገዳ ቆረጣ መስኮች በድምሩ ከ3600 በላይ ጊዜያዊ የኮንትራት ሠራተኞች ነበሩ ። እነዚህን የኮንትራት ሠራተኞች የሚበዘብዙ የፊልድ አሲስታንቶች ቁጥር ቢበዛ ከሀያ የካቦዎቹ ቁጥር ደግሞ ከአንድ መቶ የሚበልጥ አልነበረም ።

በዚህ አጭር የወንጂ ሠራተኛ ታሪክ ፣ በ1958 ለረጅም ጊዜ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ከመሄዴ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የሥራቸውንና የኑሮአቸውን አሳዛኝ ሁኔታ በመስክና በመኖሪያ ሥፍራ በቅርብ ከገመገምኩ በኋላ በማሳው ክፍል በተለይ የአገዳ ቆረጣ ሠራተኞችን በሚመለከተበማስታወሻ ደብተሬ ከመዘገብኩት ነገር በከፊል እንደሚከተለው መጥቀስ እወዳለሁ ።

" አገዳ ቆራጮች በወንጂ ከስምንት ወራት በላይ አይቆዩም ። የቆረጣ ሥራ ሲጀመር መጥተው ከቆረጣ ወራት በኋላ ወደመጡበት ተመልሰው ይሄዳሉ ። የኮንትራት ሠራተኞች በመሆናቸው ሥራቸውን በቱሎ

ለመጨረስ ሌትና ቀን ያለ እረፍትይሠራሉ።ሥራ ሲኖራቸው ሲሰሩ ውለው እየሰሩ ያድራሉ ። የማታ፣የበዓልና የእሁድ እረፍት የላቸውም። አያውቁም።

" የወንጂ የአገዳ ቆረጣ ክፍል አደጋና ሞት የሚበዛበት ክፍል ነው ። ብዙ ሠራተኞች ማታ እየሠሩ እድረው በቀን በአገዳ ውስጥና በጋሪ ሥር እንደ እሬሳ ተኝተው ይገኛሉ ። ኩባንያው በይፋ ባያሳውቅም በተኙ በት በየዓመቱ በመኪና አደጋ የሚሞቱት ሠራተኞች ቁጥር አንድና ሁለት አይደለም ። ለምሳሌ በዘህ ዓመት አንድ ወጣት ሠሪ ተኛ አገዳ በተጫነ በት ጋሪ ሥር ተኝቶ ሳለ ጋሪው ሲንቀሳቀስ በጐማ ፈጨው ። ነፍሱ ወዲ ያውኑ ስላልወጣች በሆስፒታል ውስጥ ለጥቂት ቀናት በሚያስጨንቅ ሁ ኔታ ሲሰቃይ ቆይቶ ሞተ ። "

በወንጂ ስኳር ልማት ታሪክ የጅሌ ማህበረሰብ መበተንና የወዛደሩ ስቃይ ሁለት ዋና ጥቁር ነጥቦች ናቸው ። በዘመኑ ለውጭ አገርና ለአገር ውስጥ ጥምር የወንጂ ስኳር ማምረቻ ድርጅት ባለቤቶች የሚያሳስባቸው የጅሌ ማህበረሰብ መበተንና የወዛደሩ መዘረፍ ሳይሆን ከዚህ በሚከተ ለው ሠንጠረዥ የሚታየው ከፍተኛ የስኳር ምርት ብቻ ነበር ።

ሠንጠረዥ 49

በ1947-1966 የኢትዮጵያ የስኳር ኢንዱስትሪ ምርት

የምርት ዓመት	የስኳር ምርት በቶንና በኩንታል	
	በቶን	በኩንታል
1947	15,840	158,400
1948	16,172	161,720
1949	26,050	260,500
1950	32,504	325,040
1951	35,859	358,590
1952	39,857	398,570
1953	37,588	3758,80
1954	37.416	374,160
1955	59,213	592,130
1956	62.747	627,470
1957	61,698	616,980
1958	68,861	686,610
1959	76,868	768,680
1960	67,753	677,530
1961	66,199	661,990
1962	96,967	969,670
1963	108,672	1,086,620
1964	113,989	1,139,890
1965	131,824	1,318,240
1966	120,658	1,206,580
ድምር	1,166,735	11,667,350

ምንጭ ፡ CSO. Statistical Abstract (1966, 1971, 1976).

ጥገኝነትና ኋላቀርነት ፡ የላቲን አሜሪካ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የተሰኘው መጽሐፍ ደራሲያን ከክሮፍት ፡ ፍራንክና ጆንሰን ፡ ከአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት እስከ ሀያኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ፡ በተከታታይ መጀመ ሪያ የስፔኝና የፖርቱጋል ማርካንቲሌዝም ፡ ቀጥሎም የእንግሊዝ ካፒታ ሊዝም በመጨረሻም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሥርዓትና የገበያ ጥገ ኞች በመሆን ፡ በተፈጥሮና በሰው ሀብት የበለጸጉ የላቲን አሜሪካ ሕዝቦ ችና አገሮች እንዴት ዛሬ በማህበራዊ ዕድገትና ልማት ረገድ ኋላ ቀር የሆ ነው የሦስተኛ ዓለም ክፍል ሊሆኑ እንደበቁ በታሪካዊ ትንተና አመልክ ቷል ። [1]

በደራሲያኑ ግንዛቤና ግምገማ መሠረት ፡ በሥርዓትና በማህበራዊ ዕድገት ደረጃ በተለያዩ አካባቢዎች መካከል በሚፈጠረው መስተጋብር የአንዱ አካባቢ ልማትና ብልጽግና የሌላው አካባቢ ኪሳራ ሊሆን ይች ላል ። በዕድገት ደረጃ ዝቅተኛ የሆነው አካባቢ ወይም ሕብረተሰብ ከፍ ተኛ ለሆነው ጥገኛ ይሆናል ። በመሆኑም በማህበራዊ ዕድገት ደረጃ የበ ለጠ በዳበሩ የስፔን ፡ የፖርቱጋል ፡ የእንግሊዝና የአሜሪካ ሜትሮፖሊ ታን አገሮችና በአዳጊ የላቲን አሜሪካ አገሮች መካከል በተፈጠረው ታሪ ካዊ የሥርዓትና የገበያ መስተጋብር በአንድ በኩል እስከ ዛሬ ድረስ ለሜት ሮፖሊታን አገሮች ካፒታሊስት ልማትና ብልጽግና በሌላ በኩል ደግሞ ለአዳጊ ጥገኛ አገሮች ጥቃትና ኪሳራ ምክንያት ሆኖዋል ። [2]

በእነኮክሮፍት አመለካከት ፡ የላቲን አሜሪካ አገሮችን ጭምር ፡ የዛሬ የሦስተኛው ዓለም አገሮች በማህበራዊ ዕድገትና ልማት ኋላቀርነት የአገሮቹ ጥንታዊ ወይም የተፈጥሮ ሁኔታ ሳይሆን የሜርካንታሊዝምና የካፒታሊዝም ዓለም አቀፍ ዕድገትና መስፋፋት ተጽዕኖ ያስከተለው ሥር ዓታዊ ችግር ነው ። [3] በመሆኑም መፍትሔው ከዓለም አቀፍ የካፒታሊ ዝም—ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ጋር የበዝበዛና የጭቆና ግንኙነት በአብ ዮታዊ ለውጥ አቋርጠ ኣዲስ ሶሻሊስት ሥርዓትና ሕብረተሰብ መገ ንባት [4] ብቻ ነው ።

ደራሲያኑ የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም — ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ጥገኝነት ለማህበራዊ ዕድገትና ልማት እንቅፋት እንደሆነ በታሪካዊ ልም ድና መረጃ ሲያስረዱ ፡ ከአሁን በፊት የላቲን አሜሪካ አገሮች ጊዜያዊ ማህ በራዊ የዕድገትና የልማት እርምጃዎችን ለመውሰድ የቻሉት በአስራ ሰባ ተኛው ምዕተ ዓመት በአውሮፓውያን የኢኮኖሚ ቀውስ ጊዜ ፡ በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መባቻ በናፖሊዮን ጦርነት ጊዜ ፡ በ1906—1910 የመጀመሪያው ዓለም ጦርነት ጊዜ ፡ በ1920ዎቹ የካፒታሊስት ዓለም የኢ.

ኮኖሚ ቀውስ ጊዜና በ1930ዎቹ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ከአውሮፓና ከአሜሪካ ሜትሮፖሊታን አገሮች ጋር የነበራቸው የኢኮኖሚና የገበያ ጥገኛነት በተቆራረጠባቸው አጫጭር የቀውስ ወቅቶች ብቻ እንደነበር በአድናቆት አስገንዝበዋል ። [5]

እንዲሁም በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ በተፈጥሮና በሰው ሀብት የበለጠ የበለጸጉ የዛሩ ሩሲያና የላቲን አሜሪካ አገሮች የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ጥገኞች በመሆን አዲስ የማህበራዊ ሥርዓት መገንባት ሲያቅታቸው ፣ በአንጻሩ ከሩሲያና ከላቲን አሜሪካ አገሮች በተፈጥሮ ሀብትና በሰው ኃይል አነስተኛ ብቻ ሳይሆን ፊውዳል አገር የነበረው ጃፓን ከዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም—ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ጥገኝነትና ተጽዕኖ ነጻ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ የራሱን አዲስና ነጻ የሆነ ማህበራዊ ሥርዓት ከመገንባቱም በላይ በ1897 ታላቁን የሩሲያን የዛር ሠራዊት በጦር ሜዳ አሸንፎ ለመመለስ መቻሉን ደራሲያኑ ለጸረኢምፔሪያሊስት ቲሲሳቸው እንደ አንድ ሌላ ማስረጃ አቅርበዋል ። [6]

በተጨማሪም አሁን በዘመናችን በቆራጥ አብዮታዊ ትግልና ድል ከኢምፔሪያሊስት የአውሮፓና አሜሪካ የሜትሮፖሊታን አገሮች ጋር ለረጅም ዘመን የነበራትን የዘረፋና የብዝበዛ ግንኙነት ያቋረጠችውና ራሱዋ የላቲን አሜሪካዊት አገር የሆነችው ሶሻሊስት ኩባ ከብዝበዛና ከጭቆና ነጻ የሆነ አዲስ ሶሻሊስት ሥርዓትና ሕብረተሰብ ለመገንባት መቻሏን ለትምህርታቸውና ለትችታቸው እንደ አንድ ታሪካዊ ማስረጃ አመልክተዋል ። [7]

እነኮክሮፍት ጨምረው በዝርዝር ትችትና ትንተና እንደሳወቁት ፣ የላቲን አሜሪካ ጭቁን ሕዝቦችን ከሥርዓት ጥገኝነትና ብዝበዛ ነጻ ለማውጣት በሚካሄደው የትግል ታክቲክና ስትራቴጂ ሁለት የተባበሩ የመደብ ጠላቶች ከውጭ በአሜሪካ የገቢ መደብ የሚመራው ዓለም አቀፍ የኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ፣ ከውስጥ ደግሞ የኢምፔሪያሊዝም ሥርዓት ጥገኛ ወኪል የሆኑት የላቲን አሜሪካ ብሔራዊ የቡርጎ ገቢ መደቦች ናቸው ። [8] ሁለቱ የሠርቶ አደር ሕዝብ ጠላቶች እርስ በርሳቸው ካልተደጋገፉና ግምባር ካልፈጠሩ ሊኖሩም ሕዝቡንም ሊበዘብዙ አይችሉም ። [9] ጭቁኑም ሕዝብ ደግሞ በአብዮታዊ አንድነትና ትብብር ተነስቶ ሁለቱንም ጠላቶች እስኪያጠፋአቸው ድረስ ራሱን ከሥርዓት ጥገኝነት ዘረፋ ነጻ ለማውጣት አይችልም ።

በላቲን አሜሪካ አገሮች የመሬት ፣ የማዕድን ፣ የእርሻ ፣ የንግድ ፣ የባንክ ፣ የገንዘብና የኢንዱስትሪ መሠረታዊ ሀብቶችንና ድርጅቶችን ከመንግሥት ሥልጣን ጋር የያዙ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የቡርጎ ገቢ መደቦች ፣ ድምበር ዘለል የአውሮፓና የአሜሪካ ሜትሮ ፖሊታን አገሮች ኩባንያዎች ፣ የዓለም ባንክ ፣ ዓለም አቀፍ ሞኒታሪ ፈንጅ ፣ ከአሜሪካ መንግሥት ለጥገኛ የቡርጂ መንግሥታት አለገደብ የሚሰጣቸው ወታደራዊ ትምህርትና የመሣሪያ ዕርዳታ ፣ የገንዘብ ዕርዳታና ብድር ፕሮግራሞች፣የኢምፔሪያሊስት አገሮች የዓለም ንግድ ሥርዓትና የካፒታል ኢንቬስትመንት ፖሊሲ ዛሬ ኢምፔሪያሊዝም ሕዝቦችን የሚበዘብዝባቸውና የሚዘርፍባቸው ዓይነተኛ መሣሪያዎችና መንገዶች እንደሆኑ ጸረ ኢምፔሪያሊስት ደራሲያኑ በመረጃ አሀዝና በምሁራዊ ትንተና አስረድቷል ። [10]

ከአገር ዕድገትና ልማት አኳያ ፣ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ብሔራዊ የአምስት ዓመት የልማት ፕላን በሚል የፖሊሲ መነሻ የኢትዮጵያ የፊውዶ ቡርጎ ገቢ መደብ በውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስትመንት አማካይነት ለማድረግ እንደሞከረው ፣ ከውጭ በሚገቡ የኢንዱስትሪ ዕቃዎች ምትክ በአገር ውስጥ አነስተኛና ቀላል የምግብ ፣ የመጠጥ ፣ የጨርቃጨርቅ ወዘተ ማምረቻ ድርጅቶችን ለመገንባት የሚካሄደው የአንድ አገር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ተግባር ፤

1. ለአገር ዕድገትና ልማት የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ከባድ የኢንዱስትሪ ምርት መሣሪያዎችን በአገር ውስጥ ስለማያስገኝ፣
2. ለአነስተኛና ለቀላል ኢንዱስትሪዎች ምርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችንና ብዙ ተጓዳኝ የማምረቻ ዕቃዎችን በቴክኖሎጂያዊ ግዴታ ከውጭ አገር በማስገባት በባንክ በኩል የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ በማስወጣት በውጭ ንግድ ሚዛን ላይ የበለጠ ኪሳራ ስለሚያስከትል ፣
3. ከአነስተኛ ኢንዱስትሪ ግምባታ ጋር በተያዙ ምክንቶች በውጭ አገር ሠራተኞች ቅጥርና በመሳሰሉት ብዙ መንገዶች በአንድ አገር የውጭ ገንዘብ ምንዛሪ ላይ አሁንም የበለጠ ኪሳራ ስለሚያስከትልና በሌላም ብዙ ተዛማጅ ምክንያቶች ፣

የማይሠራ ጃፓን ጭምር የአውሮፓና የአሜሪካ ሜትሮፖሊታን ኢምፔሪያሊስት መንግሥታትና ድምበር ዘለል ኩባንያዎች የኤኮኖሚ ጥገኝ በሆኑት የላቲን አሜሪካ ፣ የአፍሪካና የእስያ አገሮችን ሀብትና ጉልበት በልዩ ልዩ መንገዶች የሚዘርፉበትና የሚበዘበዙበት ልዩ የምዝበራ መሣሪያና ዘዴ እንደሆነ ደራሲያን ኮክሮፍት ፣ ፍራንክና ጆንሰን በመጽሐፋቸው በከፍተኛ ምሁራዊ ብቃት አረጋግጠዋል ። [11] ለችግሩ መፍትሔ ይሆናል ብለው በሰነዘሩት የመደምደሚያ አቋማቸው ፣ ደራሲ

ያኑ ጭቁኑ ሕዝቦች ከዚህ የሥርዓት መከራና ብዝበዛ ራሳቸውን ነጻ ለማ ውጣት ብቸኛው መንገድና የተግባር እርምጃ በአብዮታዊ አመጽና ትጥቅ የካፒታሊዝም ሥርዓት ደምስሶ በምትኩ ከብዝበዛ ነጻ የሆነ ሶሻሊስት ሥርዓትና ሕብረተሰብ መገንባት እንደሆነ ገልጸዋል ። [12]

ከዚህ በላይ እንደተገለጹት የላቲን አሜሪካ ጥገኛ የቡርዣ መንግሥ ታትና የገዥ መደቦች ሁሉ ፣ የኢትዮጵያም የፊውዶ ቡርዣ ሥርዓት የኢ ምፔሪያሊዝም ጥገኛ ሥርዓት ነበር ። በመሆኑ ከኢምፔሪያሊዝም የፖለ ቲካ ፣ የኢኮኖሚና የባህል ተጽዕኖ ነጻ የሆነ አዲስ ሕብረተሰብና ሥርዓት መገንባት አቃተው ። በዚህ ውድቀቱ ከዛሩ ሩሲያና ከላቲን አሜሪካ ጥገኛ አገሮችና የገዥ መደቦች ጋር በዓይነት አንድ ነበር ። በግል ጦርና በአካ ባቢ ኢኮኖሚ በተደራጁ ፊውዳል መሳፍንቶችና ባላባቶች ውድቀት በኢ ምፔሪያሊዝም ድጋፍ የተማከለው ዘውዳዊ ሥርዓትና ሥልጣን ራሱ የኢ ምፔሪያሊዝም ጥገኛ ኃይል በመሆኑ ለኢትዮጵያ አዲስ ሥርዓትና ሕብረ ተሰብ ለመገንባት የፖለቲካ መሣሪያ ሆኖ ለመገልገል አልቻለም ።

በድህረ ጦርነት የጥገኛው የገዥ መደብ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የገጠሩን እርሶ አደር ሕዝብ ከገባርነት ወደ ጪሰኝነት በመለወጥ ለጉልተኛው ብዝ በዛና ዘረፋ ዳረገው ። የጥገኛው የገዥ መደብ ጥንታዊ የመሬት ይዞታና የእርሻ ፖሊሲ በእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ውድቀት አስከተለ ። የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ ውድቀት ደግሞ በአገሪቱ የንግድ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ተ መሳሳይ ውድቀት አስከተለ ። በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ንጉሣዊ የፊውዶ ቡርዣው ገዥ መደብ በውጭ አገር ካፒታል ኢንቬስትመንት አማካይነት የኢንዱስትሪ ክፍል ኢኮኖሚ ለመገንባት ያካሄደው ፖሊሲ ደግሞ በአ ንድ ፈርጅ የአገሪቱን ወዛደራዊ መደብ ለውጭ ካፒታል ብዝበዛ ዳረገው፣ በሌላ በኩል አገሪቱን የኢምፔሪያሊዝም ጥገና አደረገ ።

ይህ አዲስና አያገኛ የሆነ የሥርዓት ሁኔታና ሂደት በመጨረሻ የኢ ትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ በዓለም ኢምፔሪያሊዝም ሥርዓትና በጥገኛው ፊውዶ ቡርዣ የገዥ መደብ ላይ በአብዮታዊ አመጽ እንዲነሳ ቀሰቀሰው ። የአመጹ ዋና ተዋኒያኑ በድህረ ጦርነት የፊውዶ ቡርዣው ሥርዓት ራሱ የፈጠራቸው የአገሪቱ አምራች የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ፣ በአስተዳደርና በአገልግሎት ሥራ የተሰማሩ የመስተዳደሩ የቢሮ ሠራተኞች ፣ የአገር መከ ላከያ ወታደሮች ፣ ሥራ አጥ የከተማ ቦዘኔዎችና በትምህርትና በባህል መስክ የተሰማሩ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ሆኑ ።

ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 49 በአብዮቱ ዋዜማ የአገሪቱ የወዛ ደሩ ፣ የመስተዳደር ሠራተኞችና የአገር መከላከያ ወታደሩ ዕድገትና ቁጥር በጥቅል መልኩ ቀርቦአል ። በሚቀጥለው ሠንጠረዥ 50 ደግሞ

የተማሪዎቹ ዕድገትና ቁጥር በአብዮቱ ዋዜማ ይታያል ። እነዚህ በድህረ ጦርነት በፊውዶ ቡርዣ ሥርዓት ውስጥ የተፈጠሩና በድምር በ940,000 የሚቆጠሩ የሕብረተሰቡ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ክፍሎች በታሪካዊ አመጣጣቸውና በሥርዓቱ ብዝበዛ ከአገሪቱ የገጠር አርሶ አደሩ መደብ ጋር የነበራቸው የትግል አንድነት በዚህ ጥናት አገባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ሁሉ ይታያል ። በሚቀጥለው ክፍል በአብዮት ዋዜማ የእነዚህ የሕብ ረተሰቡ ክፍሎች ጸረ ፊውዳሊዝምና ጸረ ኢምፔሪያሊዝም ትግል ይዘትና ሂደት በአጭርና በጥቅል ይቀርባል ።

ሠንጠረዥ 50

በአብዮቱ ዋዜማ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዕድገትና ብዛት

የትምህርት ደረጃ	በተመረጡ የናሙና ዓመታት በተለያዩ ደረጃዎች የተማሪዎችብዛት በቁጥር				
	በ1953	በ1957	በ1958	በ1960	በ1963
የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ፣ ክፍል 1—8	240987	372407	407562	492989	728548
የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ፣ ክፍል 9—12	8533	22974	26776	27025	62625
የኮሌጅ ተማሪ					
በአገር ውስጥ	939	1643	2256	2862	4543
በውጭ አገር	1019	1470	1565	1852	2203
	251,478	398,494	438,459	526,728	797,919

ምንጭ ፣ CSO. Statistical Abstract (1966, 1971)
Markakis, Ethiopia (1974).

በዚህ ሠንጠረዥ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በየዓመ ቱ በአራቱ የመንግሥት፣ የሚሲዮን፣የግልና የቤተ ክህነት ትምህርት ቤቶች በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት መሠረት ዘመናዊ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ድምር ብዛት ነው ። ለምሳሌ በ1960 በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከነበሩ ከአገሪቱ ጠቅላላ ተማሪዎች 406,000 የመንግሥት ፣ 47,000 የሚሲዮን ፣ 60,000 የግል 18,000 የቤተ ክህነት ተማሪዎች ነበሩ ። ከዚያ በፊት በ1952 ከአገሪቱ ጠቅላላ ተማሪ ዎች 82.3 በመቶ የመንግሥት ፣ 9.1 በመቶ የሚሲዮን ፣ 6.6 በመቶ የግል እና 2.0 በመቶ የቤተ ክህነት ተማሪዎች እንደነበሩ በ1958 ዓመታዊ የስ ታቲስቲክስ መጽሔት ተመልክቷል ።

ክፍል አራት

አብዮታዊ የሕዝብ አመፅ
1953-1966

ምዕራፍ 1 የሕዝብ አመፅ
የሕዝብና የከተማ ዕድገት ፤

በ1937 የታተመውን አዲስ ብሔራዊ ገንዘብ ስርጭት መሠረት አድርጐ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የሕዝብ ብዛት በ20,000,000 መገመቱ ይታወሳል ። ከ1937 የባንክ ግምት ጀምሮ በ1967 የመሬት አዋጅ መሠረት ሕዝቡ በገበሬና በከተማ ማህበራት እስኪደራጅ ድረስ በ30 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዛት በሚመለከት አስተማማኝ ግምት ይሁን ቆጠራ የተደረገበት ጊዜ አልነበረም ። ለማድረግም አመቺ የሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አልነበሩም ። በ1948 የተሻሻለ ሕገ መንግሥት መሠረት ለአራት ተከታታይ ጊዜያት በ1950 ፣ በ1954 ፣ በ1958 እና በ1962 በተካሄዱ የብሔራዊ የሸንጐ ምርጫዎችም የሕዝብ ተሳትፎ የተወሰነ ስለነበር ከምርጫዎቹ የተገኙ ውጤቶች ለሕዝብ ብዛት ግምት አስተማማኝ መረጃዎችና መንገዶች አልሆኑም ። [1]

በመጨረሻ ይህ ደራሲ በገጠርና በከተማ መሬት አዋጆች መሠረት የተደራጁ የገበሬና የከተማ ማህበራትን ስታትስቲካዊ መረጃ እንደ መነሻ አድርጐ በ1969 ባካሄደው የሕዝብ ብዛት ግምት የሚከተለው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው ፣ በ1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በፈነዳ ጊዜ የአገሪቱ የሕዝብ ብዛት በ40,000,000 የሚገመት ነበር ። ቀጥሎ በ1976 በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት የሕዝቡ ብዛት በ42,000,000 የሚቆጠር መሆኑን አሳይቷል ። በመሆኑም በ1967—1969 የገበሬና የከተማ ማህበራት ስታትስቲስክ መሠረት የተካሄደው የሕዝብ ብዛት ግምት ከእውነት የራቀ አይደለም ። ስለዚህ በ1937 በብሔራዊ ባንክ በ20,000,000 የተገመተው የኤትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከ30 ዓመታት በኋላ በእጥፍ አድጐ በ1966 ወደ 40 ሚሊዮን አካባቢ መድረሱ አስገራሚ ነገር አይሆንም ።

በዚህ ሠንጠረዥ በ1969 የገበሬና የከተማ ማህበራት ስታቲስቲክስ መሠረት የሕዝብ ግምትና በ1976 የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤቶች መካከል በ3,000,000 የሚቆጠር ልዩነት የታየበት ምክንያት በአካባቢዎቹ

ሠንጠረዥ 51

በ1969 የገበሬና የከተማ ማህበራት ስታቲስቲክስና በ1976 ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራ መሠረት ውጤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ግምት

ክፍለ ሃገር	በ1969 የገበሬና ከተማ ማህበራት ስታቲስቲክስ መሠረት				በ1966 ጠቅላላ የክፍለ ሃገር ሕዝብ ብዛት	በ1976 ቅ.ነጠራ ውጤት
	የገበሬና የከተማ ማህበራት ብዛት	የገበሬ ቤተሰብ ብዛት	የገበሬ ቤተሰ. ች ብዛት በ5 አማካይ ቁጥር ሲበዛ			መሠረት የክፍለ ሃገር ሕዝብ ብዛት
ሽዋ	6147	1 843 000	1843000 X 5		9 215 000	8 050 565
ወሎ	1671	968 384	968384 X 5		4 841 920	3 609 918
ሲዳሞ	1539	627 348	627348 X 5		3 136 740	3 750 579
ሐረርጌ	1455	582 393	582393 X 5		2 911 965	4 151 706
ጐጃም	3033	529 678	529678 X 5		2 648 930	3 244 882
ከፋ	1646	458 442	458442 X 5		2 292 210	2 450 369
ወለጋ	2264	449 797	449797 X 5		2 248 985	2 369 677
ጐንደር	2399	427 209	427209 X 5		2 136 045	2 905 362
ትግራይ	1268	381 471	381471 X 5		1 907 355	2 409 700
ጋምጐፋ	720	240 472	240472 X 5		1 202 360	1 248 034
አርሲ	1132	207 246	207246 X 5		1 036 230	1 612 233
ኢሉባቦር	984	193 449	193449 X 5		1 967 245	963 327
ባሌ	498	59 045	59045 X 5		295 225	1 006 491
ኤርትራ	12	5 000	5000 X 5		25 000	2 614 700
ድምር	25 001	1 075 588	7075588 X 5		35 377 940	
አዲስ አበባ	288	1 200 000	1 200 000		1 200 000	1 412 575
314 ከተሞች	969	2 623 244	2 623 244		2 623 244	—
አስተ	—	—	—		—	89 300
ጠ/ድምር	26 258		39 201 184		39 201 184	42 019 418

ምንጭ ፡ ላዲስ ጌ. ድሴቦ ፣ የምርትና የህዝብ ዘመቻ ፣ (1975) ።

ከነበረው የጽጥታ ችግር የተነሳ በኤርትራና በትግራይ በአመዛኙ በባሌና በሐረርጌ ደግሞ በከፊል በ1967 የመሬት አዋጅ መሠረት የገጠሩ ሕዝብ ለጊዜው በማህበራት ለመደራጀትና በሕዝብ ቁጥር ግምት ውስጥ ሊገባ ባለመቻሉ ነበር ። በ1969 የገበሬና የከተማ ማህበራት ስታቲስቲክስ መሠረት በተካሄደው የሕዝብ ግምት በአዲስ አበባና በ314 የክፍለ ሃገር ከተሞች የከተማ ሕዝብ ጠቅላላ ብዛት 3,832,244 ሲሆን በ1976 የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት

ደግሞ 4,742,8552 በመሆኑ ልዩነቱ በ920,000 የሚቆጠር ነው ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ነገር በ1966 አብዮቱ በፊነዳ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በዘመኑ አለበቂ መረጃና ምክንያት 22 ሚሊዮን 25 ሚሊዮን ፣ 27 ሚሊዮን ፣ 30 ሚሊዮን ፣ 32 ሚሊዮን ወዘተ... እየተባለ ይገመት ከነበረው አሀዝ በከፍተኛ ጠርዝ ይበልጥ እንደነበር ነው ።

በሌላ በኩል በ1969 የገበሬና የከተማ ማህበራ ትስታቲስቲክስ መረጃ 3,823,244 ፣ በ1976 የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት ደግሞ 4,742,855 ወይም ከጠቅላላ አገሪቱ ሕዝብ 11.3 በመቶ የከተማ ነዋሪ ነበር የሚለው አሀዝ በእርግጥ በአብዮቱ ፍንዳታ ወቅት በኢትዮጵያ የከተማ ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ እንደነበር ያሳያል ።[2] በተጨማሪም በአብዮቱ ዋዜማ በ1963 አካባቢ የዚህ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ አካል እንደሆኑ የሚቆጠሩ የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ፣ በአስተዳደርና በአገልግሎት ሥራ የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች ፣ የአገር መከላከያና የጸጥታ ዘርፍ አባሎችና የተማሪዎች ድምር ብዛት ከአንድ ሚሊዮን በታች እንደነበር ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 49 እና በሠንጠረዥ 50 አይተናል ።

በኢትዮጵያ በአብዮቱ ዋዜማ የከተማ ዕድገት በሚመለከት በሚነሳው ጥያቄ መታወቅ ያለበት መሠረታዊ ነገር የከተማ ስፋት ወይም የከተማ ሕዝብ ብዛት ሳይሆን ፣ የጥንቱ የአክሱማውያን ሜርካንታሊስት ሥልጣኔና ከተሞች ከፈረሱበት ጊዜ ጀምሮ የከተማና የዕደ ጥበብ ዕድገት ባልታየበት ጥንታዊ አገርና ፊውዳላዊ ሕብረተሰብ አዲስ የከተማ ሥርዓትና ባህል በዓይነት የመፈጠሩ ሁኔታ ነው ።[3]

በሰው ልጅ ሥራና ታሪክ ገጠርና ከተማ ሁለት ተቃራኒ የሥራና የሥርዓት ፈርጆች ናቸው ። ገጠር የፊውዳሊዝም ሥርዓት መሠረትና ምልክት የሆነውን ያህል ፣ ከተማ በባህርዩውና በተግባሩ ፀረፊውዳል ነው ። የከተማ ባህልና ሥርዓት ከፍተኛ የካፒታሊዝምና የሶሻሊዝም ሥርዓቶች መሠረትና ምልክት ነው ።

ከአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ እስከ አብዮቱ ድረስ በኢትዮጵያ በዕድገትና በተግባር በቅርብ ለተያያዙ ለዘመናዊ የንግድ ፣ የመገናኛና የከተማ ሥራዎች ዕድገትና መስፋፋት ግፊት የሰጡ ታሪካዊ ነገሮችና ሁኔታዎች ከውስጥ የአገሪቱ የማዕከላዊ መንግሥት ማጠናከርና ከውጭ ደግሞ የኢምፔሪያሊዝም ገጠመኝ ናቸው ።

በዚህ ረገድ ፣ ከ1870 እስከ 1906 ድረስ በምኒልክ አመራር በመሀል፣ በምዕራብ ፣ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ የተካሄደው ማዕከላዊ የአጼ መንግሥት አስተዳደር ማጠናከር እንቅስቃሴ የአዲስ አበባ መዲናን ጭምር በእነዚህ አካባቢዎች ላደጉ ታላላቅ ዘመናዊ ከተሞች መፈጠር ወሳኝ

መነሻ ሆነ።[4] እንዲሁም የአዲስ አበባ-ጂቡቲ የምድር ባቡር መገናኛ መስመር በሚያልፍባቸው አካባቢዎች የድሬዳዋና የናዝሬት ከተሞችን ጭምር ለብዙ ዘመናዊ የከተማ የንግድና የኢንዱስትሪ ሥራዎች ዕድገትና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አደረገ ።

የኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ገጠመኝ በሰሜን ለኤርትራ ከፍለ ሀገር ከተሞች ዕድገት ወሳኝ የውጭ መነሻ ሆነ ። እንዲሁም የፋሽዝም የወረራ ገጠመኝ በመላ አገሪቱ ውስጥ ለዘመናዊ የከተማ ፣ የንግድና የመገናኛ ሥራዎች የበለጠ ዕድገትና መስፋፋት አንድ ሌላ የውጭ ግፊት ሆነ ።[5] በመጨረሻም ከ1933 እስከ 1966 በፊውዶ ቡርኒ ዘመን የማዕከላዊ መንግሥት ቢሮክራሲያዊ ዕድገት እንዲሁም የንግድና የኢንዱስትሪ ከፍለ ኢኮኖሚዎች መስፋፋት በአብዮቱ ዋዜማ ለአጠቃላይ የከተማና የመገናኛ ሥራዎች ዕድገትና መስፋፋት ሌላ መንገድና ምክንያት ሆኑ ።

የአንድ ከተማ ዕድገት አንዱ ምልክት የነዋሪዎች ብዛት ነው ። በዚህ አኳያ የሚከተለው ሠንጠረዥ ከ1950 ጀምሮ እስከ 1966 ለናሙና በተመረጡ ዓመታት በአገሪቱ ዋና ዋና የአስተዳደርና የንግድ ከተሞች የታየውን የዕድገት መጠንና ስፋት ከከተማ ነዋሪዎች ብዛት አንጻር ያሳያል ።

ሠንጠረዥ 52

በአብዮቱ ዋዜማ በኢትዮጵያ ዋና ዋና የአስተዳደርና የንግድ ከተሞች የሕዝብ ብዛት

ከተማ	የከተማ ሕዝብ ብዛት ግምት ለናሙና በተመረጡ ዓመታት			
	በ1950	በ1958	በ1964	በ1966
አዲስ አበባ	400,000	489,400	912,090	1,120,550
አሥመራ	120,000	145,600	249,110	301,590
ድሬዳዋ	30,000	49,689	66,570	80,890
ጅማ	53,000	39,783	49,750	57,420
ሐረር	40,000	41,891	48,440	56,360
ጂማ	8,000	29,950	47,360	52,110
ናዝሬት	?	27,240	45,280	51,280
ጐንደር	14.000	30,102	38,600	44,350
መቀሌ)	?	22,630	30,780	36,210
ደብረ ዘይት	?	21,602	30,840	35,130
ደብረማርቆስ	8,000	21,093	30,260	32,360
ባህርዳር	—	12,206	26,480	26,490
አሰላ	?	13,600	19,390	23,530
ለቀምት	?	12,430	18,310	22,490
አዋሳ	—	5,460	16,790	17,650
ሻሸመኔ	?	7,676	13,840	16,410
ጐባ	?	7,154	13,500	14,710
አርባ ምንጭ	—	2,850	7.660	7,740
ድምር	1,643,000	1,180,356	1,665,940	2,097,260

ምንጭ I G. Lipsky, Ethiopia (1962); CSO. Statistical Abstace (1966, 1972, 1976).

እነዚህ ዋና ዋና የኢትዮጵያ ዘመናዊ የኤስተዳደር ፣ የንግድ ፣ የትም ርትና የኢንዱስትሪ ከተሞች በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የአገሪቱ ብሔ ራዊ አንድነት ፣ የማኅበራዊና የባህላዊ ዕድገት ፣ የመደቦች ልዩነትና ትግል መድረኮችና መሣሪያዎች እየሆኑ አደጉ ። በኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕብ ረተሰብና መንግሥት በእነዚህ የአንድነትና የትግል ከተሞች የአማርኛ ቋንቋ በገበያ ፣ በንግድ ፣ በመሥሪያ ቤትና በትምህርት የጋራ መገናኛ መ ሣሪያ እየሆነ አደገ ።

በ1977 በመቶኛው ክብረ በዓል ዋዜማ በተከታታይ የሬዲዮ ፕሮግ ራሞች ላይ ይህ ደራሲ በስፋት እንደአብራራው ፣ በአለፈው ምዕተ ዓመት የአዲስ አበባ መዲና ታሪክ የኢትዮጵያ ጥቅል ታሪክ ነው ። በዚህ ወቅት ማለትም በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ከዓ ለም አቀፍ የኢምፔሪያሊዝምና የፋሺዝም ሥርዓቶችና ኃይሎች ጋር ታሪ ካዊ ትግል አካሄዶ ብሔራዊ አንድነቱንና ነጻነቱን ከጥፋት ያዳነው በታላ ቁ የአዲስ አበባ መዲና ብሔራዊ የፖለቲካ አመራር ነው ።

በተጨማሪም ከ1950ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ የአዲስ አበባ መዲና የአፍሪካ አህጉራዊ ፀረ ኢምፔሪያሊዝም ትግል የሚካሄድበት ዓለም አቀፍ የአፍሪካ የፖለቲካ መዲና ሆነ ። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ዕድገት አኳያ ፣ በ1 950ዎቹና በ1960ዎቹ የአዲስ አበባ መዲና በኢኮኖሚ ፣ በንግድ በኢንዱ ስትሪ ፣ በትምህርትና በፖለቲካ መስኮችና ተግባራት ከፍተኛ የዕድገት ለውጥ መሻሻል አደረገ ። [6]

በፖለቲካ መስክ ዘውዳዊ የፊውዶ ቡርጎዋን ሥርዓት መሠረቱን ያጋለጠው የታኅሳስ 1953 አመጽ የተካሄደውም በአዲስ አበባ መዲና ነ በር ። የመዲናውና የአገሪቱ እምብርት የሆነው ዘመናዊው ታላቁ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትም የተሠራው በ1950ዎቹ ነበር ። ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት መነሻ የአገሪቱን የክፍለ ሀገር ከተሞች በአስተዳደርና በንግድ የሚ ያገናኙ አምስት አገር አቋራጭ የጮጃም ፣ የአምቦ — ወለጋ ፣ የጂማ ፣ የደ ሴ - አሥመራና የደብረዘይት መንገዶች [7] የተሠሩትና የተስፋፉት በ1950 ዎቹና በ1960ዎቹ ነበር ። በተጨማሪም የመዲናው ውስጣዊ የመንደርና የቀጣና መንገዶች በብዛትና በስፋት የተሠሩት በዚህ ወቅት እንደነበር ይታ ወሳል ። ቦሌ ዓለም አቀፍ የአይሮፕላን ማረፊያም የተሰራው በዚያ ጊዜ ነበር ።

በአጭሩ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የአዲስ አበባ መዲና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ሞተርና ጉማ የሚሽከረከርበት መንገድ መድረክ ሥፍራ ሆኖ አደገ ። በታኅሳስ 1953 አመጽ ግፊት በሚቀጥሉት 13 ዓመታት ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ የአብዮቱ ትምህርት ፣ ቲዎሪና ቅስቀሳ የሚ ካሄድበት የአገሪቱ ታላቅ የፖለቲካ ትግል መዲና ሆነ ። የትግሉም ብሔ ራዊ ሂደት ፣ ስፋት ፣ ይዘትና ውጤት በጥቅል እንደሚከተለው ይነበባል ።

የአርሶ አደሮችና የብሔረሰቦች አመጽ

የአንድ ሥርዓተ ማህበር የላዕላይ መዋቅርና የታህታይ መዋቅር ግለ ትም የማህበራዊ ድርጅትና የኢኮኖሚ መሠረት አለመጣጣም መሠረታዊ የምርት ግንኙነት ለውጥ እንገደሚያስከትል በሰው ልጅ ረጅም ታሪክ የተረጋገጠ ነገር ነው ።

በዚህ ነገር ከ1933 እስከ 1966 ድረስ የኢትዮጵያ የፊውዶ ቡርጎው ሥርዓት የኢኮኖሚ መሠረትና ማህበራዊ ድርጅት ፈጽሞ ሳይጣጣሙ ቀሩ። በአንድ በኩል ንጉሣዊ የገዥው መደብ በዘመናዊ የጦር የፖሊስ፣የስለላ ፣ የትምህርት ፣ የሕግና የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎችና ሥራዎች የተገነባ ላዕ ላይ መዋቅር በሌላ በኩል በአገር ውስጥ በገዥው መደብ አባሎ ችና በውጭ አገር ከበርቴዎች በጋራ የተያዙ የኢኮኖሚው የእርሻ ፣ የንግድ የገንዘብ ፣ የመገናኛ ፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችና ሥራዎች በ ሕብረትና በተናጠል በሕብረተሰቡ ላይ ታላቅ የሥርዓት ብዝበዛና ጭቆና እንደኣደረሱ ከዚህ በላይ በልዩ ልዩ መንገዶች አይተናል ።

በዚህ የጭቆና ሥርዓትና በንጉሣዊ የገዥው መደብ ላይ የሕብረተሰቡ የተለያዩ የአርሶ አደሩ ፣ የወዛደሩ ፣ የወታደሩ ፣ የቢሮ ሠራተኛው ፣ የኢን ቴሌጂንሲያውና የከተማ ቦዘኔው ክፍሎች በመሬት ፣ በቋንቋ ፣ በሃይማኖ ትና በባህል የተጨቆኑ ብሔረሰቦችና ማህበረሰቦች በየፊናቸው በተናጠል የአመጽ ትግል ጀመሩ ።

በዚህ ረገድ ፣ በሰሜኑ ደጋ የጮጃም ፣ የጐንደርና የትግራይ ሕዝ ቦች ብርቱ ተቃውሞ የመንግሥቱን የ1934 አዲስ ብሔራዊ የመሬት ይዞ ታና የግብር ሕግ በአዋጅ ቁጥር 8 መሠረት ተግባራዊ እንዳይሆን አደረገ ። በ1930ዎቹ በመንግሥቱ አዲስ የአስተዳደር ፖሊሲ ላይ በአመፅ የተነሱ የአደሬ ብሔረሰብ አባሎች በግዞት ተቀጡ ።

በመካከላቸው ለረጅም ጊዜ በነበረው የመሬት ችግር ምክንያት በጥር 1952 በአመጸኛ የጌዴኦ ጢሰኞችና በጉልተኞች መካከል በተካሄደው ጦርነት ከጢሰኛው ወገን በሰማንያ በጉልተኛው ወገን ደግሞ በሰባ በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ የሞት አደጋ እንደደረሰ ይታወሳል ።

ከ1955 እስከ 1962 ድረስ የባሌ ሕዝብ በመንግሥቱ የመሬትና የግ ብር ሕግ ላይ በአመጽ ትጥቅ ተነስቶ በመንግሥቱ ጦር ሠራዊት እንደ ተደበደበ ይታወሳል ። የ1960 የእርሻ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 255 የመ ንደር ይዞታ በሆነው መሬታቸው ላይ ተግባራዊ እንዳይሆን ለማድረግ በክፍለ አገር አስተዳደር ላይ በመሣሪያ አመጽ በመነሳታቸው የጮጃም ሰዎች እንዲሁም በጦር ሠራዊት ተደበደቡ ።

በ1934 ፣ በ1935 ፣ በ1952 ፣ በ1955 ፣ በ1960 የጐጃም ፣ የትግራይ ፣ የጌያሌና የባሌ የአመጽ እርምጃዎች በፊውዶ ቡርዣ ሥርዓትና የገዥው መደብ ላይ የአገሪቱ የአርሶ አደር መደብ አመጽ ምሳሌዎች ናቸው ። በተጨማሪም የጉልተኛ የገዥው መደብ የፖለቲካ ፣ የቋንቋ ፣ የባህልና የሃይማኖት ጭቆና በኤርትራ ፣ በኦጋዴን ፣ በመሀል አገር የፖለቲካና የብሔረሰብ ይዘት ያላቸውን የኤርትራ ፣ የኦጋዴንና የኦሮሞ የአመጽ እን ቅስቃሴዎችን በመቀስቀስ በተለይም በኤርትራና በኦጋዴን አገሪቱን ለረ ጅም ጊዜ የሚያደማውን የፖለቲካ ችግር ፈጠረ ።

በዚህ ረገድ ፣ በ1945 ፈደራላዊ ስምምነት ኤርትራ በኢትዮጵያ የአ ጼ ዘውድ ሥር በኢኮኖሚ ፣ በቋንቋ ፣ በትምህርትና በባህል የራሱ የው ስጥ አስተዳደር ሥልጣን እንደሚኖረው ፣ የትግርኛና የአረብኛ ቋንቋዎች ኦፊሴያላዊ ቋንቋዎቹ እንዲሆኑ መወሰኑ ይታወሳል ። ከአሥር ዓመታት በኋላ በ1955 የኤርትራ ፈደራላዊ የውስጥ አስተዳደር ፣ ሥልጣንና ኦፊ ሴላዊ ቋንቋዎቹ በአጼ ው መንግሥት ታገዱ ። ይህንን የፖሊሲ እርምጃ በ መቃወም በክፍለ ሀገሩ ራሱን ጀባሃ ማለትም " የኤርትራ አርነት ግም ባር " ብሎ የሰየመው የንዑስ ከበርቴ ቡድን ለረጅም ጊዜ በክፍለ ሀገሩ ለብዙ ሕይወትና ንብረት ጥፋት ምክንያት የሚሆነውን የመሣሪያ አመጽ ጀመረ ።

በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሶማሌ ማህበረሰብ አባሎችና የጐሳ መሪዎች ከምኒልክ ዘመነ መንግሥት በኋላ ፤

1. በዘውድ ሥልጣን ጥያቄ በልጅ ኢያሱ ሚካኤልና በደጃዝማች ተፈሪ መኳንን መካከል በተፈጠረው የፖለቲካ ትግል ፣ በወቅቱ በሌላ አካባቢዎች የአፋር ፣ የትግራይ ፣ የወሎና የጐጃም ሕዝቦ ችና የገዥ ቤተሰቦች እንደአደረጉት ሁሉ ፣ በአገሪቱ የመንግ ሥት ሥልጣን ጉዳይ ከልጅ ኢያሱ ጐን ተሰልፈው የፖለቲካ አቋም መውሰዳቸው ፣ [8]

2. በ1928—1933 የፋሺዝም ወረራ ጊዜ በታላቁ አርበኛ በደጃዝ ማች አመር ሰመተር መሪነት ለብሔራዊ ነጻነትና አንድነት በግምባር ደግቸውን እንደአደሰሱ ፤

3. በተለይም በ1928 አጋዴን ጦር ግምባር 2000 የሱማሌ ወታደ ሮችና የጦር አለቆች ከወራሪ ጠላት ጋር ሲዋጉ የመቁሰልና የሞት አደጋ እንደደረሰባቸው ፤ [9]

4. በ1933 የፋሺዝም ወራሪ በአፍሪካ ቀንድ ከተደመሰሰ በኋላ የሶማሌ ተወላጆች በዑመር አብራሂም መሪነት "የኢትዮጵያና

የሱማሌ አንድነት ማህበር " መሥርተው በናዳርን ማለትም የቀድሞ "ኢጣሊያ ሶማሊያላንድን " ከእናት አገር ኢትዮ ጵያ ጋር እንደጥንቱ ለማዋሀድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያደረጉት ትግል ፤ ሁሉ ሚታወስ ነው ። [10]

ነገር ግን በድህረ ጦርነት ለአገሪቱ የብሔረሰቦች አንድነት ኩልነትና የጋራ ዕድገት አሳብና ዓላማ ያልነበራቸው የኢትዮጵያ የፊውዶ ቡርዣ የገዥው መደብ ባለሥልጣኖች ፣ በኦጋዴን በማህበራዊ ዕድገት ኋላቀር ለሆ ነው ለሶማሌ ብሔረሰብ ዕድገትና ልማት ምንም እርምጃ ሳይወሰዱ ቀሩ ። በሌላ በኩል ከኦጋዴን ድምበር ባሻገር በ1952 የተፈጠረው የሶማሊያ መን ግሥት መሪዎች የኢትዮጵያ ሶማሌ ብሔረሰብን የኋላቀርነት ሁኔታ ምክ ንያት በማድረግ በአገሪቱ ብሔራዊ የግዛት አንድነት ላይ የቅስቀሳ ዘመቻ ከፈቱ ። በመሆኑም ከ1950ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ኦጋዴን የአገሪቱ አንድ የፖለቲካና የብሔረሰብ ችግር ግምባር ሆነ ።

በ1950ዎቹ የኢትዮጵያ ጨቋኙ የገዥው መደብ እንዲሁም የኦሮሞ ብ ሔረሰብን ቁጣና አመጽ በራሱ ላይ ቀሰቀሰ ። የ1950ዎቹ መጀመሪያ በአ ገሪቱ በየአካባቢው ሕዝቦች ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በፈቃዳቸው አዋጥተውና አቀናጅተው ፣ የጉራጌ መንገዶችንና የዓለምገና—ወላይታ መንገድን ጭምር ፣ ብዙ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን የጀመሩበት ወቅት እንደነበር ይታወሳል ። ለምሳሌ ከ1951 እስከ 1957 ድረስ በስድስት ዓመ ታት ጊዜ ውስጥ ከአገር ግዛት ሚኒስቴር አምሳ ስድስት ልዩ ልዩ የአካ ባቢ መሠረተ ልማት ማህበራት የሥራ ፈቃድ አውጥቷል ። [11]

ይህንን የወቅቱን ብሔራዊ ስሜትና እንቅስቃሴ በመከተል በ1955 ገደማ ሶስት ልዩ ልዩ የኦሮሞ ብሔረሰብ አባሎች ማለትም አቶ ኃይለማ ማርያም ገመዳ (1893—1964) ታዋቂ የሕግ ጠበቃ ፣ ደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ የመሬት ከበርቴ ፣ ኮሎኔል ዓለሙ ቅጤሳ የክብር ዘበኛ ጦር ባል ደረባ በየፊናቸው በቅደም ተከተል የቱላማ ፣ የሚታ—ሮባሌና የጅቡትና ሚጫ የአካባቢ ልማት ማህበራትን መሠረቱ ። በ1956 ሶስቱ ማህበ ራት በአቶ ኃይለ ማርያም ገመዳ አስተባባሪነት የሚጫና ቱላማ ማህበር በሚል ስም በአዲስ አበባ ተዋህዱ ። የሚጫና ቱለማ የልማት ማህበር ቅር ንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በወለጋ ፣ በከፋ ፣ በሲዳሞ ፤ በባሌ ፣ በአርሲ ፣ በሐ ረርጌ ፣ በሸዋ ፣ በወሎ ፣ በትግራይና በኤርትራ ከተሞች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከፍተው በየአካባቢው በአሮምኛ ቋንቋ የመሠረተ ትምህርትና የጤና ዘመቻ ጀመሩ ።

የሚጫና ቱለማ የልማት ማህበር እንደዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአ
ገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቶ የብሔረሰቡ አባሎች በሚገኙባቸው አካባቢ
ዎች ሁሉ በብሔረሰቡ ቋንቋ የመሠረተ ትምህርትና ጤና ፕሮግራሞችን
እንዲሁም የመንገድ ሥራዎችን በአገርና በወገን ስሜት ለማካሄድ ሲጀ
ምሩ የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንደሆነ በመቁ
ጠር የማህበሩን ህልውና ለማጥፋት ዘመቻ ከፈቱ ።

ይህ ከአገሪቱ መንግሥት የተሰነዘረው የቅጣት እርምጃ በፊት በማህ
በሩ ምሥረታና እንቅስቃሴ የፖለቲካ ዓላማ ያልነበራቸውን በአገርና በወ
ገን ስሜት ተነሳስተው የማህበሩ መሪዎችና አባሎች የሆኑ አሮሞዎችን
በኃይል አስቆጣቸው ። በዚህ ወቅትና ሁኔታ የመንግሥት የጦር ኃይሎች
ምክትል አዛዥ ብርጌደር ጀኔራል ታደሰ ብሩ የብሔረሰቡ አባል ከመን
ግሥት በልማት ማህበር ላይ የተደረገውን ተጽዕኖ በመቃወም አሁን
ማህበሩን በግልጽ የአሮሞ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መድረክና መሣሪያ
ለማድረግ በገሃድ ተነሳ ።

ብዙ የብሔረሰቡ አባሎች በተመሳሳይ መንፈስና ስሜት በአገር አቀ
ፍ ደረጃ ከጀኔራል ታደሰ ብሩ ጸረ መንግሥት እንቅስቃሴ ጐን መሰለፍ
ጀመሩ ። ነገር ግን በመጨረሻም በደምብ ያልተደራጁ የእንቅስቃሴ አባ
ሎች ቢጥቅምት 23 ቀን 1960 የዘውድ በዓል ቀን በአዲስ አበባ ቅዱስ ጊዮ
ርጊስ ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ " የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ "
በማለት የሥርዓቱን ቁንጮ የሆኑትን አጼ ኃይለ ሥላሴን በአደባባይ
ለማጥፋት ያልተሳካ ሙከራ ሲያደርጉ ሴራቸውን አስቀድመው በአ
ወቁ የስለላ ሰዎች በድንገት ተያዙ ።

ከዚህ በላይ በአጭርና በጥቅል የተገለጸው ከ1934 እስከ 1962 ድረስ
በልዩ ልዩ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ የጐጃም ፣ የትግራይ ፣
የአደሬ ፣ የጌዲኦ ፣ የባሌ ፣ የኤርትራ ፣ የሶማሌ ፣ የሚጫና ቱለማ የአመጽ
እንቅስቃሴዎች በፊውዶ ቡርኒ ንጉሣዊ የገዥ መደብ ላይ የተነሱት ከራሳ
ቸው ልዩ አካባቢያዊ ገጠመኝ አኳያ ነበር ። በመሆኑም ለሥርዓቱ ችግር
አንድ ብሔራዊ መፍትሔ አልነበራቸውም ። ሁሉም በየአካባቢያቸው በዘ
መናዊ ዕውቀትና መሣሪያዎች ቡተገነባው በሥርዓቱ ጠንካራ የላዕላይ
ድርጅት አንድ በአንድ ተደበደቡ ።

የወዛደሮች አመጽ ።

የወዛደሩ ብሔራዊ ዕድገትና ስርጭት

በሌላ በኩል ፣ ችግሩን ከአጠቃላይ ከሥርዓትና ከአገር አኳያ ያዩትና
የታገሉት በሙያ በሥራና በትምህርት መስኮች የተሰማሩ የወዛደሩ ፣
የጠሩ ፣ የተማሪና የአስተማሪ የአመጽ ኃይሎችና እንቅስቃሴዎች ፣ ነበሩ ።

በዚህ ረገድ በ1958 ከዚህ በላይ በሠንጠረዥ 47 ከቀረቡ ከአገሪቱ
248 የኢንዱስትሪ ማምረቻዎች በክፍለ ሀገር ስርጭት 118 በአዲስ አበባ፣
91 በአሥመራ ፣ 18 በድሬዳዋ-ሐረር ፣ 7 በወንጂ—ናዝሬት ማለትም ከአ
ገሪቱ ጠቅላላ 248 የኢንዱስትሪ ድርጅቶች 231 ወይም 93.1 በመቶ በአ
ራት በተወሰኑ የልማት አካባቢዎች ነበሩ ። በመሆኑም ፣ ለሙያ ድርጅት
ብሎም ለተሻሻለ የሥራና የኑሮ ሁኔታ የወዛደሩ ትግል ከባለሀብቶችና ከአ
ገሪቱ የገዥው መደብ ጋር የሚጀምረው በእነዚህ ቦተጠቀሱት አራት
የኢንዱስትሪ ቀጣናዎች እንደሚሆን ግልጽ ነው ።

በመሆኑም የፍራንኮ—ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩባንያ ወዛደሮች
በድሬደዋ ከተማ ለደሞዝ ጭማሪ በ1938 ለሶስት ወራት በ1939 ደግሞ
ለሁለት ወራት ሥራ በማቆም በፊውዶ ቡርኒ ዘመን አዲስ የወዛደር
ትግል ምዕራፍ ከፈቱ ። በ1940 በእንግሊዝ የቅኝ ግዛት ሥር የኤርትራ
ወዛደሮች በሙያ ማህበር ተደራጁ ። በጥቅምት 1950 የኤርትራ ወዛደሮች
የወጠኑት የሥራ ማቆም አድማ በፖሊስ ግስጠንቀቂያ ታገደ ። በተጨ
ማሪ የኤርትራ ብሔራዊ ሽንጉ ያረቀቀው የወዛደር ሕግ አዋጅ ታውጆ
ሕግ እንዳይሆን በኤርትራ በንጉሡ እንደራሴ ተከለከለ ። [12]

በሌላ በኩል ከ1950 እስከ 1955 ድረስ የአገሪቱ የኢንዱስትሪ ሠራ
ተኞች በሙያ ማህበር ለመደራጀት ከባለፋብሪካዎችና ከፊውዶ ቡርኒ
መንግሥት ጋር ታላቅ ብሔራዊ ትግል አካሄዱ ። በዚህ ወቅት በአዲስ አበ
ባ የቃጫ ፋብሪካ ወዛደር አቶ አበራ ገሙ የክልሉን ወዛደሮች በማስተባ
በርና በማደራጀት ተግባር ከባለፋብሪካዎችና ከመንግሥት ባለሥልጣኖች
ጋር ታላቅ ትግል በማካሄድ ለወዛደሩ ትግልና ድል ከፍተኛ አስተዋጽኦ
እንደ አደረጉ ታውቋል ።

የወዛደሩ የትግል ስልትና ድል

በ1953—1958 በትምህርትና በሥራ አጋጣሚ በአካባቢው በመገ
ኘት ፣ ይህ ደራሲ የወንጂ ሠራተኞች ከኩባንያውና ከመንግሥት ጋር ያካ
ሄዱትን ታላቅ የትግል ታክቲክና ስትራቴጂ በቅርብ ተከታትሎአል ።

በወንጂ የወዛደሮችን የሙያ ድርጅት ትግል በአቶ አብርሃም መኩንን የፋብሪካ ወዛደር እስተባባሪነት የጀመሩት ከአራት የማይበልጡ የፋብሪካ ወዛደሮች ነበሩ ። በታላቅ ትግል በሙያ ማህበር የመደራጀት መብት እስ ኪያገኙ ድረስ ፣ በዕድርና በለቅሶ ቦታዎች በይፋ ካልሆነ በስተቀር ፣ ወዛ ደሮች በአንድነት ተገኝተው መሰባሰብና መነጋገር በወንጂ ስኳር ኩባንያ የውስጥ ደንብና አሠራር ፈጽሞ ክልክል ነበር ። ኩባንያው ሠራተኞቹን በምንም ጊዜ በሆነ ሁሉ ምክንያት አለምንም ካሳ ከሥራ ለማባረር የባለቤ ትነት መብትና ሥልጣን ነበረው ። በወንጂ በዚህ ዓይነት ሥርዓትና አሠ ራር ሠራተኞችን በመብትና በጥቅም ጉዳይ የማደራጀት ተግባር ቀላል ት ግል አልነበረም ።

ይህ ደራሲ በወቅቱ እንደተነገረው ፣ ይህን ከፍጹም ባርነት የማይ ሻለውን የወንጂ ሠራተኞችን ዘረፋና ብዝበዛ ከቅርብ ያየ አንድ የፋብሪ ካው የውጭ አገር ሠራተኛ አ ትዮጵያዊ ሠራተኞች እንደዚህ በኩባንያው የሚበዘበዙት በሙያ ማህበር ያልተደራጁ በመሆናቸው ነው በማለት በጥ ቂት ሠራተኞች ዘንድ የቅስቀሳ አሳብ ይሰነዘራል ።

በዚህ በተባለው ቅስቀሳ ይሁን በሌላ ገጠመኝ ፣ ወዛደር አብርሃም መ ኩንንና ጓደኞቹ ከሥራቸው ቦታ ሳይንቀሳቀሱና ሳይለዩ የኩባንያው አስ ተዳደር ሆነ የፋብሪካ ሠራተኞች በግልጽ ሊያውቁ በማይችሉበት ዘዴና አሠራር የወንጂ ሠራተኞችን የድርጅት አደማ ጀመሩ ። የአድማው ማዕከ ልና አመራር በትክክል ሳይታወቅ እንቅስቃሴው በፋብሪካ ሠራተኞች መካ ከል መሰራጨት ጀመረ ። ኩባንያው በበኩሉ እንቅስቃሴዉን ለማፈን ከፍተኛ ጥረት አደረገ ። የፋብሪካ አስተዳደር ሠራተኞችንና የማሳ ፊልድአሲስታንቶችን የእንቅስቃሴውን አመራርና ሂደት እንዲያጠፉት አደራጀ ።

እንቅስቃሴውን የጀመሩትና የሚመሩት የፋብሪካ ጥቂት ወዛደሮች በሥራ ቦታና ከሥራም ጊዜ ውጭ በፋብሪካ ክልል በየትም ሥፍራ በምንም ጊዜ በአንድነት ተሰብስበው ለመነጋገር ስለማይችሉ አንድ ህቡዕ የሆነ የአድማ መድረክ ፈጠሩ ።

በዘመኑ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ ጉን ለፋብሪካው ማገዶ የሚያገለግል እንጨት በብዙ አራት ማዕዘናት ቦታዎች ላይ ተከምሮ ይታይ እንደነበር ይታወሳል ። እንጨት በአራት ማዕዘናት የተከመረበት ቦታ ሰፊ ሆኖ የክ ምሩ ውስጥ ባዶ ሥፍራ ነበር ። በአራት ማዕዘናት ቦታ እንጨቱ ከታች እስከ ላይ ድረስ የሚከመረው በመሰላል ደረጃ አማካይነት ነበር ። በመ

ሰላል ደረጃ ወጥቶና ወርዶ በክምሩ ክብ ምድር የሚሆን ሰው ወደ ላይ እንጂ ወደ ጉን ለማየት አይችልም ። በክምሩ ክብ ምድር የሰው ድምጽ ወደ ውጭ ወጥቶ ቢሰማም ከየት አቅጣጫ እንደሚመጣ በትክክል አይ ታወቅም ነበር ።

በመሆኑም የወንጂ የወዛደር ድርጅት እንቅስቃሴ ጀግሪዎችና መሪ ዎች የኩባንያው የአገር ልጅ ሰላዮችና ምንደኞች በማያገኙአቸው ጊዜ ወደ እነዚህ የማገዶ እንጨት "ጉድጓዶች" በመሰላል ደረጃ እየወጡና እየወረዱ ተሰብስበው የትግል ዕቅድና ታክቲክ በመቀየስ የድርጅት ሥራ በታላቅ ትጋትና ብርታት ይመሩ እንደነበር በወቅቱ የጉዳዩን ውስጠ ምስጢር የሚያውቁ ሠራተኞች ለደራሲው ገልጸውለታል ።

የእንቅስቃሴው አስተባባሪዎች እንደዚህ በህቡዕ መንገድና አሠራር የወንጂ የስኳር ፋብሪካ ሠራተኞችን ከዳር እስከ ዳር በድርጅት ጥያቄ ወደ አንድ የጋራ ግንዛቤና ስምምነት ከአደረሱ በኋላ በ1954 የሙያ ድርጅት ጥያቄያቸውና መብታቸው በኩባንያውና በመንግሥቱ ዘንድ የማይከበር ከሆነ በወንጂ ስኳር ፋብሪካ አጠገብ በሽቦ አጥር ግቢ ተገልለው የሚኖሩ ትን የኩባንያውን የውጭ አገር ሠራተኞች አንድ ሳይተርፍ እንደሚገድሉ አቸው ፋብሪካንም እንደሚያቃጥሉት በይፋ ማስጠንቀቅ ጀመሩ ። በዚህ ወቅት ማለትም በ1954 መጀመሪያ ለተወሰነ ጊዜ የወንጂ ስኳር ፋብሪካና የውጭ አገር ሠራተኞች የሽቦ ገቢ አመጸኛ ወዛደሮች እንዳይደርሱ ከናዝ ሬት ከተማ ታንከኛ ጦር ሄዶ ሲጠብቅ ደራሲው በዓይኑ አይተዋል ።

በዚህ በወዛደሩ የአመጽ ግፊት የፊውዶ ቡርኒው መንግሥት በወዛደሩና በአሰሪ መካከል የሚኖረውን የሥራ ግንኙነት የሚገዛውን የሠራተኛ ሕግ በ1954 በአዋጅ አወጣ።በአዋጁ የወዛደሩ በሙያ ማህበር የመደራጀት መብቱ ታወቀ።በመሆኑም የአገሪቱ በየኢንዱስትሪው የተደራጁ 28 የሙያ ማህበራት በተወካዮቻቸው አማካይነት በ1955 በብሔራዊ ደረጃ የኢት ዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማህበር (ኢሠአማ) መሠረቱ ። አቶ አበራ ገሙ የማህበሩ የክብር ፕሬዚዳንት አቶ አብርሃም መኩንን ደግሞ የማህበሩ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ ። የአገሪቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በትግል ተወ ልዶ ያደገው ወጣቱ የወዛደር መደብ ታሪካዊ ድል ተቀዳጀ ። አሠሪው የሠራተኛው ጌታ መሆኑ ቀረ ።

በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ከ1955 እስከ 1966 ድረስ የኢሠአማ ቅር ንጫፍ ማህበራትና የአባላት ዕድገትና ብዛት ይታያል ።

ሠንጠረዥ 53

በ1955 — 1966 የኢትዮጵያ ሠራተኞች እንድነት ማህበር የቅርንጫፍ ማህበራትና አባላት

ተራ ቁ.	ዓመት	የኢሠአማ ቅርንጫፍ ማህበራት ብዛት	የኢሠአማ አባላት ብዛት
1	1955	28	18,680
2	1956	34	20,127
3	1957	43	24,711
4	1958	53	26,077
5	1959	105	41,307
6	1960	112	42,307
7	1761	118	43,590
8	1962	131	45,495
9	1963	146	47,012
10	1964	159	48,590
11	1965	175	51,346
12	1966	229	69,161

ምንጭ ፡ ኤክስፖ 1971 (አዲስ አበባ) ።

የወታደሮች አመጽ

በ1966 የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ማዕከላዊ ድርጅትና አመራር ሳይኖረው በፊውዶ ቡርኂው ጨቋኝ ሥርዓትና የግዥ መደብ ላይ በየአካባቢው የአመጽ እንቅስቃሴ አካሄደ ። ምናልባትም በዘመኑ የሕብረተሰቡን የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና ከሁሉ በላይ የቀሰቀሰው በጦር ፡ በጸጥታና በፖሊስ ሙኩንኖች ተሞክሮ የከሸፈው የታኅሳስ 1953 አመጽ ነው ።

የዚህ የ1953 አመጽ የቅርብ መነሻ ከጃፓናዊ አማካሪዎች ቡድን በ1949 መጨረሻ በቀረበው የፖለቲካ ትምህርትና የድርጅት ፕላን መሠረት በ1950—1953 በፊውዶ ቡርኂው የግዥ መደብ ውስጥ በፊውዳል የሹማንቶች አንጃና ዘመናዊ ትምህርት በተማሩ ወጣት ባለሥልጣኖች መካከል የተፈጠረው አንጃዊ የሥልጣን ትግል እንደነበር በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ ለማገናዘብ ተሞክሮአል ።

በኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁና በአቶ ገርማሜ ንዋይ ተዘጋጅቶ በታኅሳስ 5 ቀን 1953 ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሬዲዮ ፕሮግራም በአልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ንባብ እንዲሰማ የተደረገው አዋጅ ፤

1. የኢትዮጵያን ማህበራዊና ብሔራዊ የዕድገት እርምጃ ጥቂት ራስ ወዳድ ግለሰቦች ወደ ኋላ እንደአስቀሩት ፡
2. በቅርቡ የተነሱ የአፍሪካ አገሮችም በብሔራዊ የዕድገት ጐዳና ጥንታዊቱን ኢትዮጵያ ቀድመው ወደፊት በመሄድ ላይ እንደሆኑ ፡

3. ይህንን የአገሪቱን ኋላቀር ብሔራዊ የዕድገት ሁኔታና ሂደት በመቃወም በወቅቱ አርሶአደሮች ፡ ነጋዴዎች ፡ ሠራተኞች ፡ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት አባሎች ፡ የተማሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን በአመጽ እንቅስቃሴ መነሳታቸውን ፤ ግልጽ አሁን ይህንን የሕዝቡን የለውጥና የዕድገት ፍላጐት የሚያሟላ አዲስ መንግሥት እንደተመሠረተ አስታወቀ ። [13]

በታኅሳስ 5 ቀን የአመጹ አዋጅ በሬዲዮ ከተላለፈ በኋላ የአመጹ መሪ ብርጌዴር ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የክብር ዘበኛ ክፍለ ጦር አዛዥ በክፍለ ጦሩ ዋና መምሪያ ለኮሌጅ ተማሪ ተወካዮች የአመጹን ዓላማና ተግባር አስመልክቶ በአደረገው ንግግር በመጨረሻ ደቂቃ አንዳንድ ሰዎች ወደ ኋላ በማፈግፈጋቸው የተወሰደው የአመጽ እርምጃ መሳካት ያጠራጥራል ቢሆንም " የለኮስ ነው እሳት ራሱ አይጠፋም " ማለቱ ታውቋል ። [14]

ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ እንደፈራውም ፡ በጦር ኃይሎች ኤታማጆር ሹም የተመራ የጦርና የፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖች አንጃ በታንክና በጦር አይሮፕላን በአዲስ አበባ ከተማ በአገሪቱ መለዮ ለባሽ ውስጥ የመጀመሪያውን የእርስ በርስ ጦርነት በመክፈት አመጹን ደመሰሰው ። በአዲስ አበባ የአሜሪካ ወታደራዊ ሚሽን በብርጌዴር ጀኔራል ዊስተር ደጋብሬ መሪነት ቀልባሹን እንጂ በአመጸኞቹ ላይ በ ተግባር ደገፉ ። [15] በተጨማሪም የአመጹ አመራር በአገሪቱ የቤተክርስቲያን መሪ ስም ከአይሮፕላን በተበተነ ጽሑፍ ተወገዘ ።

በአገር ውስጥና በውጭ አገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅና ጠላት ማን እንደሆነ በብሔራዊ ፈተና ሰዓት በተግባር ያሳየው የ1953 አመጽ በተለይ በአገሪቱ ወታደሮችና ተማሪዎች ዘንድ ታላቅ የአመለካከትና የፖለቲካ ግንዛቤ ለውጥ በማስከተል በአብዮቱ ዋዜማ ሕብረተሰቡን ለበለጠ የአመጽ እንቅስቃሴ አነሳሳው ።

ከአመጹ እስከ አብዮቱ ድረስ የወታደሮችና የተማሪዎች ግልጽና ስውር የአመጽ እንቅስቃሴዎች ፡ እንደ አርሶ አደሩ ፡ እንደወዛደሩና እንደ የብሔረሰቦቹ የአመጽ ሥራዎች ሁሉ ፡ የፊውዶ ቡርኂ ሥርዓት ጭቆና ውጤት ነበር ።

አርሶ አደሩ ለመሬት ባለቤቱ ወዛደሩም ለባለፋብሪካው የግል አሽከርና አገልጋይ እንደነበር ሁሉ ፡ የአገሪቱ ዘመናዊ የጦር ሠራዊቱ በ1936 ከተመሠረተበት እስከ 1953 አመጽ ድረስ የኢትዮጵያ ተራ ወታደር በተለይ የመንግሥትና የመኮንኑ አሽከር ነበር ለማለት ይቻላል ።

በ1936 የጦር ሠራዊት ምስረታ አዋጅ መሠረት ፥ የተራ ወታደር የወር ደመወዝ አሥር ብር ፥ የወር ቀለብ ሂሳብ ደግሞ ስምንት ብር ማለትም የወታደሩ ጠቅላላ የወር አገልግሎት ዋጋ አሥራ ስምንት ብር ነበር ። [16] ከሥነ ሥርዓትና ግዴታ አኳያ ግን የጥፋት ተግባር በሚፈጽሙ የጦር ሠራዊት አባሎች ላይ የጦር ፍርድ ቤት የሚወስንባቸው የቅጣት ዓይነቶች ከዚህ የሚከተሉትን ይጨምራሉ ። [17] በሕጉ ቃል ፤

1. ከሀያ ዓመት የማይበልጥ የእሥራት ቅጣት ፥
2. ከአገልግሎት የማስወጣት የማባረር ቅጣት ፥
3. ምክትል ሹም የሆነ እንደሆነ ወደ ዝቅተኛ ደረጃ ወይም ወደ ተራ ወታደርነት ማውረድ ፤
4. በአካል ቅጣት የሆነ እንደሆነ ከሀያ አምስት የማይበልጥ ግርፋት ፤
5. ከደሞዝ ማገድ ፤ በገንዘብ መቅጣት ፥ ደሞዝ መቁረጥ ፥
6. በብርቱ መገሠጽ ወይም ፥ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ቅጣቶች ማናቸውንም አጣምሮ መቅጣት ፤

በጥፋተኛ ወታደሮች ላይ አዛዥ መኮንን ደግሞ በሥልጣኑ

1. አጥፊውን ከአርባ ሁለት ቀን በማይበልጥ እሥራት እንዲታሠር ያደርጋል ።
2. አጥፊውን ከጦር ሠራዊት ውስጥ እንዲባረር ያደርጋል ።
3. ከአጥፊው ደሞዝ ላይ ከሀያ አንድ ቀን ሂሳብ የማይበልጥ እንዲቆረጥ ያደርጋል ።
4. አጥፊው ላጠፋው ገንዘብ ወይም ላደረገው ጉዳት ከደሞዙ እንዲቆረጥ ያደርጋል ።
5. አጥፊው ከ28 ቀን በማይበልጥ እሥራት እንዲቀጣ ያደርጋል ።
6. አንስተኛ በደሎች ሲሆኑ ጥፋተኛው ትርፍ የቅጣት ሥራ እንዲሠራ ያደርጋል ።
7. ከሀያ በማይበልጥ የግርፋት ቅጣት ይቀጣል ።[18]

ባጭሩ ከ1936 እስከ 1953 አመጽ ድረስ በኢትዮጵያ የተራ ወታደር የኑሮ ፥ የሥራና የሥነ ሥርዓት ሁኔታ በዓይነት አልተለወጠም ። የአመጹ አመራር ከመሳለሚያቹ በአንዱ የወታደሩን ይህንን የድህነትና የረሀብ ችግር ገልጾ ፥ አዲሱ መንግሥት የተራ ወታደርና የአሥር አለቃ የመነሻ ደሞዝ ሀያ ብር ፥ ከአምሳ አለቃ እስከ ሻለቃ ደረጃ ለሚገኙ ደግሞ የአምሳ ብር የደምዝ ጭማሪ መወሰኑን አስታወቀ ። [19]

የ1953 አመጽ በአንድ በኩል በንጉሣዊ የግዥ መደብ ላይ ታላቅ የወታደር ፍርሃት አሳደረበት ። በሌላ በኩል በወታደሩ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የአመለካከትና የፖለቲካ ግንዛቤ ለውጥ አስከተለ ። በመሆኑ ከ1953 አመጽ በኋላ ወታደሮች የፊውዶ ቡርጎዋውን መንግሥትና ምርጥና የተደላደለ ኑሮ የሚኖሩ ከፍተኛ መኰንኖችና አዛዦችን በአመጽ እየተነሱ የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄያቸውን ማስከበር ጀመሩ ። በዚህ ሁኔታ ወታደሮችና የጦሩ የበታች ሹማምንቶች በመጋቢት 1953 እና በነሐሴ 1956 ለመንግሥቱ የደሞዝ ጥያቄ አቅርበው በሁለቱም ጊዜ ጭማሪ አገኙ ። [20]

በአጭሩ ከ1953 አመጽ በኋላ የኢትዮጵያ ወታደሮችና የጦሩ የበታች ሹማምንቶች በፊውዶ ቡርጂው መንግሥትና በከፍተኛ የጦር መኮንኖቹ ላይ መብታቸውንና ጥቅማቸውን የሚያስከብሩት በታማኝ አሽከርነት ሳይሆን በትጥቅ አመጽ እንደሆነ በልምድ እየተማሩ መጡ ።

ምዕራፍ 2 አብዮታዊ እንቅስቃሴ

የተማሪዎች አመጽ

የተማሪዎች አብዮታዊ ትምህርት

ከ1953 አመጽ እስከ 1966 አብዮት ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ የአመጽ እንቅስቃሴ ከፊውዶ ቡርጂ መንግሥት የትምህርት ዓላማና ተግባር ጋር በቅርብ የተያያዘ ከስተት ነበር ። በዘመኑ በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ዘንድ ትምህርት የኢኮኖሚና የባህል ግምባታ መሣሪያ እንደሆነ ግንዛቤ አልነበረም። በ1901 የዎኂልክ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አብዮቱ ድረስ የኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ዋና ዓላማና ተግባር ለመንግሥት ሥራ በውጭ ቋንቋና ባህል የሰለጠኑ ወጣት ባለሥልጣኖችንና ሠራተኞችን ማሰልጠን ነበር ። በዚህ አኳያ ፥ ልጅ ኢያሱ ሚካኤልን ፥ ልጅ ብሩ ወልደ ገብርኤልን ፥ ልጅ ጌታቸው አባተን ፥ ልጅ እምሩ ኃይለ ሥላሴን፥ደጃዝማች ተሬሬ መኩንንን ጭምር የዎኂልክ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ተማሪዎች የአገሪቱ የወደፊት መሪዎችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የሚሆኑ የመሰናንትና የመኳንንት ልጆች እንደነበሩ ይታወሳል ። [1]

ከፋሽስቶች ወረራ በፊት በውጭ አገር ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ የኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ብዛት በ250 የሚቆጠር ነበር።ከእነዚህም ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ በጠላት ወረራ ዘመን እንደሞቱ ፥ 55 በድህረ ጦርነት የመንግሥት የመጀመሪያ የተማሩ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ለመሆን እንደበቁ በአንድ ጥናት ተመልክቷል ። [2] በድህረ

ጦርነት መጀመሪያ አሥር ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት በውጭ አገርና በአገር ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞችን ለማሰልጠን ታላቅ ጥረት እንደ አደረገ ታውቋል ። በዚህም ጥረት በ1934 የትምህርት ሚኒስቴር ተመሠረተ ። በ1943 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተከፈተ ። በ1954 ወደ ውጭ አገር ተልከው የተማሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሥራት ጀመሩ ።

በሌላ በኩል ከ1933 ጀምሮ በ1950ዎቹ መባቻ እስከ አጼ ዉ ልዩ ካቢኔ ምሥረታና የ1953 አመጽ ድረስ ከአጼ ሥር የመንግሥትን የበላይ ሥልጣን ይዘው አገሪቱን ከገዙ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች መካከል ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢትወደድ መኩንን እንዳለካቸው ራስ አበበ አረጋይ ፣ ልዑል ራስ ካሳ ኃይሉ ፣ አቶ መ ሮ ንን ሀብተወልድ ጨምሮ ዘመናዊ ትምህርት ያልተማሩ በጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና እምነት ጠንካራ መሠረት የነበራቸው ጥቂት ግለ ሰቦች እንደነበሩ ይታወሳል ። [3]

በ1953 አመጽ ከእነዚህ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ብዙዎቹ እስኪገ ደሉ ድረስ ዘመናዊ ትምህርት በተማሩ ወጣት የመንግሥት ባለሥልጣኖ ችና በተጠቀሱት የዱሮ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች መካከል ታላቅ የግንዛቤ ፣ የሥልጣንና የጥቅም ግጭት ተፈጠረ ። ከአመጹ በኋላ በ1950ዎቹ በ19 60ዎቹ በውጭ አገርና በአገር ውስጥ በአመዛኙ ዘመናዊ የቀለምና የአስተዳ ደር ትምህርት የተማሩ ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ እየበዙ ሄዱ ። በአንጻሩ ደግሞ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት በሌለበት ፊውዶ ቡርኒ ሥርዓት የመንግሥቱ የቅጥር ሥራ ችሎታ ከዓመት ወደ ዓመት እያነሰ በመሄድ በትምህርት ዓለም በተሰማሩ ወጣት ዜጎች ዘንድ ታላቅ ስጋትና ጭንቀት በማሳደር በሥርዓቱ ላይ ለተማሪዎች የአመጽ እንቅስቃሴ አስተ ዋጽኦ አደረገ ።

ከአመጹ እስከ አብዮቱ ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ለከፍተኛ ትም ህርት በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተሰማሩባቸው በሶስት የዓለም አካ ባቢዎች ራሳቸውን ፤

1. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር (አአዩተማ) ፣
2. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በሰሜን አሜሪካ (ኢተማሰአ) ፣
3. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በአውሮፓ (ኢተማአ) ፣
4. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ማህበር (ኢተዓአማ) በማለት አደራጁ ።

ከድርጅትና ከፖለቲካ ትጥቅ አንጻር ደግሞ ከኢተዓአማ ቅርንጫፍ አህጉራዊ ማህበራት አአዩተማ የታገል ፣ ኢተማሰአ የቻሌንጅ ፣ ኢተማአ ደግሞ የታጠቅና የትግላችን መጽሔቶችንና የቲዎሪ ልሳኖችን መሠረቱ ።

በእነዚህና በሌላም የፖለቲካ ትግል መሣሪያዎች አማካይነት ከ1953 እስከ 1958 ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪ ማህበራት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚከተሉ መሠረታዊ የፖለቲካ አቋሞችን ወሰዱ ።

1. የኢተዓአማ ማህበራት ፣ አባላትና መጽሔቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአጋጠመው የሥርዓት ችግር መፍትሔው የፖለቲካን ጥገና ሳይሆን አብዮታዊ የሥርዓት ለውጥ እንደሆነ የፖለቲካ አቋም ወሰዱ ።
2. መሬት ላራሹ የሚባለውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄ አስተጋቡ ።
3. አምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና የመ ደብ ጠላቶች እንደሆኑ የፖለቲካና የትግል አቋም ወሰዱ ።

የተማሪዎች እንቅስቃሴና የኤርትራ ተገንጣዮች

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ፣ የአአዩተማ ፣ የኢተማሰአ ፣ የኢተማአና የኢተዓአማ ስብሰባዎችና ልሳኖች የተጠቀሱ ፖለቲካዊ አብዮታዊና ርዕዮተዓለማዊ መፈክሮችና መግለጫዎች ከተግባርና ከድርጅት አኳያ ግለትም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታና ሂደት አኳያ ምን ግለት እንደሆኑ የአገሪቱን የፖለቲካ ኢኮኖሚ መርምረውና አገናዝበው የተረዱ ትና የገለጹት ተግባራዊ የትምህርትና የዕውቀት ግንዛቤ ግን የተወሰነ ነበር ።

ይህ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ተግባራዊና ትምህርታዊ ድክመት በኋላ የአአዩተማ ፣ የኢተማሰአ ፣ የኢተማአና የኢተዓአማ አካላት ፣ አባላትና ልሳኖች ከ1961 እስከ 1966 ድረስ ሁለት ተጨባጭ የብሔረሰብና የድር ጅት ችግሮችን ለማንሳት ሲጀምሩ በገሃድ መከሰት ጀመረ ።

በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ የአመጽ እንቅስቃሴ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ያሳደረው ራሱን ጀበሃ ማለትም " የአርነት ግምባር " በማለት ሰይሞ ከታህሳስ 1953 አመፅ በኋላ በኢትዮጵያ ፊውዶ ቡርኒ መንግ ሥት ላይ በትጥቅ የተነሳው የኤርትራ ተገንጣይ ቡድን ነበር ።

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች በዘመኑ በአገር ውስጥና በውጭ ዓለም ለመጣል በሚታገሉት አስከፊው የፊውዶ ቡርዣው ሥር ዓት ላይ አስቀድሞ የመሣሪያ ትግል በመከፈቱ ጀበሃን ተራማጅ

ቡድን እንደነበር በመገመት ከ1954 እስከ 1961 ድረስ የአንድነት ድጋፍ ይሰጡት ነበር ።

ነገር ግን ታሪክና ጊዜ በኋላ እንዳሳየው ፣ የጀበሃ ዓላማ ፀረኢትዮጵያ ከሆኑ የአካባቢ አገሮች የመሣሪያና ገንዘብ እርዳታ አግኝቶ የኤርትራን ክፍለ ሀገር ከኢትዮጵያ ቆርጦ የአረብ ዓለም አካል ማድረግ ነበር ። ከ1954 እስከ 1961 ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ " የአዞ ማህበር " በሚል ሕቡዕ ድርጅት በአእዩተማ አመራር ውስጥ ጀበሃን በስውር አመራር የሚደግፉ ግለሰቦች ነበሩ ።

በሌላ በኩል ይህን የጀበሃን እኩይ የመገንጠል ዓላማና ተግባር ለረጅም ጊዜ ከመረመረ በኋላ በነሐሴ 1961 በፊላደልፊያ ከተማ በተካሄደው በአሥራ ሰባተኛው ጉባኤ ኢተማሰአ የግምባሩ አመራር የኤርትራን ሠርቶ አደር ሕዝብ የማይወክል በኢምፔሪያሊዝምና በፊውዳሊዝም የጋራ ጠላቶቻቸው ላይ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችንና ሠርቶ አደር ሕዝብን መደባዊ የትግል አንድነት የሚያዳክም አድሃሪ ኃይል ነው በማለት በይፋ አወገዘ [4] ።

በአንጻሩ ግን በአገር ውስጥ በአስጨናቂው የፊውዶ ቡርጂው መንግሥት ላይ በሚጠቀሙበት "አዞ" በተባለው ስውር ድርጅታዊ አሠራር በአእዩተማ ውስጥ የጀበሃ ደጋፊዎች የነበሩት ተማሪዎች በነሐሴ 1961 ኢተማሰአ በፊላደልፊያ ጉባኤ ግምባሩን በሚመለከት የወሰደውን አቋም " የብሔር ትምክህተኝነት " መግለጫ ነው በማለት አወገዙ ። በአጸፋው " የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ " በሚል ርዕስ በህዳር 7 ቀን 1962 በማህበሩ መጽሔት ታግል ቅጽ 5 ቁጥር 2 አብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች በማህበራዊ የዕድገት ደረጃቸው ብሔሮች ስለሆኑ ከጨቋኝ ሥርዓትና መንግሥት የመገንጠል መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት በራሳቸው ላይ የመንግሥቱን የታህሳስ 1962 ቁጣና ቅጣት ቀሰቀሱ ።

" የብሔረሰቦች ጥያቄ በኢትዮጵያ " የተባለው ጽሑፍ በታግል መጽሔት ከወጣበት ከህዳር 7 ቀን 1962 ጀምሮ በታህሳስ ሦስተኛው ሣምንት በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ላይ የፖሊስ እልቂት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የፊውዶ ቡርጂው መንግሥት በሕብረተሰቡ ዘንድ በተማሪዎች ላይ የማስሚዲያ ዘመቻ ከፈተ ። ለምሳሌ በህዳር 19 ቀን 1962 " ከመጠኑ አለፈ " በሚል ርዕስ የመንግሥቱ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ በተማሪዎች ላይ የሚከተለውን ሰነዘረ ። በጋዜጣው ቃል ፤

" ገና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከሚመኙት የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ የሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስ ከተፈጥሮ ሀብት ከሰው ጉልበትና ከካፒታል ሌላ ዕውቀት ሀብረትና ቅጥታው የተጠበቀ መንግሥቱ የፀና አቋም እንዲኖር አስፈላጊ ነው ።

ሰላምና ፀጥታ ሲታጣ ሥርዓትና ሕግ ሲጣስ በሕይወትና በንብረት ላይ የሚያስከትለውን ጥፋት ለመገንዘብ የሩቅ ምሳሌ መሻት አያስፈልግም ።

" በአለፉት ወራቶች ውስጥ በጥቂት ተማሪዎች አነሳሽነት አልፎ አልፎ ፀጥታ የሚያደፈርስ በሕዝብ ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ የሚያደርስ ሁከት እየተፈጠረ ጥፋተኞቹ ከሕግ ፊት እየቀረቡ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ መደረጉ ይታወሳል ።

" ጥቂቶቹ ተማሪዎች የኢትዮጵያን አንድነት በሚጠሉ የባዕድ ተንኮለኞች ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ ፀጥታ ለማደፍረስ ለሰላማዊው ሕዝብ ሰላም ለመንሳት ያደረጉት ጥፋት በትዕግሥትና በይቅርታ ታልፎ ሳለ ሰሞኑን ጥቂቶች የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚያሳዩት ተግባር ሕገወጥ ከመሆኑ አልፎ መንግሥት ከዚህ ቀደም እንዳደረገው ሁሉ በትዕግሥት ከማይታለፍበት ደረጃ ደርሷል ። [5]

እንደዚሁም በህዳር 20 ቀን 1962 " ፍሬቢስ ሙከራ " በሚል ርዕስ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሳምንታዊው ጋዜጣ በተማሪዎች ላይ በከፊል የሚከተለውን አስተያየት ደረደረ ። በጋዜጣው አባባል ፡

" የኮሙኒዝምን ኢይዶሎጂ እናስፋፋለን የሚሉት ጥቂት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየጊዜው በሚያወጡት መጽሔታቸውና በሚበትኑአቸው ወረቀቶች የሕዝብ ፀጥታና ሰላማዊ ኑሮ ለማደፍረስ መሞከራቸው ተደጋግሞ ተገልጧል ። የባዕድን ፍልስፍና በመከተል የአገሪቱን ነባሪ ሥርዓትና ባህል ለመሻር መሞከር ከንቱነት ነው ።

" ኢትዮጵያ እንደሌሎች መንግሥቶች በሕገ መንግሥት ትመራለች ። ሕገ መንግሥቱም ግልጽና ቀና ነው ። ከሕገ መንግሥት ውጪ የሆነ ሁሉ ሕጋዊ አይደለም ። ያስከስሳል ። ያስቀጣል ። ሕገ መንግሥቱን የሚሳደብ የሚፃረር የሚተናኮልና የሚቃረን የመንግሥቱ ጠላት ነው ። ሕዝብ አምኖ የተቀበለውን ሥርዓት ለመሻር ባዕድ አሳብ የሚሰንዝር የቆየውንና የናረውን ልማድ ሁሉ የሚያኳስስ ሃይማኖትን የሚያቀል አባቶችን የሚያዋርድ የተደነገጉትን ሕጐች የማይታዘዝ በአጉል ትምክህትና ትዕቢት የሚመራ ብቻ ስለሆነ አሳቡና ዝንባሌው አደገኛ ነው ። " [6]

በዚህ ሁኔታ በተማሪዎች እንቅስቃሴና ተግባር ላይ በማስሚዲያ ዘመቻ የሕብረተሰቡን የቁጣና የጥላቻ ስሜት ከቀሰቀሰ በኋላ በታህሳስ መጨረሻ የፊውዶ ቡርጂው መንግሥት የቅጣት ክንዱን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ በማንሳት የአእዩተማ ፕሬዚዳንት ጥላሁን ግዛውን ጨምሮ በ30 የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ገደለ ። ዩኒቨርሲቲውንም ለአልተወሰነ ጊዜ ዘጋ ። የአእዩተማና የታግል መጽሔት ህልውና

ከዩኒቨርሲቲው ሰማዕታት ጋር አበቃ ። በዚህ ጊዜ በዩኒቨርሲቲው የጀበሃ ደጋፊዎች ከነበሩት ተማሪዎች ብዙዎች ሄደው ከምባሩ ጋር በመስክ ሲቀላቀሉ ሌሎቹ በውጭ አገር በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ የአ መጽ እንቅስቃሴ ላይ የሂስ ዘመቻ ከፈቱ ።

አአዩተማ በታህሳስ 1962 የፊውዶ ቡርጎው መንግሥት እስኪበት ነው ድረስ ከመንግሥቱ የፖሊስና የስለላ ኃይሎች ጋር በስውር የሚታግ ልበት "የአዞ" ድርጅት ወይም አሠራር (The crocodile Society) ተብሎ የሚታወቅ ምስጢራዊ የትግል ስልት እንደነበረው ከዚህ በላይ ተጠቅሶ አል ። በዚህ በአዞ የትግል ስልትና አሠራር የአአዩተማ አመራርና አባላት በአድሃሪው የገዥ መደብ ላይ ማንናኛውንም የተንኮል ዘዴ ፣ ሙያሪያ ፣ ታክቲክና ስትራተጂ በመጠቀም ከፍተኛ የሆነ የአመጽ ትግል እንዳካ ሄደበት የተረጋገጠ ነው ።

ነገር ግን የፊውዶ ቡርጎው መንግሥት በታኅሣሥ 1962 በአአዩተማ አመራርና አባላት ላይ የቅጣት እርምጃ ከወሰደባቸው በኋላ ከቀድሞ የአአ ዩ ተማ መሪዎችና አባላት አንዳንዶቹ ይህንኑ በመደብ ጠላት ላይ የተ ጠቀሙበትን የአዞ ምስጠራዊ የትግል ስልትና አሠራር ይዘው በልዩ ልዩ መንገዶችና ምክን የቶች ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ በፍለሳ በመሄድ ከኢ ተማሰአና ከኢተማአ አመራርና አባላት ጋር በጓዳዊ የትግል መንፈስ መቀላቀል ጀመሩ ።

የፍለሳው ዋና ዓላማ ግን የትምህርትና የሥራ ፍለጋ ሳይሆን በተለይ በነሐሴ 1962 ኢተማሰአ በአስራ ሰባተኛው ጉባኤ በጀበሃ ላይ የወሰደ ውን አቋም የብሔር ትምክህተኝነት መግለጫ ነው በማለት ውድቅ አድ ርጐ በኢተማሰአ አቋም ላይ በጀበሃ ደጋፊዎች የሚመራውን የአአዩተማ መስመር ለማራመድ ነበር ።

በዚህ ውስብስብ ነገር ፣ በነሐሴ 1962 ከአአዩተማ አባላት ጥቂቶች የአዞ ማህበርና አሠራር ኢንጂነር በነበረው በብርሃነ መስቀል ረዳ መሪነት አንድ የኢትዮጵያ መንገደኛ አይሮፕላን ጠልፈው ወደ ካርቱም ሱዳን መግ ባታቸው ይታወሳል ። እነዚህ በቁጥር ሰባት ወይም ስምንት የሚሆኑ ተማ ሪዎች ከሱዳን ወደ አልጀሪያ በመሄድ በብርሃነ መስቀል መሪነት ራሳቸ ውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በሰሜን አፍሪካ ወይም የአልጄሪያ ቡድን እያሉ መጥራት ጀመሩ ።

በታኅሣሰ 1962 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ መንግሥቱ የቅጣት እርምጃ ከወሰደ በኋላ ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ የፈለሱ የቀ ድሞ አአዩተማ አባላትና የአልጄሪያ ቡድን የኢትዮጵያ አብዮትና ብሔ ረሰቦች ጥያቄ በሚመለከት የአመለካከት ፣ የግንዛቤና የዓላማ አንድነት

ነበራቸው ። ሁለቱም ክፍሎች በአገር ውስጥ ከቀሩ የአአዩተማ አባላትና አመራር ጋር ጥብቅ የግንዛቤና የትግል አንድነት እንደነበራቸው የሚታ መስ ነው ።

በተጨማሪም ወደ አሜሪካና አውሮፓ የፈለሱ የቀድሞ አአዩተማ አባላትና የአልጄሪያ ቡድን በሕብረት በኢተማአ ላይ በኋላ የትግል ዘመቻ እስከከፈቱበት ድረስ የኢተማአ አመራር በኢተማሰአ ላይ የጀበሃ ግምባር ጥያቄ ጨምሮ በብሔረሰቦች ጉዳይ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የአአዩ ተማ አቋም ደጋፊ ነበር ።

መንግሥቱ በታኅሣሥ 1962 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የቅጣት እርምጃ ከወሰደ በኋላ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ስርጭትና የትግል መስመር እንደዚህ ሆኖ ሳለ ፣ ከቀድሞ የአአዩተማ መሪ ዎችና አባላት ወደ አሜሪካ የፈለሱት በነሐሴ 1962 በዋሽንግተን ዲ. ሲ. ከተማ ቢጀርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ በተደረገው በኢተማሰአ አሥራ ስምንተኛው ጉባኤ ተገኝተው በጀበሃ ጥያቄ ላይ በተለይ በኢትዮጵያ ብሔ ረሰቦችና አብዮት ጥያቄ ላይ በአጠቃላይ ኢተማሰአ በአሥራ ሰባተኛው ጉባኤ ላይ የወሰደው የቲዎሪና የፖሊሲ አቋም አደገኛ የሆነ የብሔር ትም ክህተኝነት መግለጫ ነው በማለት ብርቱ ሂስ ሰነዘሩ ። በአገር ቤት ውስጥ ለኢትዮጵያ አብዮት ነባራዊ ሁኔታ ተሟልቶ በላቲን አሜሪካ እንፊደል ካስትሮ እንቹጉቬራ ያካሄዱትን ዓይነት የትጥቅ ትግል በኢትዮጵያ ለመጀ መር ጊዜው መድረሱን "ፋኖ ተሰማራ እንደ ቼጉቬራ" እያሉ ከብዙ የትግል መፈክሮች ጋር በታላቅ ስሜት ተናገሩ ። የኢተማሰአ አባላትን የወጦበር ላይ ምሁራን ናቸው በማለት ነቀፉ ።

የተማሪዎች እንቅስቃሴ የትግል ስልት

ከዚያ በኋላ የተጠቀሱት ሰዎች የኢተማሰአ አስራ ዘጠነኛው ጉባኤ በነ ሐሴ 1963 በካልፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ግቢ በሉሳንጀለስ ከተማ እስኪደረግ ድረስ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በልዩ ልዩ የአሜሪካ ከተሞች በሚገኙ የኢተማሰአ ቅርንጫፍ የቀበሌ ማህበራት ውስጥ እየተዘዋወሩ በሚመ ጣው የማህበሩ ጉባኤ የኢተማሰአን አመራር ለመያዝ በአአዩተማ የአዞ ስልትና አሠራር የተሳካ ቅስቀሳና ዝግጅት አካሄዱ ።

በተጨማሪም በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥያቄ ከአልጄ ሪያ ቡድን The National Question In Etqiopia በሚል ርዕስ ከጥላሁን ታከለ በሚል የብዕር ስም በብርሃነ መስቀል ረዳና በኢያሱ ዓለማየሁ ተዘ ጋጅቶ የተላከውን አንድ ልዩ ጽሑፍ በኢተማሰአ የኒዮርክ ቀበሌ ቅርን

በድብቅ አሳትመው በብሔረሰቦች ጥያቄ የራሳቸውን አቋም በኢትማሰአ ስም በመላው ዓለም ላይ ለሚገኙ ለኢትዮጵያ አማ አካላትና አባላት በይፋ አሰራጩ ። [7]

በኢትማሰአ ውስጣዊ ደንብ መሠረት እስከ 1963 የሎሳንጀለስ ጉባኤ ድረስ የማህበሩ ፀፕሬዚዳንት የሚመራ አመራር ምክር ቤት በዓመቱ ጉባኤ ፍጻሜ በዲሞክራሲያዊ አሠራር በማህበሩ መደበኛ አባሎች በይፋ ይመረጣል ። ከአንድ ዓመታዊ ጉባኤ እስከሚቀጥለው ጉባኤ ድረስ የማህበሩን ጉዳይ ለአንድ ዓመት በበላይነት የሚመራውና በጉባኤው የሚቀጥለውን የአመራር ምክር ቤት አስመርጦ ሥልጣኑን ለተከታዩ አመራር የሚያስረክበው የማህበሩ ዓመታዊ ፕሬዚዳንት እንደነበር ይታወሳል ።

በትግልና በአገር አንድነት ስም በኢትማሰአ የ1963 ሎሳንጀለስ ጉባኤ በአንድነት የተገኙ የቀድሞ አአዩተማ አባላት በቅድሚያ በአሜሪካ ከተሞች እየተዘዋወሩ በኢትማሰአ ቅርንጫፍ ማህበራት ውስጥ በአዞ የድርጅትና የአመራር ስልት የማህበሩን ሥልጣን ያዙ ። [8] የማህበሩን ነባር አመራር ከሥልጣን አወረዱ ። ራሳቸውን "አዲሱ ኢትማሰአ" ብለው ሰየሙ ።

በዚህ ሁኔታና አሠራር በጀበሃና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥያቄ በ1963 ሎሳንጀለስ ጉባኤ ኢተሰአማ "አዲሱ ኢትማሰአ"እና "አሮጌ ኢትማሰአ" ተብሎ በሁለት አንጃዎች ተከፈለ ። ከ1963 ሎሳንጀለስ "ኩዴታ" በኋላ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ የአመጽ እንቅስቃሴ የብሔረሰቦች ጥያቄ የመጀመሪያ ደረጃ የአብዮትና የመደብ ጥያቄ የሁለተኛ ደረጃ ትኩረትና ተግባር እየሆነ ሄደ ።

በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ የአንጃዎች ክስተት

በአአዩተማ የአዞ ስልትና አሠራር የኢትማሰአን ሥልጣንና አመራር የያዘው " አዲሱ ኢትማሰአ " በጉባኤው ውሳኔ የጀበሃንና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ጥያቄዎች በሚመለከት በ1962 የኢትማሰአ ጉባኤ በፊላደልፊያ ውሳኔ የወሰደውን አቋም በመሻር በምትኩ ፡ በፊት በህዳር 1962 በአአዩተማ መጽሔት ታኅሳሥ 1962 ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሞት የቅርብ ምክንያት የሆነውንና "የአዲሱ ኢትማሰአ" መሥራቾች ከአልጀሪያ ቡድን ጋር ተመሳጥረው በአዞ አሠራር በመጋቢት 1963 በኢትማሰአ የቀበሌ ቅርንጫፍ ማህበር መጽሔት አሳትመው ያሰራጨትን አቋም አሁን በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ይፋ የሆነ የፖሊሲ አቋም አድርጎ በልዩ መጽሔት በዓለም ላይ አሰራጨ ። [9]

በአውሮፓ የኢተማአ አመራር እንደ አአዩተማም የጀበሃንና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ጥያቄ በሚመለከት የኢተማሰአን የፊላደልፊያ ውሳኔ መቃወሙ ይታወሳል ። በመሆኑ የቀድሞ አአዩተማ አባላት በነሐሴ 1963 ሎሳንጀለስ ጉባኤ የኢትማሰአን አመራር " በኩዴታ " መያዛቸውን በደስታ ተቀበለ ። [10]

ነገር ግን ከሎሳንጀለስ ጉባኤ በኋላ ብዙ ሳይቆዩ የአልጄሪያ ቡድንና አዲሱ የኢትማሰአ አመራር ግምባር ፈጥረው ኢተማአንም ጨምረው ለመውሰድ አዲስ የአዞ ዘመቻ በኢትማአ ላይ ቀየሱ ። በዚህ አካሄድ በ1964 በፊረንሳይ አገር በተካሄደው በኢተማአ አሥራ ሁለተኛ ጉባኤ በቀረበ በአንድ ጽሑፍ በብርሃነ መስቀል ረዳ የሚመራው የአልጄሪያ ቡድን በኢትማአ አመራር ላይ ብርቱ ነቀፋ ሰነዘረ ። [11]

በሌላ በኩል በኢተማአ አሥራ ሁለተኛው ጉባኤ የኢተማአ ተወካዮች በበኩላቸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች የዓለም አቀፍ ማህበር (ኢተዓአማ) ደንብና አሠራር የሚሻሻልበት የውሳኔና የደንብ ረቂቅ በድርጅታዊ አሠራር አዘጋጅተው አቀረቡ ። በቀረበው አሳብ ላይ አዲሱ ኢትማሰአና የአልጄሪያ ቡድን ተወካዮች ተስማሙ ። በመሆኑም የኢተዓአማ ጉባኤ በሚያዝያ 1965 በበርሊን ከተማ ተካሄደ ።

በበርሊኑ ጉባኤ ለኢተዓአማ ምስረታ የአባል ማህበራት ውክልናና የምርጫ ሥነ ሥርዓት ጥያቄ ተነስቶ ከፍተኛ ችግር ፈጠረ ። በዚህ ነገር እስከ 1962 ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ ሶስት መሠረታዊ አባል ማህበራት አአዩተማ ፡ ኢተማሰአና ኢተማአ እንደነበሩ ይታወሳል ። በ1965 በበርሊኑ ጉባኤ በኢተዓአማ አባል ማህበራት የምርጫ ሥነ ሥርዓት ጥያቄ የስድስት ቀናት ጭቅጭቅ ከተካሄደበት በኋላ ሶስት አዳዲስ ማህበራት ማለትም የአልጄሪያ ቡድን ፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በሌባኖን (ኢተማሌ) እና የኢትዮጵያ ሴቶች ዓለም አቀፍ ጥናት ክበብ (ኢሴዓአጥክ) ዓለም አቀፍ የአመጽ እንቅስቃሴው ቅርንጫፍ ማህበራት እንዲሆኑ ተወሰነ ። በሌላ በኩል በአገር ውስጥ በነበረው የፖለቲካ ችግር ምክንያት በበርሊኑ ጉባኤ የአአዩተማ ተወካዮች አልተገኙም ። እንዲሁም ከሰሜን አሜሪካ " አሮጌው ኢትማሰአ " የኢተማአና የአዲሱ ኢትማሰአ የትግል መስመሮችንና ስልቶችን በመቃወም በበርሊኑ ጉባኤ አልተሳተፈም ።

በጉባኤው የአልጄሪያ ቡድን ተወካይ ነኝ ብሎ የቀረበው ክፍል የወከለው በአልጄሪያ በስምንት የሚቆጠሩ ስደተኞችን ሲሆን ፡ በሌባኖን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ተወካይ ተብሎ የቀረበው ክፍል ደግሞ የወከለው በዚያ የመካከለኛው ምሥራቅ አገር በወቅቱ በ30 የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ነበር ። የኢትዮጵያ ሴቶች ዓለም አቀፍ

ጥናት ክበብ ተወካይ ተብሎ በጉባኤው የአባልነትና የምርጫ መብት የተሰጠውም ክፍል ቢሆን በአሜሪካ አዲሱ ኢተማስአ ገና ከስሩ ለማደራጀት የሚፈልገው የሴቶች ማህበር ጥንስስ ነበር ።

ስለዚህ በ1965 በበርሊኑ ጉባኤ የአልጄሪያ ቡድን ፡ የኢተማሌና ኢ.ሴ.ኤ.አ.ተክ ተወካዮች የተባሉ ግለሰቦች የተደራጁ ማህበራት ተወካዮች አልነበሩም ። በጉባኤውም በወቅቱ የጀበሃንና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን ጥያቄ በተመለከተ ተመሳሳይ አመለካከትና ገንዛቤ የነበራቸው ሁለቱም የኢተማአና የአዲሱ ኢተማሰአ የአመራር ክፍሎች ኢተአዓማን በአዲስ ቅርጽ በማደራጀት በየበኩላቸው የኢትዮጵያ ተማሪዎችን ዓለም አቀፍ የአመጽ እንቅስቃሴ አመራር በድርጅታዊ ጥበብ ማለትም በአዞ የትግል ስልት ለመያዝ ስውር ዓላማ ነበራቸው ።

በመጨረሻ ለአዲሱ ወይም ለተሻሻለ ኢተዓአማ ምሥረታ በሚያዝያ 1965 በርሊኑ ጉባኤ ከተገኙ አምስት አባል ማህበራትና ቡድኖች በጉባኤው የምርጫ ሂደትና ውጤት በሁኔታዎች አመለካከትና ግንዛቤ ተመሳሳይ የነበሩ ከአሜሪካ አዲሱ ኢተማሰአ ፡ የአልጄሪያ ቡድንና የኢ.ሴ.ኤአ ጥክ ተወካዮች በአዞ የትግል ስልትና አሠራር በሌላው ወገን እንዲሁም የራሳቸው የሆነ ልዩ የፖለቲካ ዓላማና የትግል ስልት የነበራቸውን የኢተማአንና የኢተማሌን ተወካዮች በምርጫ ስነስርዓት በማሸነፍ ራሳቸውን በሕብረት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን (ኢተዓአፌ) በማለት በአዲስ አካልና መዋቅር በይፋ መሠረቱ ። [12]

የኢተማአና የኢተማሌ ተወካዮች በምርጫ ሂደት በፌዲሬሽኑ አንጃ እጅ ታላቅ ሽንፈት ከደረሰባቸው በኋላ የጉባኤውን ውጤት ውድቅ አድርገው ወደ እየማህበራቸው ተመለሱ ።

በዚህ ሁኔታ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ታሪካዊው የአመጽ እንቅስቃሴ በጀበሃና በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥያቄ ከነሐሴ 1961 እስከ ሚያዝያ 1965 ድረስ ለአምስት ዓመታት በተነሳው አንጃዊ የአመለካከትና የግንዛቤ ውዝግብ በመጨረሻ በአዞ የትግል ስልትና አሠራር የተፈጠረው ኢተዓአፌ ሆኖ ቀረ ። በአገር ውስጥ የነበረው አአዩተማ የፌዴሬሽኑ አካል ሲ ሆን በአንጻሩ ግን ኢተማአሰና አሮጌው ኢተማሰአ የፖለቲካ ጠላት ሆኑ ።

ባጭሩ በ1966 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት እንደ እሳት ገሞራ በድን ገት በፈነዳ ጊዜ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሶስቱ የፊዴሬሽን ፡ የኢተማአና አሮጌው ኢተማሰአ አንጃዎች እርስ በርሳቸው የፖለቲካና የሥልጣን ጠላቶች ነበሩ ።

ምዕራፍ 3 የአብዮቱ ፍንዳታ ፡

የመንግሥቱ የቅጣት እርምጃ

በታኅሣሥ 1962 በአዲስ አበባ የፊውዶ ቡርዣ መንግሥት በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ ግድያ ፈጽሞ ዩኒቨርሲቲውን ከዘጋ በኋላ ከ1962 እስከ 1966 ድረስ የአገሪቱ ዓለም አቀፍ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበራት በተለይ በጀበሃና በብሔረሰቦች ጥያቄዎች ላይ በአንጃዊ ቡድኖች ተከፋፍለው እርስ በርሳቸው አንጃዊ የፖለቲካ ጦርነት ሲዋጉ ፡ በአገር ውስጥ የሁለተኛና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችና መምህራን በሕብረት እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ በቀድሞ ዘውዳዊ የገዥው መደብ ላይ የአመጽ እንቅስቃሴ በአገር አቀፍ ደረጃ እንደአፋፋሙት ይታወሳል ።

በዚህ ወቅት የተማሪዎች የአመጽ እንቅስቃሴ ምን ያህል በአገር አቀፍ ደረጃ ተስፋፍቶ እንደነበር በተጨባጭ ከሚያሳዩን ነገሮች አንዱ በ1964 መጀመሪያ ከአጼው ጋር አልጋወራሹ ፡ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ፡ የዘውድ ኣማካሪዎችና የካቢኔ ሚኒስትሮች በአንድነት በጉባኤ ተቀምጠው በሰጡት የሥራ መመሪያ መሠረት ፡ " ስለተማሪዎች የጸጥታ ማስከበሪያ " የተቋቋመውና በአገር ግዛት ሚኒስትር ሰብሳቢነት የአገር መከላከያና የትምህርት ሚኒስትሮች ፡ የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም ፡ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ፡ የምድር ጦር ዋና አዛዥ ፡ የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ ፡ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ፡ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዋና ሹም ፡ የልዩ ካቢኔ ሹምና የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት በአባልነት የሚገኙበት ኣንድ ከፍተኛ ኮሚቴ በተማሪዎቹ የአመጽ እንቅስቃሴ ላይ ያሳለፈው ብርቱ የቅጣት ውሳኔ ነው ። የኮሚቴው ውሳኔ በአብዮቱ ታሪክ በአጠቃላይ በተማሪዎች አብዮታዊ አመጽ በተለይ አንድ ከፍተኛ ሰነድ ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርቦአል ።

በኮሚቴው ቃል ፡

" የኢትዮጵያ ተማሪዎች በየጊዜው እየተነሱ ትምህርት በማቆም በሕዝብ ንብረትና ሕይወት ላይ አደጋ በማድረስ ትምህርት ቤቶችን በመስበር የትምህርት ዕድገት እንዲጨናገል፡ የልጆች ዕድል እንዲሰናከል፡ ሕዝብና የመንግሥት ባለሥልጣን የሚዘልፍ ሕግ ውጥ ፖለቲካ አዘል የሆነ ልዩ ልዩ ጽሑፍ በመበተን ግርግርና ሽብር አድርገው ጸጥታ በመንሳታቸው ጉዳዩ ግርግዊ ጀንሆይ ፡ ልዑል አልጋወራሽ ፡ ከቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ፡ ክቡራን የዘውድ አማካሪዎችና የካቢኔ ሚኒስትሮች ባሉበት ስብሰባ ተደርጉ አጥፊ እንዲቀጣ ፡ ትምህርት የሚፈልግ እንዲማር ጸጥታው

በአሥራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች በሚገባ እንዲከበር ተብሎ በተወሰነው መሠረት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ባለሥልጣኖች ስለተማሪዎች ጸጥታ ማስከበር ቀደም ብለው ስለተቋቋሙ ጉባኤው ስብሰባ አድርጉ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት እንዲፈጸም ወስኗል ።

ው ሳ ኔ ፤

1. " ማናቸውም የዩኒቨርሲቲ ፣ የ2ኛ ደረጃና የግዛት ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንማራለን ካሉ ጸጥታ ነሾችን ለመከላከል ፖሊስ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ እንዲጠብቅ ፤

2. " ብጥብጥ ያስነሱ የተማሪ መሪዎች እንዲያዙና እንዲቀመጡ ፣ ቅጣትም ከልማት ጋር የተያያዘ አድካሚ ሥራ እንዲሆን ፣ አንማርም ብለው ከትምህርት ቤት የወጡት ተማሪዎች ዳግመኛ እንዳይገቡ እንደወጡ እንዲቀሩ ፣

3. " ተማሪዎች በየጊዜው የሚያደርጉትን ሕገወጥ ሥራ ሕዝብና ወላጆች እንዲያውቁት በወላጆች ኮሚቴ በኩል በቴሌቪዥን ፣ በሬዲዮ ፣ በጋዜጣ በገዥዎች ጭምር ያለማቋረጥ እንደሚገባ እንዲገለጽ ፤

4. " ሕገወጥ የሆኑ የዩኒቨርሲቲ ፣ የኮሌጅና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ማህበር ጥፋታቸው በፖሊስና በጸጥታ በኩል ተጣርቶ ለዩኒቨርሲቲ ቦርድና ለትምህርት ሚኒስቴር እያቀረቡ ማህበሩ እንዲፈርስ ማድረግ ፣

5. " ትእዛዙን አክብሮ እንማራለን ያሉ ተማሪዎች ጥቂትም ቢሆኑ ጥበቃ እየተደረገላቸው እንዲማሩ ፣

6. " በዚህ ቃለ ጉባኤ በቁጥር 2 የተመለከቱትና ከትምህርት ቤት ከወጡ በኋላ ጥፋታቸውን እየተቀበሉ የሚማሩትን እንዳይማሩ የሚያውኩ ለጥፋት ሥራ የሚዘጋጁ ተማሪዎች ሲገኙ በ28 ኛው ዓመት በቁጥር 13 በአንቀጽ 3 በፊደል " ሀ " መጋቢት 27 ቀን 1961 ዓ ም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣና ይኸው አንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በማስረዘም በ31ኛው ዓመት ቁጥር 5 በ"ሀ" ፊደል ታኅሣሥ 19 ቀን 1964 ዓ ም በወጣው አዋጅ መሠረት ፖሊስ እየያዘ አስፈርዶ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ያደርጋል ።

7. አጥፊ ተማሪዎችን ፖሊስ እየሰበሰበ ብዛታቸው ከፍ ያለ እንደ ሆነ በጸጥታ ማስከበሪያ አዋጅ መሠረት ለአገር ግዛት አቅርቦና አስወስኖ ለጦር ሠራዊትና ለክብር ዘበኛ ያከፋፍላል ።

8. " ተማሪዎች በጥፋታቸው ሲቀጡ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ለሌሎችም ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስቴር ለምግብና ለሌላ ወጭ የሚሰጠውን ገንዘብ ተማሪዎቹ ለተሠሩበት ክፍል ይከፍላል ። ከዩኒቨርስቲና ከትምህርት ሚኒስቴር የሚገኘው ተመላሽ ባይበቃ በተለይ ቀርቦ እንዲፈቀድ ይደረጋል ።

9. " እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ውሳኔዎች በአሥራ አራቱም ጠቅላይ ግዛቶች ፣ አውራጃዎችና ወረዳዎች እንዲሠሩባቸው ስለተወሰነ ከቡራን ጠቅላይ ገዥዎችና የጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች ፣ የጠቅላይ ግዛት ፖሊስና ዋና አዛዦች ፣ የክብር ዘበኛና የብሔራዊ ጦር አዛዦች ፣ የጠቅላይ ግዛቱ የትምህርት ሥራ መሪ ፣ የአውራጃና የወረዳ የትምህርት ቤቶች ሥራ መሪዎች በአገረገዥዎች ኃላፊነት እየተሰበሰቡ በህብረት ፕላን በትእዛዝ እያወጡ ያፈጸጸሙን ውጤት በየጊዜው እንዲሰጡ ማድረግ ነው ።

" ፊርማ————የሰብሳቢውና የአባሎች

" ማህተም ————ያገር ግዛት ሚስቴር " [1]

የተማሪዎች አመፅ በገጠር

በዚህ ከፍተኛ የመንግሥት ፖሊሲ ውሳኔና ትእዛዝ መሠረት ፣ ለምሳሌ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በጉልተኞችና በመንግሥት ባለሥልጣኖች ላይ በተማሪዎች ፣ በአስተማሪዎችና በገጠሩ ሕዝብ ሕብረት የተቀሰቀሰውን ታላቅ የአመጽ እንቅስቃሴ በኃይል ለማጥፋት በጥቅምት 1965 በአውራጃው ገዥ ሰብሳቢነት ፤ የተካሄደው ጉባኤ ቃል እንዲህ ያላል ።

" የጸጥታው ሁኔታ እየተባባሰ በመሄዱ አስጊና አሳሳቢ መስሎ ስለታያ ፣ የ6ቱ ወረዳ ገዥዎችን ፣ ምክትል ወረዳ ገዥዎችንና የ6ቱ ወረዳ ፖሊስ አዛዦችን ፣ ባላባቶች ፣ አፈርመልከኞች ፣ ሠንጋ ቆሮጮች ፣ ጭቃሹሞችና ታላላቅ የሀገር ሽማግሌዎች ቀርበው ባሉበት ሃሳብ ለሃሳብ ተወያይተው አንድ ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል " ተብሎ የተጠራው ከፍተኛ ጉባኤ በአውራጃው የአመጽ ኃይሎች እንቅስቃሴ ላይ የወሰነው ብርቱ የቅጣት እርምጃ በደራሲው የምርትና የባህል ዘመቻ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ (1975) በተሰኘው መጽሐፍ በገጽ 105—113 ሰፍሮ

በአብዮቱ ዋዜማ በአገሪቱ ገጠር የአመጽ ኃይሎችን የእንቅስቃሴ ስፋትና ዓይነት በግልጽ ያሳያል ።

የአውራጃው የቅጣት ውሳኔ የአመጽን ኃይሎች እንቅስቃሴ ሲገልጽ እንደሚከተለው ይወነጅላል ። በሰነዱ ቃል ፤

" ተማሪዎችና ግብረአበሮቻቸው የሆኑት ወላጆቻቸውና ሌሎችም መንገድ እንሠራለን በማለት ምስጢሩ ያልታወቀ የውስጥ ስምምነት አድርገው የመንግሥቱ ክፍል ባለሥልጣን ያላመነበት ውል ተፈራርመው ጉዳዩን የማያውቀውን ሰላማዊ ሕዝብ የእነርሱ ሕገ ወጥ አሠራርና ተግባራቸውን ተባባሪ ለማድረግ ፈርሙ እያሉ በማስገደድ የሚያስፈርሙ ለመሆኑና አልፈርምም ያለውን ከመንግሥት ሕግና ሥርዓት ውጭ በማዋረድ ንብረቱን በመዝረፍ ባለንብረቱንም በእግር ብረትና በገመድ " [2] እያሰሩ የአመጽ ቅጣት ይሰጡ ነበር ።

የመምህራን አመፅ

በ1966 የኢትዮጵያን መምህራን በፊውዶ ቡርዣው መንግሥት ላይ በአመጽ የቀሰቀሱአቸው ወቅታዋ ጥያቄዎች የደሞዝ ጭማሪና የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጉዳዮች ነበሩ ። ከ1934 ጀምሮ በኢትዮጵያ በሀውርታዊ ሕብረተሰብ ዘንድ በትምህርት መሣሪያ ብሔራዊና ባህላዊ ውህደት በመገንባት ተግባር የኢትዮጵያ መምህራን ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ዜጐች ናቸው ። በ1941 " የኢትዮጵያ መምህራን ሕብረት " የአገሪቱ የመጀመሪያው የሙያ ማህበር ነበር ። በ1958 የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) በመንግሥቱ ዘንድ በይፋ ታወቀ ።

ከ1958 እስከ 1964 የኢመማ የሽግግር ወቅት ነበር ። በዚህ የሽግግር ዘመን የኢትዮጵያ መምህራን በአስራ አምስት የአዲስ አበባ ፣ የሸዋ ፣ የአርሲ ፣ የሐረርጌ ፣ የባሌ ፣ የሲዳሞ ፣ የጋሞጐፋ ፣ የኢሉባቦር ፣ የከፋ ፣ የወለጋ ፣ የጐጃም ፣ የጐንደር ፣ የወሎ ፣ የትግራይና የኤርትራ የክፍለ ሀገር ቅርንጫፍ ማበሰራትና በቅርንጫፍ ማህበራቱ አንድነት ደግሞ በብሔራዊ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ተደራጁ ። " የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አመሠራረትና ታሪክ " በሚል ርዕስ ከማህበሩ አካባቢ በተገኘው በአንድ ጽሑፍ እንደተገለጸው ፣ የኢመማ አባላት ዕድገትና ብዛት — በ1948 ዓ ም 165 ፣ በ1955 ዓ ም 842 ፣ በ1964 ዓ ም 5640 ፣ በ1966 ዓ ም 11769 ነበር ።

ከ1964 እስከ 1966 ኢመማ በድርጅት ፣ በቁጥርና በፖለቲካዊ ግንዛቤ ከፍተኛ ዕድገት ያሳየበት ጊዜ ነበር ። ከድርጅት አኳያ ፣ ኢመማ በአገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ አምስት አባላት—ፕሬዚዳንት ፣ ምክትል ፕሬዚዳንት ፣ ዋና ጸሐፊ ፣ ምክትል ዋና ጸሐፊና ገንዘብ ያዥ ያሉት ማዕከላዊ የአመራር ኮሚቴና በፕሬዚዳንቶች የሚመሩ አሥራ አምስት ክፍለ ሀገር ቅርንጫፍ ማህበራት አሉት ። የኢመማ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ተራ በተራ በየክፍለ ሀገሩ ርዕሰ ከተማ ይካሄዳል ።

የኢመማ ሰባተኛው መደበኛ ዓመታዊ ጉባኤ በ1964 በአሥመራ ከተማ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በአብዮቱ የቅርብ ዋዜማ በድርጅትና በአመለካከት ከፍተኛ ዕድገት እንደአሳየ የሚከተሉት የዕድገት ለውጥ ምልክቶች ይመሰክራሉ ። ለምሳሌ ከአሥመራ ጉባኤ በኋላ የኢመማ አባላት ብዛት በኃይል እየጨመረ ሄደ። በ5000 ብር አካባቢ የነበረው የማኅበሩ ዓመታዊ ገቢ መጠን ደግሞ ወደ 120,000 ብር አደገ ። በ27,000 ብር የሚገመት የገንዘብና የጉልበት ወጪ ተደርጉበት በአዲስ አበባ የማኅበሩ ማዕከላዊ ጽሕፈት ቤት ከሙሉ መሣሪያ ጋር ተደራጀ ። የመምህራን የመረዳጃ ድርጅት ተመሠረተ ። በዚህ ሁኔታ የመምህራኑ የፖለቲካ አመለካከትና ግንዛቤ እያደገ ሄደ ።

የኢመማ የደሞዝና የትምህርት ጥያቄ

በመጨረሻ የኢመማ የድርጅትና የፖለቲካ አመለካከት ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ የታየው በመስከረም 1966 በአርባ ምንጭ ከተማ በዘጠነኛ መደበኛ ዓመታዊ ጉባኤ የመምህራን ደሞዝ ጭማሪና " ሴክተር ሪቪው " በተባለው በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጉዳዮች ላይ በወሰደው ታሪካዊ ውሳኔ ነው ።

ሴክተር ሪቪው ወይም አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ለኢትዮጵያ መምህራንና ሕዝብ ሳይታወቅ ከዓለም ባንክ በተሰጠ የገንዘብ እርዳታ 51 የአገር ውስጥ 30 የውጭ አገር የትምህርት ባለሙያዎች ከ69 የመንግሥት ሠራተኞች ጋር በድምሩ 160 የትምህርት ባለሙያዎችና የመንግሥት ሠራተኞች ከግንቦት 1964 እስከ ነሐሴ 1965 ድረስ በሁለት ዓመታት ውስጥ በምስጢር አጥንተው ያቀረቡትና በመስከረም 1967 በሥራ ላይ እንደሚውል የታሰበ አዲስ የትምህርት ፖሊሲና ፕሮግራም ነበር ። [3]

የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማ አገሪቱ ከ1934 እስከ 1966 ድረስ ለ32 ዓመታት የተከተለችው የትምህርት ፖሊሲና ፕሮግራም ለአገሪቱ የትምህርት ደረጃ በመጠንም በዓይነትም በቂ ዕድገት የማይሰጥ ሆኖ በመገኘቱ ፣

ለሕዝብ የሙያ ትምህርት በዝቅተኛ ደረጃ በብዛትና በስፋት ለማዳረስ ይችላል ተብሎ የተገመተ ነበር ። [4] የሥርዓተ ትምህርቱ ዓላማና ተግባር ምን እንደሆነ በወሬ እንደሰሙ የኢትዮጵያ መምህራን ፣ ተማሪዎችና ወላጆች በዘመነ ኮሎኒያሊዝም አውሮፓውያን ለቅኝ ግዛት ሕዝቦች ያስተምሩት የነበረውን ዓይነት ዝቅተኛ የሙያ ትምህርት አያስፈልገንም በማለት በመንግሥቱ ላይ የቅስቀሳ ዘመቻ ከፈቱ።[5] የዘመቻው መሪና አዝማች ኢመማ ሆነ ።

የመምህራን ደሞዝ ጭማሪና አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በሚመለከት ፣ በመስከረም 1966 አርባ ምንጭ ጉባኤ መጨረሻ ኢመማ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች ቀጥሎ የተመለከቱት ነበሩ ። [6]

የደሞዝ ጥያቄ ።

1. የእያንዳንዱ መምህር ደሞዝ አሥር በመቶ እንዲያድግ ፣
2. መምህራን ከሥራቸው በጡረታ እስኪወጡ ድረስ በደሞዛቸው ዕድገት የጣራ ወሰን እንዳይደረግ ፤
3. በደሞዝ ጭማሪ ጉዳይ ለቀረበው ጥያቄ መንግሥት እስከ ጎዳር 30 ቀን 1966 ድረስ ተገቢውን የስምምነት መልስ እንዲሰጥ ኢመማ " በጥብቅ " ጠየቀ ።

የሥርዓተ ትምህርት ጥያቄ

1. የሥርዓተ ትምህርቱ " ብሔራዊ ፍልስፍናው " በቅድሚያ ሳይገለጽ ፣
2. " የመሬት ይዞታ ለውጥ " በቅድሚያ ሳይደረግ ፣
3. " የአውራጃዎች የውስጥ አስተዳደር ደንብ " አስቀድሞ ሳይወጣ ፤
4. የሥርዓተ ትምህርቱ " ትምህርታዊ ጽሑፎችና መሣሪያዎች" በቅድሚያ ሣሳይዘጋጁ ፤
5. " የግል ትምህርት ቤቶች በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የሚሠሩ መሆናቸው " በቅድሚያ ሳይታወቅ ፣
6. በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት " የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲከፈልበት መጠየቁ " የማይሰራ በመሆኑ እስኪሰረዝ ፤
7. በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ለመምህራኑ " የሥራው ዋጋ የተመደበው 153 ብር ካለው የኑሮ ሁኔታ ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ " እስኪለወጥ ድረስ " የሥርዓተ ትምህርቱን በሥራ ላይ መዋል በጥብቅ እንቃወማለን " በማለት ኢመማ አስጠነቀቀ ።

የመምህራኑን ደሞዝ ጥያቄ በተመለከተ መንግሥት በጎዳር 30 ቀን 1966 የሰጠውን መልስ የኢመማ የአመራር ኮሚቴና የአሥራ አምስቱ ክፍለ ሀገር ቅርንጫፍ ማህበራት ተወካዮች በታኅሣሥ 12 ቀን 1966 በጋራ ስብሰባ መርምረው የቀረበውን ጥያቄ በትክክል የማይመልስ ነው በማለት ውድቅ አድርገውት ፣ ከታኅሣሥ 12 ቀን ጀምሮ በ58 ቀናት ውስጥ ለመምህራኑ የተስተካከለ የደሞዝ ጭማሪ ባይደረግ በፋሽዝም ሰማዕታት በዓል ዋዜማ ማለትም በየካቲት 11 ቀን 1966 የአገሪቱ መምህራን በአገር አቀፍ ደረጃ ሥራ እንደሚያቆሙ ማስጠንቀቂያ ሰጥተው ወደ እየመጡበት ተመለሱ ።

ነገር ግን ከታኅሣሥ 12 ቀን እስከ ጥር 27 ቀን 1966 ድረስ በ43 ቀናት ውስጥ የመምህራኑን የደሞዝና የሥርዓተ ትምህርት ጥያቄዎች በሚመለከት የትምህርት ሚኒስቴር ምንም ተግባራዊ እርምጃ ሳይወሰድ ቆየ ። በሌላ በኩል በዚህ ወቅት የአገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በመንግሥቱ ላይ ብዙ ተፅዕኖ ማሳደር ጀመሩ ።

ለምሳሌ በዚህ ወቅትና ሁኔታ በመንግሥቱ በኩል ተደብቆ የኖረው የወሎ ረሀብ እልቂት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከስቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመንግሥቱ ላይ በታይለ አስቆጣ።በዓለም አቀፍ ደረጃ በነዳጅ ዘይት ዋጋ ላይ የተደረገው ለውጥ በኢትዮጵያም ላይ የኢኮኖሚ ችግር አስከተለ ። በመሆኑም በታኅሣሥ 30 ቀን 1966 የንግድ ፣ የኢንዱስትሪና የቱሪዝም ሚኒስቴር በነዳጅ ይዘት የዋጋ ለውጥ " እንደሚደረግ በዜና ማሰራጫዎች ለሕዝቡ አስታወቀ ። በጥር 4 ቀን በነገሌ ቦረና በኑሮ ሁኔታ ግፊት የአራተኛው ብርጌድ ወታደሮች በአመጽ እርምጃ አለቆቻቸውን በቁጥጥር ሥር እደረጉ የሚል ወሬ ተሰማ።በአዲስ አበባ ተማሪዎችና አስተማሪዎች በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጉዳይ በየቦታው ወረቀት እየበተኑ ሕብረተሰቡ በመንግሥቱ ላይ በአመጽ እንዲነሳ ብርቱ ቅስቀሳ ጀመሩ ።

የኢመማ ታሪካዊ ትግል በአፄው የመጨረሻ ችሎት

በአዲስ አበባ መንገዶችና መሥሪያ ቤቶች በመንግሥቱ ላይ የተበተኑ የቅስቀሳ ጽሑፎች በኢመማ ጽሕፈት ቤት ማባዣ ማሽን እየተባዙ እንደሚሠራጩ በመንግሥቱ ጸጥታ ክፍል እንደተደረሰበት ታውቋል ። ይህንን መነሻ በማድረግ በከተማው ጸረ መንግሥት የሆነ ቀስቀሳ እንደሚካሄድ የፀጥታ ክፍሎች በቀጥታ ለአጼው በማሳወቃቸው ፣ ሰኞ ጥር 27 ቀን የኢመማ ፕሬዚዳንት በፖሊስ ሠራዊት አዛዥ አቅራቢነት ለጥያቄ በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ወደ አጼው ቀረበ ።

በአዲስ አበባ ኢመማ ለተማሪዎችና ለአስተማሪዎች ጸረ መንግሥት ቅስቀሳ ማዕከላዊ መሣሪያ ሆኖአል የተባለውን ወሬ በአጼው ዘንድ አስተባብሎ የኢመማ ፕሬዚዳንት በሌላ በኩል በኢትዮጵያ መምህራንና በት

ምህርት ሚኒስቴር መካከል በደሞዝና በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጥያቄ ዎች ከፍተኛ የሆነ ችግር መፈጠሩን ለአዱው በቀጥታ ለማሳወቅ ጥሩ አጋጣሚ አገኘ ። ከዚያ በኋላ አዱው ፕሬዚዳንቱን የተባለውን ችግር በሚ መለከት አስፈላጊውን ማስረጃ ይዘህ በማግሥቱ ጥር 28 ከጥዋቱ በአራት ሰዓት ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት እንድትቀርብ ብለው አዘዙት ።

ማክሰኞ ጥር 28 ቀን በታላቁ ቤተ መንግሥት ከአዱው ጋር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ፣ የአገር ግዛትና የትምህርት ሚኒስትሮች ፣ የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ፣ የእልፍኝ ዋና አስከልካይ ፣ የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ ፣ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ፣ የሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ ዋና ሹም ፣ የቀዳማዊ ኃይ ለ ሥላሴ በጉ አድራጉት ሽልማት ዲሬክተር ጭምር ብዙ የአገሪቱ ከፍ ተኛ ባለሥልጣኖች በተገኙበት ስብሰባ የኢመማ አመራር ኮሚቴ አባላት በግምባር ቀርበው በመምህራኑ ደሞዝና በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጉዳ ዮች በትምህርት ሚኒስቴርና በአገሪቱ መምህራን መካከል የተፈጠረውን ከፍተኛተ ችግር አስረዱ ።

በስብሰባው የትምህርት ሚኒስትር በበኩሉ ከኢመማ አመራር የተሰ ጠው ማብራሪያ መሠረተቢስ ነገር ነው በማለት ሲቃወም ፣ ጠቅላይ ሚኒ ስቴሩ ደግሞ እንደተባለው በየካቲት 11 ቀን መምህራኑ ሥራ የማቆም አር ምጃ እንዳይወስዱ ማድረግ የኢመማ አመራር ኮሚቴው አላፊነት እንደ ሆነ በብርቱ አስጠነቀቁ ።

በሌላ በኩል የፖሊስ ሠራዊትና የክብር ዘበኛ አዛዦች ሁለቱም በየ በኩላቸው የተባለው ችግር ወደ ሕብረተሰቡ ዘንድ መድረሱን በየፊናቸ ው እንደአረጋገጡ ገልጸው በአስቸኳይ ተገቢው መፍትሔ እንዲፈለግ ያስ ፈልጋል በማለት ከትምህርት ሚኒስትር የተሰነዘረውን አሳብ ተቃወሙ ።

በደሞዝና በሥርዓተ ትምህርት ጥያቄዎች የመምህራኑ ሥራ የማቆም ውሳኔ የተደረገው በጠቅላላ መምህራኑ ስምምነት በመሆኑ ፣ የኢመማ አመራር ኮሚቴ ብቻውን ለመለወጥ ሥልጣን እንደሌለው ተወካዮች በሚ ያሳምን ሁኔታ ስለገለጹ ፣ የኢመማ የክፍለ ሀገር ቅርንጫፍ ማህበራት ተወ ካዮች በሁለት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከአመራሩ ጋር ተነጋግረው በታኅሣሥ 12 ውሳኔ መሠረት በየካቲት 11 ቀን መም ህራኑ ሥራ እንዳያቆሙ የሚያደርግ ሌላ ውሳኔ እንዲያሳልፉ በአዱው ተወሰነ ። በታላቁ ቤተመንግሥት የዕለቱ የአርባ አምስት ደቂቃ ስብሰባ በዚሁ ውሳኔ አበቃ ።

በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ውስጥ የኢመማ የክፍለ ሀገር ማህበራት ተወካዮች ወደ አዲስ አበባ ገቡ ። ቅዳሜ የካቲት 2 ቀን የኢመማ የአመ ራር ኮሚቴና የክፍለ ሀገር ተወካዮች ከትምህርት ሚኒስቴር ባለሥልጣና

ች ጋር በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት አዳራሽ በመምህራኑ ደሞዝና በሥ ርዓተ ትምህርት ጥያቄዎች የሦስት ቀናት ክርክር ጀመሩ ።

በትምህርት ሚኒስቴር ባለሥልጣኖችና በኢመማ ተወካዮች መካ ከል የተጀመረው የከረረ ክርክር ገና ከፍጸሜው ሳይደርስ ፣ ሰኞ የካቲት 4 ቀን ሀያ አንድ የኢመማ የአመራርና የክፍለ ሀገር ተወካዮች ወደ ኢዮቤ ልዩ ቤተ መንግሥት ተጠርተው ለአዱውና ለመንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥ ልጣኖች በመምህራኑ ደሞዝና በሥርዓተ ትምህርት ጥያቄዎች በጽሑ ፍና በቃል ሰፊ ገለጻ አደረጉ ። የተወካዮቹ ማብራሪያ ከተሰማ በኋላ አዱው " ይህ በንባብ የቀረበው ነገር እውነት ከሆነ ከሚኒስትሮች ጋር በእንድነት ተነጋግራችሁበት ውጤቱን እንድናውቀው ይሁን " የሚል ትእዛዝ ሰጥተው በማስቱ ማክሰኞ የካቲት 5 ቀን ለአንድ ሳምንት የሥራ ጉብኝት ወደ ኤርትራ ከፍለ ሀገር ሄዱ ።

ከጥር 27 ቀን እስከ የካቲት 7 ቀን 1966 በመምህራን ሥራ የማቆም አድማ ጥያቄ ከቀድሞ ንጉሥና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር በማባር ታሪካዊ ክርክር ያካሄዱ የኢመማ ማዕከላዊ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና የክፍላተ ሀገር ቅርንጫፍ ማህበራት ተወካዮች የሚከተሉት ናቸው ። [7]

1. የኢመማ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት
2. የኢመማ ም/ ፕሬዚዳንት
3. » ዋና ፀሐፊ
4. » ም/ ዋና ፀሐፊ
5. » ገንዘብ ያዥ
6. የበጌምድር ቅርንጫፍ ማህበር ተወካይ
7. የትግሬ » » »
8. የአዲስ አበባ » » »
9. የወለጋ » » »
10. የሸዋ » » »
11. የሲዳሞ » » »
12. የከፋ » » »
13. የባሌ » » »
14. የኤርትራ » » »
15. የአርሲ » » »
16. የወሎ » » »
17. የኢሉባቦር » » »
18. የሐረርጌ » » »
19. የጐጃም » » »
20. የጐንደር » » »

ከአጼው በተሰጠው መመሪያ መሠረት ፣ ከየካቲት 4 እስከ 6 ቀን የኢመማ ተወካዮች ከትምህርት ሚኒስቴርና ከመንግሥት ሠራተኞች ማ ስተዳደሪያ ኮሚሽን ባለሥልጣናች ጋር እንደገና በያሬድ ሙዚቃ ትምህ ርት ቤት አዳራሽ በመምህራኑ ደሞዝና በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጥያ ቄዎች ለሦስት ተከታታይ ቀናት ያካሄዱት በጣም የከረረ ክርክር ፣ የደሞዝ ስሌትና የትምህርት ፍልስፍና ትችት በእጀንዳ ለቀረበው ችግር መፍትሔ ሳያስገኝ ቀረ ። [8] የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ዓላማና ታክቲክ ለችግሩ ተገቢ መፍትሔ ፈልጐ ማግኘት ሳይሆን በኢመማ ተወካዮች ላይ የሥል ጣን ተጽዕኖ አሳድረው መምህራኑን በየካቲት 11 ቀን ቀጠሮ መሠረት የሥራ ማቆም እርምጃ እንዳይወስዱ የሚያግድ የአጸፋ ውሳኔ በመምህራኑ ፍላጐትና ጥቅም ላይ እንዲያሳልፉ ማስገደድ ነበር ።

የሥርዓቱን ኃይለኛ የሆነ የላዕላይ መዋቅር በእጁ የያዘው የኢትዮ ጵያ ንጉሣዊ የገዥው መደብ እንደዚህ በኢመማ ተወካዮች ጉሮሮ ላይ ሲቆ ም በሌላ በኩል ጊዜና ሁኔታ በእርግጥ በኢመማ ተወካዮች ጐን ሆኖ ተገ ኘ ። ከጥር 27 ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 7 ቀን ድረስ በኢመማና በመንግ ሥት መካከል በመካሄድ ላይ የነበረውን ያልተመጣጠነ የፖለቲካ ትግል በጥሞና ይከታተሉ የነበሩት የአዲስ አበባ ተማሪዎችና አስተማሪዎች ፣ በቃል ፣ በጽሑፍና በተግባር መንግሥቱን በሕብረተሰቡ ዘንድ የማጋለጥ ብርቱ ዘመቻ ከፈቱ ። ማክሰኞ የካቲት 5 ቀን በደብረ ዘይት የአየር ኃይል አባሎች በአመጽ እርምጃ አዛዥ መኮንኖችን በቁጥጥር ሥር በማዋል በ መንግሥቱ ላይ የበለጠ ስጋት አሳደሩ ። ለኢመማ ተወካዮች ደግሞ የበ ለጠ ብርታትና ድፍረት ሰጡ ። ረቡዕ የካቲት 7 ቀን የአዲስ አበባ ተማሪ ዎች በኢመማ ጐን በመሰለፍ በከተማው ባለመኪናዎች ላይ የድንጋይ ጦርነት አካሄዱ ። የታክሲ ሹፌሮች አመጽ ደግሞ ለኢመማ ተወካዮች በ መንግሥቱ ላይ ሌላ የብርታትና የድፍረት ምንጭ ሆነ ።

በሌላ በኩል የመንግሥቱ ማስሚዲያ በታኅሣሥ 1962 በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የጥፋት ዘመቻ እንደከፈተው ሁሉ ፣ አሁን ደግሞ በኢመ ማ አካላትና አባላት ላይ ተመሳሳይ የጥፋት ዘመቻ አካሄደ ። የመንግሥቱ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ በየካቲት 7 ቀን 1966 እትሙ ቃል ፤

" የአዲሱን የትምህርት አጠቃላይ ጥናት መንፈስ በሚገባ ያልተገ ነዘቡ አንዳንድ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል ። አያስገርምም ። ማንኛውም አዲስ አሳብ ለጊዜው ግራ የሚያጋባ መሆኑ የታወቀ ነው ። አዲሱ የትምህርት አጠቃላይ ጥናት መንፈስና ዓላማ ዛሬ ያልገባቸው አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩ ነገ ከፀፀት ላይ ይወድቁ ይሆናል።ዋናው ቁም ነገር ግን ካለማወቅ ለኢትዮ

ጵያ የትምህርት ርምጃ እንቅፋት ከመሆን መቆጠብ ነው። በታሪክ ምዕራፍ ላይ ጥቁር ነጥብ ከጣሉ በኋላ መፀፀት ውጤት አያስገኝም። ትምህርትን ለማ ዳረስ የወጣውንእጅግ የሚያጓጓ እቅድ ሥራ ላይ ለማዋል እያንዳንዱ ኢት ዮጵያዊ ከፍተኛ መስዋዕት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ጊዜ ነው ። " [9]


ሐሙስ ቀን የካቲት 7 የትምህርት ሚኒስቴር ለኢመማ አመራር ኮሚቴ በጻፈው ደብዳቤ የመምህራን ደሞዝና የሥርዓተ ትምህርት ጥያቄ ዎችን በሚመለከት የሚወሰደው እርምጃ " ከላይ ውሳኔ ሲሰጥበት " በኢ መማ በኩል ለመምህራኑ ይገለጻል በማለት ጉዳዩን ዘጋ ። ዕለቱን የኢመማ ተወካዮች በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ችግሩ መፍትሔ አለማግኘቱን በግምባር ቀርበው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አስረዱ ። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ለኢመማ ተወካዮች በሰጡት መልስ ፤

" ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም የመምህራኑ አቤቱታ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በወቅቱ መልስ ባያገኝም ጉዳዩ ለግርማዊ ጃንሆይ መቅ ረቡንና ይኸው ተጠንቶ በአስቸኳይ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ይህንኑ በመምህራኑ ሹማምንት አማካይነት ለመምህራን በያሉበት እንዲገለጽ ማስፈለጉን ከማስገንዘባቸውም በላይ የትምህርት አጠቃላይ ጥናትም እንደ ጥላን የሚቆጠር ስለሆነ በየጊዜው እስፈላጊው ማሻሻያ እየተደረገለት ከሥራ ላይ የሚውል መሆኑን በተጨ ማሪ ገልጸዋል ። " [10]

ከዚያ በኋላ የኢመማ ተወካዮች በመንግሥቱ ፖሊስና ፀጥታ ኃይ ሎች ተከበው አንድ ሙሉ ቀንና ሌሊት የፈጀ ስብሰባ አድርገው በአሳለ ፋት ውሳኔ በየካቲት 11 ቀን የመምህራኑ የሥራ ማቆም እርምጃ የማይደ ግፉ መሆናቸውን ገልጸው በሌላ በኩል ውሳኔያቸውን የሚቃረን በአንድ ሳምንት ውስጥ በመምህራኑ ደሞዝና በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ጥያቄ ዎች ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ያደረጉት ክርክር ሁሉ ውድቅ መሆ ኑን የሚያሳይ ቃለጉባኤ ከውሳኔ ጋር ወደ ኢመማ ቅርንጫፍ ማህበራት አስተላለፉ ። በተጨማሪም በኮድ መልእክቶች ለኢመማ አካላትና አባላት ውሳኔው በበላይ ተጽዕኖ የተወሰደ እርምጃ መሆኑን አስታወቁ ። መንግ ሥት በበኩሉ የመምህራኑ የሥራ ማቆም እርምጃ በተፅዕኖ ውሳኔ የሚ ቀር መስሎት እስከ የካቲት 11 ቀን ተዝናንቶ ተቀመጠ ።

ይሁን እንጂ በታኅሣሥ 12 ቀን 1966 ታሪካዊው ውሳኔ መሠረት የኢመማ የክፍለ ሀገር አካላትና አባላት ማክሰኞ የካቲት 11 ቀን የሥራ ማቆም አድማ መቱ ። ዕለቱኑ በአዲስ አበባ የታክሲ ሹፌሮች ለሕዝብ አገ ልግሎታቸውን አቆሙ ። በሕዝቡ ብሔራዊ የአመፅ ግፊት በየካቲት 20 ቀን አሮጌው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፈረሰ ። የሕዝቡ የአመፅ እርምጃ በአገር አቀፍ ደረጃ ቀጠለ ። የጉልተኛው ሥርዓትና ዘመን ፈረሰ አዲስ ሥርዓትና ዘመን ተጀመረ።

1



2



የግርጌ ማስታወሻ

ክፍል አንድ

ምዕራፍ 1

ማዕከላዊው መንግሥትና የገባሩ ሥርዓት

1 Stephen U. Chukumba, *The Big Powers Aganist Ethiopia: Anglo- Franco- American Diplomatic Maneuvers During the Italo- Ethiopian Dispute*, 1934- 1938 (1977).

2 ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፤የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ (1982) ክፍል 2 ም. 8

3 ገብረ ሥላሴ ፤ የታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ (1959) ፤ ም. 39፣ 44 ።

4 Bairu Tafla, " Marriage as a Political Device: An Appraisal of a Socio- Political Aspect of the Menelik Period 1889-1916". *Journal of Ethiopian Studies*, vol. 10, No.1(1972), pp. 13-21;

መኮንን እንዳልካቸው (ራስ ቢትወደድ) ፤ መልካም ቤተሰቦች (1949) ።

5 ማሀተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ፤ ዝክረ ነገር (1962) ፤ ገጽ 52-53 ።

6 ገብረ ሥላሴ ፤ ዳግማዊ ምኒልክ ፤ገጽ 284 ።

7 ገብረ ሥላሴ ፤ ዳግማዊ ምኒልክ ፤ገጽ 336-338።

8 C.P. Rosenfield, *A Chronology of Menelik II of Ethiopia* (1976) P.232;

" በአዲስ አበባ ከተማ ርስት መግዛት ፤ " ማሀተመ ሥላሴ ፤ ዝክረ ነገር ገጽ ፤ 166-171

9 ገብረ ሥላሴ ፤ ዳግማዊ ምኒልክ ፤ ገጽ 334 ፤ 336 ።

10 ማሀተመ ሥላሴ ወ/ መ ፤ ዝክረ ነገር ገጽ 767-782 ፤ኃይለ ሥላሴ (አፄ) ፤ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በ2 ቅጽ (1966) ቅ1 ገጽ 148-149 ።

11 ማሀተመ ሥላሴ ፤ ዝክረ ነገር ገጽ 775-776 ፤ 792 ።

12 ኃይለ ሥላሴ ፤ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 140 ።

13 ኃይለ ሥላሴ ፤ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅ. 1 ገጽ 148-149 ።

14 Guebre Selassie Chronique du regne de Menelik II, ed., de Coppet, 2vols. (1930-),11 pp. 599-609; Paul Meıab, *Impressions* d' *Ethiopie*, 3 vols. (1922-29), III pp. 123-145; G. Montandon, *L' Esclavage en Ethiopie* (1932); M. Perham. *The Government of Ethiopia* (1969) pp. 217-236; R. Pankhurst, *Economic History of Ethiopia*, 1800-1935 (1968), pp. 73-134,

15 *Ibid., Impressions, III*, p. 123; *The Government*, pp. 219-220; Guebre Selassie *Menelik II*, II, pp. 601-603.

16 *Ibid., The Government*, p. 217; paulos Tzadua, *The Fetha Nagast: The Law of the kings*, (1968), chap. 31

17 *Ibid., The Fetha Nagast,* p. 175.

18 Merab, *Impressions,* III, p. 145.

19 Guebre Selassie, *Menelik,* II , p. 604; Pankhurst, *Economic* History, PP III, 124

20 *Ibid., Menelik* II, p. 603

21 Pankhurst, *Economic History* p. 84

22 Perham, *Government,* p. 225.

23 ኃይለ ሥላሴ ፤ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 59 ።

24 Pankhurst, *Economic History,* p. 119.

ምዕራፍ 2.

ብሔራዊ ኢንቴሌጂንሲያውና የጣሩ ሥርዓት

1 E. Gibbon, *The Decline and Fall of the Roman Empire,* vol 5. P. 66

2 Guebre Selassie, *Chronique de Menelik,* II, pp. 502-504.

3 Getahun Dilebo, " Historical Origins and Development of the Eritrean Problem 1889-1962, *A Current Bibliography on* African Affairs, vol. 7, No. 3 (1974), p. 233.

4 Aren, *Evangelical Pioneers in Ethiopia: Origins of the Evangelical Church Mekane Yesus* (1978)

5 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ አጼ ምኒልክና ኢትዮጵያ ፤ ገጽ 10 ።

6 አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ (ነጋድራስ)፤ " የዳግማዊ ምኒልክ ወቀሳ " ጥቅምት 1909 *Modern Ethiopia,* by. J. Tubiana(1980), pp. 3-10.

7 R. Greenfield, *Ethiopia: A New Political History* (1965)

8 G.J. Afevork ,*Guide du Voyageur en Abyssinie* (1908), p. 182.

9 *Ibid.,* p. 212.

10 *Ibid.,* pp. 213-214.

11 *Ibid.,* p. 214.

12 *Ibid.,* pp. 214-215.

13 *Ibid.,* p. 216.

14 *Ibid.,* p. 217.

15 *Ibid.,* p. 225.

16 *Ibid.,*

17 *Ibid.,* p. 227.

18 *Ibid.,* pp. 230-231.

19 *Ibid.,* p. 233.

20 *Ibid.,* p. 234.

21 *Ibid.,* p. 235.

22 *Ibid.,* p. 238.

23 *Ibid.,* p. 237.

24 አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ፤ "መዲወኤቦ " ፤ ብርሃንና ሰላም (ሐምሌ 18 ቀን 1921)።

25 አስቤ ኃይሉ ፤" ስለ መንግስት ጉዳት "፤ ብርሃንና ሰላም (ሐምሌ 14 ፤ 21 ቀን 1919) ።

26 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ (ነጋድራስ) አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ ገጽ 8 ፤ Addis Hiwet, *Ethiopia from Autocracy to Revolution* (1975). pp. 70-71.

27 ኃይለ ሥላሴ ፤ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅ.1 ም. 12

Ethiopia (Gov.), *The Ethiopian Penal Code of* 1930 (1941); *Bahru Zewde,* " Economic Origins of the Absolutist State in Ethiopia, 1916-1935" *Journal of Ethiopian Studies ES,* vol. 17(1984), pp. 1-29; R.J. Davis, *Fire on the Mountains: The Story of a Miracle, the Church in Ethiopia* (1966 F. P. Cotterell, *Rorn at Midnight* (1973); C.W. Duff,, *Cords of Love*: A *Pioneer Mission to Ethiopia* (1980); I. Lass- Westphal, "Protestant Missions During and After the Italio - Ethiopian War, 1935 - 1937". *Journal of Ethiopian Studies* vol. 10, No. 1 (1972), pp. 89-101.

28 አስቤ ኃይሉ ፤" ስለ መንግስትና ሕዝብ ጉዳት "፤ ብርሃንና ሰላም (ሐምሌ 14 ፤ 21 ቀን 1919)።

29 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር (1953) ፤ ገጽ 16 ።

30 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ገጽ 58 ።

31 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ገጽ 11።

32 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ ፤ገጽ 13-16

33 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ፤ ገጽ 88-103 ።

34 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ፤ገጽ 88 ።

35 ገብ ረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ፤ ገጽ 67 ።

36 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ፤ገጽ 75 ።

37 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ፤ ገጽ 127-128 ።

38 ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፤ መንግስትና አስተዳደር ፤ገጽ 97 ።

39 ደረሳ አመንቱ ፤" ስለጊዜው የጎንዝብ ችግር " ፤ ብርሃንና ሰላም (የካቲት 3 ቀን 1924)

40 ማህተመ ሥላሴ ገዝረ ነገር ገፅ 775 ።

41 "History of Japan", *The New Encyclopaedia Britannica,* 30 vols (1984), vol 10, pp. 78-91.

42 " Documentation Relating to the Dispute between Ethiopia and Italy" *League of Nations Official Journal,* vol. 16, No. 11 (November, 1935); A. Delboca, *The Ethiopian* War 1935-1941 (1965); A. Mockler, *Haile Sellassie war* (1984). J.H. Spencer *Ethiopia At Bay*: Personal; Accounts of the Haile Selassie Years (1984).

ምዕራፍ 3

1928—1933 ጦርነት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ውጤቶች

36-37, 75, 85-114.

1 Lapiso G. Dillebo, " Land Tenure, Underlying Cause of the Ethiopian Revolution " *Proceedings of the Fifth International Conference on Ethiopian Studies* (The University of Chicage, 1978), pp. 719-720.

2 A. Delboca, *The Ethiopian War* 1935 - 1941 (1965) pp. 232-233.

3 A Sbacchi, *Ethiopian Under Mussolini: Fascism and the Colonial Experience* (1985), pp *p. p.* 36, 137

4 *Ibid.,* 129; R. Greenfield, *Ethiopia A New Political History* (1965), pp. 272-281;

በጥቅምት 23 ቀን 1940 በዘውድ በአል በአደረጉት ንግግር አጼ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1928 ፡ ጦርነት በሰሜን በደቡብና በምሥራቅ የጦር ግንባሮች የጦር መሪዎችና እዝግቾች የነበሩትን 54 ከፍተኛ የመሰፍንቶችና መኳንንቶች የስም ዝርዝር ፡ እንዲሁም በ1928 - 1933 በእርበኝነት ትግል በአመራር ላይ የነበሩ 241 - ተራ - ዜጋ የጦር መሪዎች ንና እዝግቾችን የስም ዝርዝር ለገከረ ታሪክ እንዳአቀረቡ ይታወሳል ።

5 *Ibid.*, p. 205.

6 George L. Steer, *Sealed and Delivered* (1942), pp. 16-18.

7 Sbacchi, *Ethiopia Under Mussolini*, pp. 157- 166.

8 *Ibid.*, pp. 43, 85-93.

9 *Ibid.*, p. 157.

10 *Ibid.*, p. 158.

11 *Ibid.*, p. 159.

12 *Ibid.*, p. 160.

13 *Ibid* ., pp. 173-174.

14 *Ibid.*, pp. 161-165.

15 *Ibid.*, pp. 163-164.

16 Ethiopia (GOV). *Documents on Italian Warn Crimes*, 2 vols. (1949, 1950), I, P. 2

17 Sbacchi *Ethiopia Under Mussolini*, p. 163.

18 *Ibid.*

19 *Ibid.*

20 *Ibid.*

21 G. K. N. Travaskis, *Eritrea*: *A Colony in transition* 1941-52 (1960) pp. 132-133.

ክፍል ሁለት

የጅምር ካፒታሊዝም ላዕላይ መዋቅር

1933—1936

ምዕራፍ 1.

ፍጹማዊ የዘውድ ሥርዓት ምዕከልና

የመንግሥት አደረጃጀትና አገልግሎት

1. ፍስሐፁ ሐጉስ ፡ ዋንታዊና ዘመናዊ የኢትዮጵያ የኤርትራ ታሪክ (1956) ፡ ገፅ 147-153። Tekeste Negash, *Medicine for the Bite of the white snake*; *Notes on Nationalism and Resistance in Eritria*, 1890-1940 (1986),p. 41

2 Bairu Tafla, " Marriage as a Political Device "

3 Karl Marx, *A Contribution to the Critique of political Economy*, ed. with a Introduction by Maurice Dobb(1970), p.20.

4 *Ibid*: pp. 20-21.

5 የዘመኑ የትእዛዝ ፡ የድንጋጌና የአዋጅ ሕግ ትርጉም - አዋጅ የሕጉ ረቂቅ በብሔራዊ ሸንጉ ከጸደቀ በኋላ በንጉሡ ሕግ ሆኖ የሚታወጅ ፡ ድንጋጌ ሕጉ በንጉሡ ከታወጀ በኋላ ወደ ብሔራዊ ሸንጉ ቀርቦ ገና የሚጸድቅ ሲሆን ፡ የትእዛዝ ሕግ በብሔራዊ ሸንጉ ሳይጸድቅ በአጼው ውሳኔ ብቻ የሚጸና ሕግ ነበር ።

6 " የአሰሪዎች ማምለጥና መያዝ የተፈረደባቸው ፍርድ ታህሳስ 19 - ጥር 5 ቀን 1937 አንድ ያልታተመ የቤተመጻሕፍት ሰነድ ነው ። ተይዘውና ተፈርዶባቸው ከሞቱት አሰሪዎች አንዱ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ነው ።

7 ኃይለ ሥላሴ ፡ ሕይወቴና (አፂ) የኢትዮጵያ እርምጃ ፡ ቅ 2 ገፅ. 323 ።

8 ያገር ግዛት ሚኒስቴር መጽሔት ፡ ከ1958 በፊት የወጡ ልዩ ልዩ እትሞች የተለተመ መረጃ ነው ።

9 የኢትዮጵያ መንግሥት ፡ " የ1938 በጀት " ነጋሪት ጋዜጣ ፡ አዋጅ ቁጥር 80 (ነሐሴ 21 ቀን 1938) ።

10 ከአንድ ያልታተመ የቤተ መጻሕፍት ሰነድ ነው ።

11 በጥቅምት 23 ቀን 1940 በአጼው የዘውድ ክብረ በዓል የተደረገ ንግግር ።

ምዕራፍ 2

የሃይማኖት ትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ

British, Gov., *Correspondence Respecting Abyssinia* 1846-1868 (1868), pp.172-73; Zeneb, The Chronicle of king Theodore, ed. by E. Littmann (1902), pp. 30-45; R. A. Caulk, "Religion and the State in Nineteenty Century Ethiopia", *Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 1 1 (1972) pp. 23-41.

2 D. Grummey, *Priests and politicians*: *Protestants and catholic Missions in Orthodox Ethiopia* 1830-1868 (1972); G. Aren, *Evangelical Pioneers in Ethiopia*: *origins of the Evangelical Church Mekane Yesus* (1978).

3 *Ibid.*, *Evangelical Poineers*, p. 312.

4 Wolde Mariam, *Chronique de Theodros* II, Roi des Rois d' Ethiopie, ed. by C. Mondon-Vidailhet (1904), p. 32; ገብረሥላሴ ፡ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ (1959)፡ ገጽ 67 ።

5 ገብረሥላሴ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ 67 ።

6 ገብረ ሥላሴ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ 68 - 69 ።

7 ገብረ ሥላሴ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ 86 - 92 ።

8 ገብረ ሥላሴ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ 93 ፡ አጥመጊዮርጊስ ፡ የጋላ ታሪክ በ2 ቅጽ ፡ (ያልታተመ ጽሑፍ በብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት) ቅ.2 ገጽ 48 - 49 ፡ ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፡ የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ (1982) ፡ ገጽ 68 ፡

9 ገብረ ሥላሴ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገጽ 233 ። E. Starkie, *Arthur Rimbaud in Abyssinia* (1937), pp. 56-57, 92, 107, 114; R.A. Caulk, "The Occupation of Harar: January 1887", *Journal of Ethiopian Studies*, Vol, 9 No.2(1971), p. 3; H. Marcus, *The Life and Times of Menelik* II: Ethiopia 1844-1913 (1974), pp. 60-61.

10 *Ibid.*, "The Occupation of Harrar".

11 *Ibid.*, pp. 17-18; R.A. Caulk, " Menelik's Conquest and Local Leaders in Harar", History Department, Faculty of Arts, Addis Ababa University (ND); Seifu Metaferia, " Sixteenth Letters of Ras Makonnen and his Sons to Haji Ahmad Abonn of Harar " *Journal of Ethiopian Studies*, vol. 12 No. 2 (1974), p.180.

12 " በቁርጥ ስለሚገብሩ አገሮች ፣ " ግሁተመ ሥላሴ ዝክረ ነገር (1942) ገጽ 165

13 ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፣ የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ፣ ገጽ 21 ።

14 G.W.B. Huntingford,"Arabic Inscriptions in Southern Ethiopia", *Antiquity*, Vol.29 (1955).

15 E. Cerulli, *Ethiopia's Relations with the Muslim World in* UNESCO, *History of Africa*, Vol. III (1988), pp. 575- 585; Jean Doresse, *Histoire Sommaire de la Corne Oriental de L'Afrique* (1971) pp. 234-337; J.S. Triminghham, *Islam in Ethiopia* (1952), pp.58-62 95-97; Arab- Faqih, *Histoire* de la Conquete de L' Abyssinie, tr. and ed., R. Basset (1897); E. Wagner, "Three Arabic Documents on the History of Harar" *Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 12, No. 1 (1974), pp. 213-224;

PP. 213 - 224 ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፣ የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ገጽ 152-153 ።

16 E. Ullendorff, *Ethiopia and the Bible* (1967), pp. 63-64.

17 Aren, *Evangelical Pioneers*, pp. 13, 43.

18 Ullendorff, *Ethiopia and* the *Bible*, p.65.

19 Aren, *Evangelical Pioneers*, p. 44.

20 ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፣ የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ም. 5፣ 6፣
Getahun Dilebo, „Early Portuguese Imperialism in Ethiopia 1490- 1632; Origins, Responses, Consequences", M.A. Thesis (Howard University, Wash. D.C., 1971), Chap.7

21 *Ibid.* " The Portuguese in Ethiopia", p. 146; R. Pankhurst, *An Introduction to the Economic History of Ethiopia* (1961), p. 85.

22 Getahun Dilebo " The Portuguses in Ethoipia", pp. 143 - 159.

23 D. Richard, *Modern Europe* 1789- 1945 (1969), pp. 40-55.

24 Henry Salt, -A *Voyage to Abyssinia, and Travels into theInterior of that Country*, 1809-1810 (1814); Charles Beke, *The French and British in the Red Sea* (1962), pp. 5-6.

25 Beke, *The French and* British *in the Red Sea*, pp. 8-12.

2 6 *Ibid.*, p.10.

27 *Ibid.*, Ullendorff, *Ethiopia and the Bible*, p. 65.

28 Beke, *The French and English in the Red Sea*, pp. 10-17.

29 *Ibid.*, pp. 7-9.

30 *Ibid.*, pp. 14-17; Aren *Evangelical Pioneers*, pp. 48-84.

31 ገብረሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 92 ።

32 ገብረሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 180 ።

33 R. Pankhurst " The Foundations of Education, Printing Newspapers, Book production, Libraries and Literacy in Ethiopia", *Ethiopia observer*, Vol. 6, No. 3 (1962), p. 248

34 Aren, *Evangelical Pioneers*, pp. 177-180.

35 *Ibid.*,pp. 114-123.

36 *Ibid.*, pp. 130. 234, 249, 274, 378, 387-396.

37 *Ibid.*, pp. 171-203, 211-230.

38 *Ibid.*, pp. 383-385.

39 *Ibid.*, pp. 312-313.

40 *Ibid.*, pp. 369-370.

41 *Ibid.*, 387-437.

42 *Ibid.*, p. 162.

43 *Ibid.*, p. 402.

44 Ibid., p. 432;
ገብረሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 336 ፣
Tekeste Negash, *The Crisis of Ethiopian Education: Some Implications for Nation-Building* (1990), p. 1; pankhurst, " The Foundation", p. 259.

45 ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ፣ ገጽ 266 ፣281—282

46 ላጵሶ ጌ. ድሌቦ ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ ፣ ገጽ 267 — 268 ።

47 ገብረ ሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 86 - 93 ፣ 180 ፣ 326 ።

48 ገብረ ሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ ፣ 326 ።

49 V. Stitz, "Distribution and Foundation of Churches in Ethiopia", *Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 13, No. 1 (1975), pp. 11-36

50 *Ibid.*, p. 12.

51 *Ibid.*, pp. 18, 36.

52 Nathaniel Pearce, *The Life and Adventures of Nathaniel* Pearce 1810-1819, 2 Vols. (1831) II, p. 51; Seven Rubenson, *The Survival of Ethiopian Independence* (1976, pp. 34, 62-68 349, 357.

53 ከ1870 የቦሩ-ግዳ ጉባኤ ውሳኔ በኋላ በአገሪቱ በሃይማኖት በፖለቲካና በኢኮኖሚ ፣ በማኅበራዊ ጉዳዮች የማዕከል አቡኖች በተለይ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናችና መምህራን በአጠቃላይ በሕብረተሰቡ ዘንድ የነበራቸውን ኃይል በሚመለከት የመንግሥቱ ለማ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ (1959) ትምህርታዊ ሰነድ ነው ።

54 -Aren , *Evangelical Pioneers*, p. 277.

55 ግሁተመ ሥላሴ ዝክረ ነገር ገፅ 54

56 ግሁተመ ሥላሴ ዝክረ ነገር ገፅ 504

57 Tekeste Negash,"Ethiopian Education", pp. 1-2; Pankhurst, "The Foundations", pp 279-280.

58Aren, *Evangelical Pioneers*, p. 433.

59 *Ibid.*

60 *Ibid.*, pp. 433-437

